# አዲስ ዘመን

እኛንድ

እሁድ 83 ዓመት ቁጥር 342 ነሐሴ 12 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




## ውጤታማ ሲቪል ሰርቪስ እንዴት ይገነባል?

ሳሙኤል ወንደሰን

ዜና ትንታኔ

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ውጤታማነቱን አደጋ ላይ የሚጥሉ እልፍ ውጣ ውረዶችን እየታገለ ነው። ሙስና፣ የአቅም ማነስ፣ ብልሹና የተጓተተ አሰራር የሕዝቡን አመኔታ በመሸርሸር የአገልግሎት አሰጣጥ ላይ እንቅፋት ሆነዋል። መንግሥት የሲቪል ሰርቪሱን መልሶ ለማነቃቃት ማሻሻያ ቢጀምርም ተጽኖአቸው ግን አሁንም ይታያል።

ለመሆኑ ውጤታማ ሲቪል ሰርቪስ እንዴት መገነባት ይቻላል? በመንግሥት አገልግሎት (ሲቪል ሰርቪስ) ሥርዓት ውስጥ የሚስተዋሉ ዋና ዋና ችግሮች ምንድን ናቸው? ችግሮቹ እንዴት ሊፈቱ ይችላሉ? በሚሉና ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ የዘርፉን ምሁራን ጠይቀናል።

የሕዝብ አመራር እና የፖሊሲ ጥናት ምሁር እንዳለ ኃይሌ (ዶ/ር)፤ አንድ መንግሥት ሶስት መሠረታዊ ክፍሎች አሉት። ሕግ አውጪ፣ ሕግ ተርጓሚና ሕግ አስፈፃሚ። ሲቪል ሰርቪስ የምንለው በሕግ አስፈጻሚው ስር የምናገኘው መዋቅር መሆኑን ገልጸዋል።

ሕግ አስፈጻሚ ስንል ፕሬዚዳንታዊ ሥርዓት ባላቸው፣ በፕሬዚዳንቱ የሚመራው ሲሆን፤ እንደኛ ፓርላሜንታዊ ሥርዓት ያላቸው ደግሞ በጠቅላይ ሚኒስትር የሚመራና

ውጤታማ ሲቪል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## የባንኮች ውህደት ጉዳይ

ቃልኪዳን አሳዬ

ዜና ትንታኔ

የዘመነ የአሰራር ሥርዓት እና ከፍተኛ ካፒታል ያላቸው የውጭ ባንኮች ወደ ሀገር ውስጥ ሲገቡ፣ የሀገር ውስጥ ባንኮች ጠንካራና ተወዳዳሪ ሆነው ለመውጣት ተዋህደው መሥራት እንዳለባቸው ሲነገር ቆይቷል፡፡

ብሔራዊ ባንክም የባንክ ሥራ አዋጅን ለማሻሻል ባዘጋጀው አዲስ ረቂቅ ውህደትን የተመለከተው አንቀጽ እንዲካተት የተፈለገበት አንዱ ምክንያት ባንኮች ካልተዋሀዱ በቀር ተወዳዳሪ ይሆናሉ ተብሎ ስለማይታመን እንደሆነ በምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች ይነሳል፡፡

የባንኮች ውህደት... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




## ለሌማት ታስቦ ለገበያ የተትረፈረፈው ምርት

ሄለን ወንድምነው

ዜና ሀተታ

ወይዘሮ ጽላተማርያም ተመስገን በዶሮ እርባታና በንብ ማነብ የተሰማሩ እናት ናቸው፡፡ የንብ ማነብ ሥራውን ከጀመሩ አራት ዓመታትን ተሻግረዋል፡፡ አሁን ላይ 375

ለሌማት ታስቦ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ጽላተማርያም ተመስገን



ወጣት ሰውነት ሸዋደርጋ



አቶ መላኩ ታደሰ



ወጣት አደሸሹም አስሙ
















## ዜና

# “ከምርታማነታችን ጎን ለጎን የቁጠባ ባህላችንን ካላዳበርን ከድህነት መውጣት አንችልም“

-አቶ ሽመልስ አብዲሳ
የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት



**አስቴር ኤልያስ**

ሳጉሬ፡- በኦሮሚያ ክልል ከሚካሄደው የልማት ሥራ ጎን ለጎን የቁጠባ ባህልን ማዳበር ካልተቻለ ከድኅነት መውጣት አይቻልም ሲሉ የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት አቶ ሽመልስ አብዲሳ ገለጹ:: ፕሬዚዳንቱ በአርሲ ዞን በሊሙና ቢልቢሎ እና በዲገሉና ጢጆ ወረዳዎች እየተከናወኑ ያሉትን የልማት እንቅስቃሴዎች ጎብኝተዋል::

አቶ ሽመልስ፣ በአርሲ ዞን በሊሙና ቢልቢሎ እንዲሁም በዲገሉና ጢጆ ወረዳዎች በክላስተር እየለማ ያለውን ስንዴ እና ከብቶችን በሰው ሰራሽ የማዳቀል ዘዴ እየተከናወነ ያለውን ስራ ጎብኝተዋል::

ፕሬዚዳንቱ በጉብኝቱ ወቅት እንዳስታወቁት፤ የአርሲ ዞን ለምና በሰፊው የሚታረስ መሬት አለው፤ ሕዝቡም ሰርቶ የማይጠግብና ባህሉን አክባሪ ነው:: ይሁንና ዋናው ጉዳይ በሰፊው ማምረት መቻል ብቻ ሳይሆን የቁጠባ ባህል ማዳበር ያስፈልጋል:: የቁጠባ ባህልን ማዳበር ካልተቻለ ከድኅነት መውጣት የሚታሰብ አይሆንም ብለዋል::

ካልቆጠብን ባለሀብቶች መሆን አንችልም ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ቁጠባን ባህል በማድረግ ከአርሶ አደሮች መሃል በርካታ ባለሀብቶች መፍጠርና ብልጽግናን ማረጋገጥ እንደሚቻል ተናግረዋል::

ሁሉም የቁጠባ ደብተር ሊኖረው እንደሚገባም ጠቅሰው፤ ሕዝቡ መሬት፣ ተስማሚ የአየር ንብረት፣ ማዕድንና ሌሎችም የተፈጥሮ ሀብት እያለው ሀብት ግን የለውም ብለዋል:: አርሶ አደሩ በኢኮኖሚው ጠንካራ ይሆን ዘንድ ጠንክሮ መስራትና መቆጠብ ይጠበቅበታል ሲሉ አብራርተዋል::

ማንኛውም ምርት በአካባቢያችሁ ብቻ ተወስኖ መቅረት የለበትም፤ ይልቁኑ ከሀገር አቀፍ አልፎ እስከ ውጭ ገበያ ድረስ መቅረብ የሚችልበትን ሁኔታ መፍጠር ይገባል ብለዋል::

በተለይ አርሲን የወተት ባህር ማድረግ እንደሚቻልም ጠቁመው፤ ይህ የሚሆነው ግን ጠንክሮ በመስራትና አሁን ካለው የወተት ምርት በእጥፍ ድርብ ማምረት ሲቻል መሆኑን አስገንዝበዋል::

በአሁኑ ወቅት በክልሉ የተለያዩ ትልልቅ ስራዎች እየተሰሩ መሆናቸውንም ገልጸው፤ ይህም ተጠናክሮ እንዲሄድ የሚያበረታቱ መሆኑን አስታውቀዋል::

በጉብኝቱ ወቅት ያዩት በክላስተሮቹ ላይ የተሰራው ስራ መልካም መሆኑን ጠቅሰው፤ በከብት ዕርባታ ላይ እየተሰራ ባለው ስራ ላይ የበለጠ ለውጥ ማምጣት ይጠበቃል ብለዋል::

የአርሲ ዞን ዋና አስተዳዳሪ አቶ ኢብራሂም ከድር፣ ዞኑ በሚያመርተው ምርት የአገር ባለውለታና ዋልታም ጭምር ነው ብለዋል:: ከክልሉ የወረደውን ኢንሼቲቭ ተግባራዊ በማድረጉ በኩል የተለያዩ ስራዎች እየተሰሩ ነው:: በክላስተር እየተመረተ የሚገኘው ስንዴ፣ ገብስ፣ አተርና ባቄላም ጭምር ነው ብለዋል::

እንደ አቶ ኢብራሂም ገለጻ፤ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት በሰው ሰራሽ ከብትን የማዳቀል ስራ ከ35 ሺ በላይ ጥጆች መወለድ ችለዋል:: በዞኑ በወተት ምርት ትልቅ ስራ እየተሰራ ሲሆን፣ ይህን ተከትሎ የገበያ ችግር ተፈጥሯል:: ይሁንና ከጋላማ ዩኒየን ጋር በመነጋገር ወተት የሚቀነባበርበት ፋብሪካ እንዲገነባ በመደረግ ላይ ይገኛል::

# የመኪና መገጣጠሚያ በሙሉ አቅሙ ወደ ሥራ ሲገባ ለአንድ ሺህ ዜጎች የሥራ እድል ይፈጥራል

## - በአንድ ወር 30 የኤሌክትሪክ አውቶቡሶች ለገበያ ይቀርባሉ

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በደብረብርሃን ከተማ የገነባው የመኪና መገጣጠሚያው በሙሉ አቅሙ ወደ ሥራ ሲገባ ለአንድ ሺህ ዜጎች የሥራ እድል እንደሚፈጥር የላይነህ ክንዴ ግሩፕ የፌቤላ ኢንዱስትሪ አስታወቀ:: በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ 30 አውቶቡሶች ለገበያ እንደሚቀርቡ ተመላክቷል::

በፌቤላ ኢንዱስትሪ የደብረብርሃን መኪና መገጣጠሚያ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ መሐመድ አህመድ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የመኪና መገጣጠሚያው በተጠናቀቀው 2016 በጀት ዓመት ወደ ሥራ ገብቷል::

ፋብሪካው ወደ ምርት የገባው 40 በመቶ የማምረት አቅሙ ሲሆን፤ በቋሚነትና በጊዜያዊ ለ400 ዜጎች የሥራ እድል ፈጥሯል:: በቀጣይ በሙሉ አቅሙ ማምረት ሲጀምር በቀን 12 ተሽከርካሪዎችን ማምረትና ለአንድ ሺህ ዜጎች ቋሚ የሥራ እድል የሚፈጥር ነው::

እንደ ሥራ አስኪያጁ ገለጻ፤ ፋብሪካው ሥራ ከጀመረ ጀምሮ 216 ኤሌክትሪክ ሚኒባሶችን እና ሁለት የከተማ አውቶቡሶችን ለገበያ አቅርቧል:: 30 የከተማ አውቶቡሶች በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለገበያ ይቀርባሉ:: በቀጣይም 100 አውቶቡሶችን ለመገጣጠም እቃ ከውጭ እየገባ መሆኑን አመላክተዋል::

ፋብሪካው ወደ ምርት መግባቱ ውጪ ተገጣጥመው የሚገቡ ተሽከርካሪዎችን በሀገር ውስጥ ለመተካት፣ ለቴክኖሎጂ ሽግግርና ለሥራ እድል ፈጠራ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል ብለዋል::

የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ በሀገር ውስጥ መገጣጠሙ ሀገሪቱ ያላትን ከፍተኛ የሆነ ኤሌክትሪክ ኃይል አቅም ለመጠቀም እና ለነዳጅ የሚወጣውን የውጭ ምንዛሬ ለማስቀረት ሚናው ከፍተኛ መሆኑን ገልጸዋል::

የተሽከርካሪዎች የነዳጅ ወጪ እና የኤሌክትሪክ ኃይል ፍጆታ ከፍተኛ የሆነ ልዩነት አለው ያሉት ሥራ አስኪያጁ፤ ለማነጻጸር ያህልም አንድ በነዳጅ የሚሰራ የከተማ አውቶቡስ 560 ኪሎ ሜትር ለመጓዝ ከ30 እስከ 40 ሺህ ብር የሚያስወጣ ነዳጅ ይጠቀማል:: የኤሌክትሪክ አውቶቡሶች ግን 500 ብር ባልሞላ የኤሌክትሪክ ኃይል



ፎቶ፡-አዩብ ተፈሪ

540 ኪሎ ሜትር መጓዝ ይችላሉ ሲሉ አብራርተዋል::

ተሽከርካሪዎቹ የውጭ ምንዛሬን ከማስቀረት ባለፈም ድምጽ አልባና ወደ ከባቢ የሚለቁት ጭስ አለመኖሩ በሀገሪቱ አረንጓዴ ትራንስፖርትን መገንባት ያስችላሉ ብለዋል::

ለፋብሪካው ከውጭ ምንዛሬ እጥረቱ በተጨማሪ በዘርፉ የሰለጠነ በቂ የሰው ኃይል፣ ግብዓት የሚሆኑ መሳሪያዎችን የሚያመርት የብረት ማቅለጫ ፋብሪካ በሀገር ውስጥ አለመኖሩ ተግዳሮት መሆኑን አንስተዋል::

ችግሩን ለመፍታት ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር በትብብር በመስራት ተማሪዎች ከንድፈ ሃሳብ በተጨማሪ በተግባር ሰልጥነው እንዲወጡ በማድረግ በዘርፉ ብቁና ተወዳዳሪ የሰው ኃይልን ለማፍራት እየሰሩ እንደሚገኝ አስረድተዋል::

የፌቤላ ኢንዱስትሪ ደብረብርሃን መኪና መገጣጠሚያ በፈጠረው የሥራ እድል ተጠቃሚ የሆነው አለበል አድማሱ በበኩሉ፤ በሥራ ዕድሉ እራሱን ማስተዳደር እንዳስቻለውና በንድፈ ሃሳብ የተማረውን በተግባር በመስራት ሙያዊ ክህሎቱን ለማዳበር እንደረዳው ተናግሯል::

በፋብሪካው ውስጥ ከቻይናዎች ጋር በጋራ እንደሚሰራ ገልጾ፤ ይህም የሥራ ባህልንና በኢትዮጵያ የሌሎች ቴክኖሎጂንና ሙያዊ ክህሎትን ለመማር አግዞናል ብሏል::

ፋብሪካው ወደ ሥራ መግባቱ በኢንጂነሪንግ ዘርፍ ያለውን የሥራ አጥ ቁጥር ለመቀነስና የውጭ ምንዛሬን ለማዳን ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት አመላክቷል::

# የዝንጀሮ ፈንጣጣ በሽታን ለመከላከል ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል

**ማህሌት ብዙነህ**



አዲስ አበባ፡- የዓለም አቀፍ አሳሳቢና ድንገተኛ የኅብረተሰብ ጤና አደጋ የሆነውን የዝንጀሮ ፈንጣጣ በሽታን ለመከላከል ማህበረሰቡ ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊያደርግ እንደሚገባ የጤና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የጤና ሚኒስቴር ዴኤታ ዶክተር አየለ ተሾመ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የዝንጀሮ ፈንጣጣ ኤምፖክስ በሚባል ቫይረስ አማካኝነት የሚመጣ ሲሆን፤ በወረርሽኝ መልክ ሊከሰት የሚችል በሽታ ነው፡፡ ከእንስሳት ወደ ሰው ከፍተኛ የመተላለፍ ባህሪ ስላለውም ማህበረሰቡ ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊያደርግ ይገባል፡፡

የበሽታው ዋነኛ መገለጫው ቆዳ ላይ የሚወጣ ቁስል ወይም ሽፍታ መሆኑን ገልጸው፤ ሽፍታ የወጣበት ቆዳ የመቅላት ከዛም አብጦ ፈሳሽ የመቋጠር ምልክት የሚያሳይ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ ቁስሉም በየትኛም የሰውነት አካል ላይ የሚከሰት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

እንዲሁም በሽታው ሲጀምር ትኩሳት፣ ራስ ምታት፣የድካም ስሜት፣ የመገጣጠሚያ ህመምና ድካም የሚታዩ ምልክቶች መሆናቸውን አስታውቀው፤ ምልክቶቹም ብዙውን ጊዜ ከ2 እስከ 4 ሳምንታት ይቆያሉ ብለዋል፡፡

የዝንጀሮ ፈንጣጣ በሽታው ካለበት ሰው ወይም እንስሳ በንክኪ የሚተላለፍ ሲሆን፤ የቆዳ ቁስል ወይም የሰውነት ፈሳሾች ንክኪ፣ በበሽታው ከተያዘ ሰው በትንፋሽ ፣ በግብረ ሥጋ ግንኙነት እና በቆዳ ለቆዳ ንክኪ፣ የተያዘ ሰው ተጠቅሞባቸው ከተበከሉ እቃዎች ንክኪ የሚተላለፍ መሆኑንም አስታውቀዋል፡፡

በሽታው እንዳይተላለፍ ለመከላከልም በበሽታው ከተያዘ ሰው ጋር ንክኪ አለማድረግ፣ የእጅን ንጽህና በሳሙና እና በውሃ ወይም በሳኒታይዘር መጠበቅ፣ ማስክ ማድረግ፣ ከሌሎች ጋር የምንጋራቸው እቃዎች ንጽህና መጠበቅ ብሎም ከእንስሳት ጋር ግንኙነት ያላቸው ሰዎች ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡

እንዲሁም በሽታው የተገኘበት ሰው ራስን ከሌሎች ሰዎች በማግለል ወይም ኳራንቲን በማድረግ ከሌሎች ጋር የቅርብ ግንኙነት ከማድረግ በመቆጠብ በሽታው እንዳይተላለፍ ማድረግ የሚገባ መሆኑን ዶክተር አየለ ገልጸው፤ ኅብረተሰቡ የበሽታውን ምልክቶች በሚያይበት ጊዜ በቅርቡ ባለው ጤና ተቋም በመሄድ ህክምና ማግኘት ይኖርበታል ብለዋል፡፡

ሚኒስቴሩም ይህ በአንዳንድ የዓለም ሀገራት የተከሰተውን የዝንጀሮ ፈንጣጣ በሽታ ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገባ ለመከላከል የሚያስችሉ የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

በዚህም የኅብረተሰብ ጤና አደጋዎች ማስተባበሪያ እና ምላሽ ማዕከል በማቋቋም ሀገሪቱ ከሌሎች ሀገራት ጋር በሚያገናኙ በሁሉም ድንበሮች እና አየር መንገድ ላይ የበሽታ ቅኝትና ምላሽ ሥራ በመሥራት ተገቢውን ጥንቃቄ የማድረግ ሥራዎችን በመሥራት ላይ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

እንዲሁም በበሽታው ዙሪያ ኅብረተሰቡን ለማስገንዘብ ስለ ቫይረሱ በማስተማር በሽታውን አስቀድሞ መከላከል የሚያስችሉ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑንም ዶክተር አየለ አስታውቀዋል፡፡

ዶክተር አየለ በሽታው በቀጥታ ከሰው ወደ ሰው ሆነ ከእንስሳት በንክኪ የሚተላለፍ እንደመሆኑ መጠን የበሽታውን ምልክቶች የሚያሳይ ማንኛውም ሰው በአቅራቢያው ወደሚገኝ የጤና ተቋም ሪፖርት እንዲያደርግ ወይም በ952 እና 8335 ነጻ የስልክ መስመር ጥቆማ እንዲደረግ አሳስበዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## በአንድ ጀንበር 600 ሚሊዮን ችግኞችን የመትከል ጥሪ ምላሽ በመስጠት ዳግም ታሪክ እንጻፍ!

ኢትዮጵያ አንድም የአየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖን ለመቀልበስ፤ አንድም ከደን የሚገኘውን ዘርፈ ብዙ ትሩፋት ለመቋደስ እና የምግብ ዋስትና፣ የስራ ዕድል ፈጠራና መሰል ጉዳዮችን ለማሳካት በሚያስችላት መልኩ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብርን እየተገበረች ስድስተኛ ዓመት ላይ ደርሳለች፡፡ የዚህ ተግባሯ አንዱ መገለጫ ደግሞ በየአመቱ እያከናወነች የዘለቀችው በአንድ ጀንበር በመቶ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ችግኞችን የመትከል ተግባሯ ነው፡፡

በዚህ ረገድ ሐምሌ 22/2011 ዓ.ም በአንድ ጀንበር 200 ሚሊዮን ችግኞች የመትከል መርሃ ግብር ደግሞ የመጀመሪያው የአንድ ጀንበር ችግኝ ተከላ ንቅናቄ ሲሆን፤ በዚህም በእለቱ 20 ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን የተሳተፉበት 354 ሚሊዮን ችግኞችን በመትከል ከእቅድ በላይ የተከናወነ ተግባር ነበር፡፡ ይሄ መርሃ ግብር ለየት የሚያደርገው በሕንድ ተይዞ የነበረውን የአንድ ጀንበር ችግኝ የመትከል ክብረወሰን ኢትዮጵያ እንድትረከብ በማድረጉ ነው፡፡

በዚህ መልኩ የተጀመረው እና በአራት ምዕራፎች ተከፋፍሎ 20 ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል የታቀደለት የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር፤ በአራት ዓመታት ጉዞው እና በመጀመሪያው ምዕራፍ ማጠናቀቂያ 2014 ዓ.ም ላይ 25 ቢሊዮን ችግኞችን በመትከል ከእቅድ በላይ የተሳካበት፤ በአንድ ጀንበር የችግኝ ተከላ መርሃ ግብሮችም ኢትዮጵያ የራሷን ክብረ ወሰን እያሻሻለች የሄደችበት፤ በሂደቱም በአማካይ በየዓመቱ 20 ሚሊዮን ዜጎች እየተሳተፉበት የተጓዘ ነበር፡፡

የመጀመሪያውን ምዕራፍም የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር መጠናቀቅን ተከትሎ፣ በ2015 ዓ.ም አንድ ብሎ የጀመረው የሁለተኛው ምዕራፍ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብርም በማጠቃለያው 25 ቢሊዮን ችግኞችን የመትከል እና አጠቃላይ በመርሃ ግብሮቹ የተተከሉ ችግኞችን 50 ቢሊዮን የማድረግ ግብ ያስቀመጠ ነው፡፡ በዚህ ምዕራፍ የመጀመሪያ ዓመት ሥራም ለዓመቱ የተቀመጠውንም ሆነ በአንድ ጀንበር ለመትከል የታሰበውን ከእቅድ በላይ ማሳካት ተችሏል፡፡

ለምሳሌ፣ ሐምሌ 10/2015 ዓ.ም በተካሄደ በአንድ ጀንበር የ500 ሚሊዮን ችግኝ ተከላ መርሃ ግብር፤ ኢትዮጵያ ዳግም የራሷን ክብረወሰን ያሻሻለችበትን የችግኝ መጠን መትከል ችላለች፡፡ በዚህ መርሃ ግብር የተያዘው ግብ 500 ሚሊዮን ችግኞችን በአንድ ጀምበር የመትከል ሲሆን፤ መላው ኢትዮጵያውያን ባደረጉት ከፍ ያለ ርብርብ በእለቱ መርህ ግብር 566 ሚሊዮን 971 ሺህ 600 ችግኝ መተከላቸውን ነው በወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የገለጹት፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በወቅቱ እንዳስታወቁት፤ በእለቱ በ302 ሺህ ሄክታር መሬት ላይ የችግኝ ተከላ የተካሄደ ሲሆን፤ የተተከሉት ችግኞች ቁጥር በጂኦስፓሻል መረጃ መሠረት የተጠናቀረ ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር ግን በጂኦስፓሻል ባልተካተቱ አካባቢዎች የተተከሉ ችግኞች በመኖራቸው የችግኞቹ ቁጥር ከዚህም ከፍ ሊል ይችላል፡፡ ይሄ ደግሞ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር የአየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖን ለመቋቋም እያስቻላትም፤ መርሃ ግብሩ እንደ ሀገር ካለው ዘርፈ ብዙ ፋይዳ ተጠቃሚ እንድትሆንም እያደረጋት ይገኛል፡፡

ዘንድሮም ለተከታታይ ስድስተኛ ዓመት ወይም የሁለተኛው ምዕራፍ ሁለተኛ ዓመት መርሃ ግብር ከፍ ባለ ውጤት ታግዞ እየተከናወነ ይገኛል፡፡ በ2016 ዓ.ም የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር 6 ነጥብ 5 ቢሊዮን ችግኞች ለመትከል በተደረገው ዝግጅት ከሰባት ቢሊዮን በላይ ችግኞች ተዘጋጅተው በተከላ ሂደት ላይ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ችግኞችም 60 በመቶ የሚሆኑት ለጥምር ግብርናና ፍራፍሬ፣ 35 በመቶ የሚሆኑት ለደን ልማት፣ እንዲሁም አምስት በመቶ የሚሆኑት ለውበት የሚሆኑ ናቸው፡፡

በዚህ ዓመትም እንደ ቀደሙት ሁሉ በአንድ ጀንበር 600 ሚሊዮን ችግኞች ተከላ መርሃ ግብር የሚካሄድ ሲሆን፤ ይሄም በሁለት መልኩ የሚገለጽ ነው፡፡ አንዱ እስካሁን የተከናወኑ የአንድ ጀንበር መርሃ ግብሮች ምንም እንኳን የዓለም ክብረ ወሰንን የሰበሩ ቢሆንም፤ ለዚህ ዓለም አቀፍ እውቅናን ለመስጠት የሚመለከታቸው አካላት ምክንያት ሲደረድሩ ከርመዋል፡፡ እናም ተግባሩን የዓለም ሪከርድ አካል ለማድረግ በሚያስችል መልኩ በእነዚህ አካላት በተለዩ እና በጂኦስፓሻል (ጂ.አይ.ኤስ) መረጃ ክትትል በሚያደርጉበት አግባብ 150 ሚሊዮን ችግኞችን የመትከል ነው፡፡

ሌላኛውና ዋነኛው ግን ኢትዮጵያውያን የራሳቸውን ክብረ ወሰን የሚሰብሩበት የ600 ሚሊዮን ችግኞችን በአንድ ጀንበር የመትከል መርሃ ግብር ነው፡፡ ይሄን መርሃ ግብር አስመልክቶ የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)፣ "ነሐሴ 17፣ 2016 ዓ.ም በአንድ ጀንበር 600 ሚሊዮን ችግኞችን በመትከል አሻራችንን እናኑር፤" ሲሉ ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በመልዕክታቸው፤ በአንድ መንፈስ በመላው ኢትዮጵያ አሻራችንን እናኑር፡፡ አንድ ከሆንን ከዚህም በላይ እንችላለን፡፡ ይህ እንዲሆንም፤ አዋቂዎች ከ20 በላይ፣ ታዳጊዎች ከ10 በላይ በመትከል ለሀገር ያለንን ፍቅር፣ ለትውልድ ያለንን ስጦታ በተገቢው ስፍራ እንግለጥ በማለት ለኢትዮጵያውያን አሳስበዋል፡፡ በመሆኑም ለዚህ ከፍ ላለው ራዕይ መሳካት ሲባል ለቀረበው ታሪካዊ ጥሪ ተግባራዊ ምላሽ መስጠት እና ዳግም ታሪክ ለመጻፍ መዘጋጀት ከሁሉም ኢትዮጵያዊ የሚጠበቅ ነው!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ከፓርቲ በላይ የሕዝብ አንድነት፣ሰላምና ህልውናን ማስጠበቅ ይገባል

ታምራት ተስፋዬ

የታሪክ ተመራማሪና የፍልስፍና አዋቂው ፕሮፌሰር ዩቫል ኖህ ሐረሪ ዓለማችን ካፈራቻቸው ድንቅ ሥራዎችን ካበረከቱ ምሁራን መካከል በበርካቶች ዘንድ በግንባር ቀደምትነት ስማቸው ይጠቀሳል፡፡ እስራኤላዊው ፕሮፌሰር በተለይም Sapiens /ሳፒየንስ/ እና 21 Lessons for the 21st Century በሚል ባሳተሟቸው መጽሐፍ ይበልጡን ይታወቃሉ፡፡ ፕሮፌሰሩ ሁለተኛ ላይ በተጠቀሰው ሥራቸው በ21ኛው ክፍለ ዘመን የሰው ልጅ ሊማርባቸው ይገባል ብለው ከዘረዘሯቸው 21 ነገሮች ውስጥ ጦርነት አብላጫውን ቦታ ይወስዳል፡፡

ፕሮፌሰሩ እኤአ በ2018 ባሳተሙት በዚህ መጽሐፍ የጦርነትን አስከፊነት በጥልቀት ከመተንተን ባሻገር የሰው ልጅ በታሪኩ ካሳለፋቸው ጦርነቶች ሊማር ግድ ስለመሆኑና በጦርነት ኪሳራ እንጂ ትርፍ እንደሌለ መለስ ብሎ መቃኘት እንደሚገባ አጽንኦት ይሰጡታል፡፡

እንደ እርሳቸው ሁሉ የጦርነትን አስከፊነት በሚመለከት በርካቶች ጽፈዋል፡፡ ስለ ሰላም ብዙዎች ዘምረዋል፡፡ አዚመዋል። አያሌዎች ሕይወታቸውን ሰውተዋል፡፡ ሰላምን ሁሉም በተግባር ይፈልገዋል፡፡ ይፈቅደዋል፡፡የተለየ ዋጋ ይሰጠዋል፡፡ በሁሉም ባህሎችና እምነቶች እንዲሁም ሕዝቦች ዘንድ ሰላም ከፍተኛ ዋጋ አለው፡፡

ሰላምን የማያስተምር እምነት የለም፡፡ በየቤተ እምነቱ በሚደረጉ ፀሎቶችም ሰላም ከቀዳሚ ርዕሶች የመጀመሪያው ነው፡፡ ሕዝብ እንደ የእምነቱ ፈጣሪን እለት እለት በሰላም ያሳደርከኝ በሰላም አውለኝ ከማለት አልፎ፤ ለሀገሩ፣ለሕዝቡ ሰላም መሆን ይመኛል፡፡ ይፀልያል፡፡

በተለይ በፖለቲካው ዓለም ፉክክርና የትግል ተሳትፎ ሁለናተናዊ ሰላም እውን ይሆን ዘንድ ከሀገርና ከሕዝብ በፊት ሥልጣንን ማስቀደም፣ ከራስ ክብርና ዝና በላይ ለሌላው አለመጨነቅና ዕብሪት አሸቀንጥሮ ማስወገድ የግድ ይላል፡፡ ልዩነትን ማቀራረብ ወይም ቅራኔን ማርገብ የሚቻለው በክብ ጠረጴዛ ዙሪያ እንጂ፣‹‹የምፈልገውን አስፈጽማለሁ›› በሚል ጀብደኝነት አይደለም፡፡

ሰላምን በጉልበት የማምጣት ሙከራዎችም በአብዛኛው ትርፋቸው መከራ ነው፡፡ በጉልበትና በጠመንጃ የሚጠበቅ ሰላም ቀን ጠብቆ ፍርክርኩ መውጣቱ አይቀሬ ነው፡፡አንዳንድ ፀሐፍት እንዳውም በጉልበት የተገኘ ድል ከሽንፈት እኩል ያነፃፅሩታል፡፡ ምክንያታችን የሚሉት ደግሞ ጊዜያዊ መፍትሄ መሆኑን ነው፡፡

ኢትዮጵያ ታሪክ በቀደሙት ዓመታት አንድ ችግር ሲያጋጥምና ሰላም ሲደፈርስ ተነጋግሮ መፍትሔ ለማፍለቅ ከመትጋት ይልቅ ዱላ መምዘዝ የተለመደ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ግጭትን ወይም ጦርነትን ሙጥኝ በማለት ዓላማን ለማስፈጸም ጥድፊያው ሲበረታም ይታያል፡፡ ይህን ተከትሎም በየጊዜው የሰላም አየር ይደፈርሳል፡፡

የሩቁን ትተን የቅርቡን እንኳን ብናስታውስ ሀገሪቱ የሰሜኑ ጦርነት ባስከተለው ሁለንተናዊ ቀውስ ከባድ መንገራገጮችን ወይንም shocks ውስጥ ቆይታለች፡፡ በጦርነቱ ምክንያት በርካቶች ሞተዋል፡፡ ከአካላዊና ከሥነ ልቦናዊ ጉዳት በተጨማሪ ከሞቀ ጎጃቸው ተፈናቅለዋል፡፡ ግምቱ እጅግ በጣም ከፍተኛ የሆነ የሕዝብና የሀገር ሀብት ወድሟል፡፡

ይህ ቀውስ እልባት ያገኝ ዘንድ የኢትዮጵያ መንግሥት የሰላም ንግግር ሃሳብን በዋናነት ሲደግፉና እንዲጀመር ከፍተኛ ግፊት ሲያደርጉ መቆየቱም የሚታወስ ሲሆን፤ ከብዙ ጥረት በኋላም በአፍሪካ ኅብረት ጥላ ሥር በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ ከተማ በፌዴራል መንግሥትና በሕወሓት መካከል የሰላም ንግግር እውን ሆኗል፡፡ የኢትዮጵያን ጥቅምና ክብር ባስጠበቀ መልኩ ሰላምን እውን ለማድረግ ከስምምነት ተደርሷል፡፡

ከውጭ ሀገራት አሸማጋዮች ይልቅ‹‹እኛው ለእኛው››በሚል መርህ መከወኑ ደግሞ በተለይ የአፍሪካ ሀገሮች ከምእራባውያን ይልቅ በራሳቸው አቅም ያለማንም ጣልቃ ገብነት ከቅኝ ግዛት እሳቤ ተላቀው የራሳቸውን ችግር በራሳቸው መፍታት እንደሚችሉ ተጨባጭ ምሳሌ የመሆን ትርጉሙን ያልቀዋል፡፡

ይህም የሰላም መንገድ ለኢትዮጵያ ትልቅ ድል ነው። በሰላም እንጂ በጦርነት ያተረፈ ሀገር አለመኖሩን በመረዳት ግጭትና ጦርነት ይብቃን መባሉ እጅግ የሚደገፍና የሚያስደስት ነው። ከምንም በላይ ለሕዝባችን ትልቅ እፎይታ ነው፡፡የሰላም አየር መተንፈስ መጀመሩ በተለይ ኢትዮጵያ የታሪካዊ ጠላቶቿ መቀለጃና መፈንጫ እንዳትሆን ያደርጋል፡፡

በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ እጃቸውን አስረዝመው የሚያስገቡ የውጭ ኃይሎች ፍላጎት እንዳይሳካ ግዙፍ ሚና ይጫወታል፡፡ ይህን ከግምት ከማስገባት በጦርነቱም ወቅት የታለፉ የጨለማ መንገዶችን ማስታወስ በቂ ነው፡፡

በሰለጠነ መንገድ በሰላም መንገድ ማራመድም ትሩፋቱ በርካታ ነው፡፡ በተለይ ኢትዮጵያ የታሪካዊ ጠላቶቿ መቀለጃና መፈንጫ እንዳትሆን ያደርጋል፡፡ በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ እጃቸውን አስረዝመው እያስገቡ ያሉ የውጭ ኃይሎች ፍላጎት እንዳይሳካ ግዙፍ ሚና ይጫወታል፡፡

የሰላም አየር መተንፈስ መጀመሩም ለኢትዮጵያ በተለይም ዘርፈ ብዙ ስቃይ ውስጥ ላሳለፈው የትግራይ ሕዝብ ዋጋው በምንም የማይገመት ነው፡፡ ከስምምነቱ በኋላም የክልሉ ሕዝብ በአንጻራሪ ሰላም ውስጥ እጁን ለልማት በመሰብሰብ እንቅስቃሴ ሲያደርግም ቆይታል፡፡ ይሁንና ይህ እንቅስቃሴው ምቾት ያልሰጣቸው አንዳንድ አካላት ዳግም ሰላሙን እንዲነጠቅ ከፍ ሲል ለጦርነት እጁን እንዲሰበስብ ሲገፋፉት ታዝበናል፡፡

እንደሚታወቀው፤ ሕወሓት በፕሪቶሪያው ስምምነት የፌዴራል ተቋማትን አሠራሮት፣ ሕጎችና አካሄዶች በጥብቅ ሊያከብር ግዴታ ጥሎበታል። ይህን ለማድረግ ተስማምቶም ፊርማውን አስቀምጧል፡፡ይሁንና የድርጅቱ አንዳንድ አመራሮች በተለያዩ አጋጣሚዎች ላይ ቀደም ሲል የተገባውን ግዴታ ሲሸራርፉ ታይተዋል፡፡ ከሰሞኑ ደግሞ በግልጽ ስምምነቱን ለማፍረስ የሚመስል እንቅስቃሴ እያስመለከቱ ናቸው፡፡

ከሕዝብ በላይ የድርጅቱን ህልውና ማስቀጠልን ታሳቢ ያደረጉ አንዳንድ የድርጅቱ አመራሮችና አሻ ጃግሬዎቻቸውም የሰላም አየር ለመበረዝ ከግራና ከቀኝ እጅ ጥምዘዛና ጉተታ የተያያዙት መስለዋል፡፡ የሰላም አምባሳደር ሚናን ከመወጣት ይልቅ ጥቅማቸውን እያሰቡ መራመድን ብቻ ምርጫ ሲያደርጉም እየተመለከትን እንገኛለን፡፡

በተለይ ከሰሞኑ የሚስተዋለው የፓርቲው አመራሮች የእርስ በእርስ ሽኩቻ እንዲሁም በሕወሓት እና ጊዜያዊ መንግሥቱ መካከል ያለ እሰጣ ገባ ከአንድ ፓርቲ የውስጥ ጉዳይነት አልፎ በክልሉ እና አጎራባች ክልሎች ውስጥ በሚገኙ ንፁሐን ዜጎች ላይ ከባድ አደጋን ይዞ ሊመጣ የሚችል ነው፡፡

መሰል ሕግና ሥርዓትን አክብሮ የማይንቀሳቀስ የትኛውም አይነት የፖለቲካ እንቅስቃሴ የመጨረሻ ግቡ ጥፋት ነው። የፌዴራል መንግሥት እንዳስታወቀውም፤የሕወሓት ድርጊት የትግራይ ሕዝብ ያገኘውን አንጻራዊ ሰላም እንደመንጠቅ የሚቆጠር ነው፡፡

ኢትዮጵያ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች እድገት ለማስመዝገብ መጀመሪያ ሊኖራት የሚገባው ሀብት ሰላም ነው። ሰላም በመገኘቱ የሚከስር ሕዝብም ሆነ የሕዝብ አጀንዳ የለም፡፡ ይሁንና ከሰላም ይልቅ ጦርነት ምርጫቸውና የደስታቸው ምንጭ የሆነ አንዳንዶች መኖራቸው የሚደበቅ አይደለም፡፡ የሰላምን መንገድ ስንራመድ ሰላም እውን እንዳይሆን የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች የተዳፈነውን እሳት እሳቱን ለማራገብ አድፍጠው እንደሚተጉም ለአፍታ መዘንጋት የለበትም፡፡

አንዳንድ የፓርቲው ሰዎችም እንደ ሀገር የተደረሰውን የሰላም ስምምነት ዘላቂ ይሆን ዘንድ ከመሰል እሰጣ ገባ በመራቅ ስለ ሰላም ኃያልነት መንገር ቋሚ መልዕክታቸው ሊሆን ይገባል፡፡ ከፓርቲ በላይ የሕዝብ አንድነት ሰላምና ህልውናን ማስጠበቅ ግድ ይላቸዋል፡፡

በዚህ ሂደት በአንድ አፍ ስለሰላም እየዘመሩ በሌላ አፍ ጦርነትን የሚደግፉ የፖለቲካ ተዋንያንም ሆኑ አክቲቪስቶች፣ የሰላም መንገዱ እንዲዘጋና ጦርነቱ እንዲያገረሽ ከሚያደርጉ ፕሮፓጋንዳዎች እንዲታቀቡ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር ሕዝቡን ላልተፈለገ መስዋዕትነት ለመዳረግ የሚፍጨረጨሩ አካላትን አደብ ማስገዛትና በሕግና በሥርዓት ተጠያቂ ማድረግ የግድ ይላል፡፡

እድገት እንጂ ዝቅታዋን፣ ደስታዋን እንጂ ሃዘኗን፣ ክብሯን እንጂ ውርደቷን ፈፅሞ የማይመኙ የኢትዮጵያ ልጆችም ፣ሀገራቸው ከግጭት የፀዳች ሀገር እንድትሆን ያላቸውን ቁርጠኝነታቸውን በቀጣይም አጠናክረው በተግባር ማሳየት ይጠበቅባቸዋል፡፡

መላው የትግራይ ሕዝብም ከፓርቲ በላይ አንድነት፣ሰላምና ህልውናውን ማስጠበቅ በተለይም በሴረኞች መረብ ላለመጠለፍ መጠንቀቅ ይኖርበታል፡፡ በሰላም መንገድ እጅ ለእጅ ተያይዞ በመራመድ፣የኢትዮጵያን ዝቅታ ለሚመኙ ከፍታዋን ማሳየትና ወዟን የሚነጥቁ ውበቷንም የሚሰርቁ ቀማኞችን ሁለንተናዊ ፍላጎት ጠንቅቆ መረዳት ይኖርበታል፡፡

ዜና

# ውጤታማ ሲቪል ሰርቪስ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ከዚያ በታች በየደረጃው ባሉት መዋቅሮች የሚመራ ነው። ከወታደራዊ ክፍል ውጪ ያለውን ጠቅልለን ሲቪል ሰርቪስ ብለን እንገልጻዋለን ነው ያሉት።

ሲቪል ሰርቪስ ለአንድ ሀገር ትልቅ ዋልታ ነው። በዋናነት ደግሞ በሙያተኞች የሚያዝ ቦታ ነው። በዚህም የወጣን ሕግ ያስፈጽማል፤ ይፈጽማል። የሕግ ምንጭም ይሆናል ያሉት እንዳለ (ዶ/ር)፤ የመንግሥት ተቋማቱ በአዋጅ የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት በአግባቡ እየተወጡ ነው ወይ የሚለውን ጥያቄ ማንሳት ተገቢ መሆኑን አንስተዋል።

ሌላው ተቋማቱ በሚሰጡት አገልግሎት ኅብረተሰቡ ደስተኛ ነው አይደለም የሚለውንም ማወቅ ያስፈልጋል ያሉት እንዳለ (ዶ/ር)፤ ከዚህ አንፃር የኅብረተሰቡን እርካታ መሰረት ያደረገ ጥናት ባለመኖሩ ድምዳሜ ላይ መድረስ እንደማይቻል ይናገራሉ።

ይህም የመንግሥት ተቋማት በሚሰጡት አገልግሎት እና ኅብረተሰቡ በሚፈልገው አገልግሎት መካከል ከፍተኛ ክፍተት መኖሩን ያሳያል የሚሉት ምሁሩ፤ የመንግሥት ተቋማት መሰረታዊ ችግሮች ሲታይ የመጀመሪያው መዋቅራዊ ችግር ነው ያሉት።

መዋቅራዊ ችግር ስንል ተቋማቱ የተደራጁት ውጤትን መሰረት ከማድረግ ይልቅ ሂደት ተኮር መሆናቸውን ይገልጻል::ለአብነት አንድ ዜጋ ንግድ ፈቃድ ለማውጣት ወደ ተቋማቱ ቢሄድ በተለያዩ የአሰራር ሂደቶች ጊዜው ይባክናል። ይህም ተቋማቱ የተደራጁት በሂደት ተኮር ሥርዓት ላይ መሆኑን ያሳያል ነው ያሉት እንዳለ (ዶ/ር)።

እንደ እንዳለ (ዶ/ር) ገለፃ፤ ሌላው በተቋማቱ የሚስተዋለው የውስጣዊ አደረጃጀት ችግር የስልጣን እርከንን መሰረት ያደረጉ መሆናቸው የተንዛዙና አድካሚ ሁኔታዎችን ይፈጥራሉ። ለአብነት አንድ ግለሰብ የሚፈልገውን ጉዳይ ለማስፈጸም የግድ ኃላፊን ማግኘት የሚጠይቁ ሁኔታዎች አሉ።

በዚህም ግለሰቡ ሁለትና ሦስት ኃላፊዎችን ሳያገኝ ጉዳዩን ሳያስፈጽም ሊቀር ይችላል። ይህም ተቋማቱ መሰረታዊ የውስጣዊ አደረጃጀት ችግር እንዳለባቸው ያሳያል ያሉት እንዳለ (ዶ/ር)፤ ተቋማቱ ሰብሰብ ያሉ ባለመሆናቸው በአንድ ተቋም መጠናቀቅ የሚችሉ ተግባራት ለሁለትና ለሦስት ተቋማት መሰጠታቸው ሌላኛው ችግር መሆኑን ጠቅሰዋል።

ለአብነት የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን፣ የሕዝብ እምባ ጠባቂ ተቋም እና ስነ ምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን ጠቅሰው፤እነዚህን ሦስት የተለያዩ ተቋማት ከማድረግ ይልቅ በአንድ ሚኒስትር እና በሦስት ሚኒስትር ዴኤታዎች በማዋቀር አንድ ጠንካራ ተቋም መፍጠር ይቻላል ነው ያሉት።

ይህም የሚደጋገሙ እና የተበታተኑ ሥራዎችን በአንድ ቦታ ለመሰብሰብ እንደሚያስችል ገልጸው፤ የሲቪል ሰርቫንቱ ክፍያ ዝቅተኛ መሆን እና የመንግሥት ሰራተኛው ጋር ያለው የስነ ልቦና ችግር የሲቪል ሰርቪሱ ሌላኛው መሰረታዊ ችግር መሆኑን ጠቁመዋል።

የሌሎች ሀገራት ተሞክሮን ብንመለከት ሲቪል ሰርቫንቱ የሚቀጠረው ኅብረተሰብን ለማገልገል አስቦ ነው። ይህንን ከኢትዮጵያ የመንግሥት ሠራተኞች አንፃር ስንመለከተው ስሜቱ አንድ አለመሆኑን ያስረዳሉ።

ሲቪል ሰርቪሱ ሚናውን በአግባቡ እንዲወጣ እና እንዲጠናከር ወይም ኅብረተሰቡ በሚፈልገው ልክ ውጤት ማምጣት እንዲቻል በምን መልኩ መደራጀት ያለበት የሚለው ጉዳይ ላይ ትኩረት ማድረግ ይገባል ያሉት እንዳለ (ዶ/ር)፤ ሕዝብን ማገልገል አለብኝ የሚል አስተሳሰብ፣ አመለካከትና ስነልቦና የተላበሰ የመንግሥት ሠራተኛ መፍጠር እንደሚገባ ያብራራሉ።

ሌላው ነፃና ገለልተኛ ሲቪል ሰርቪስ ተቋም ለመፈጠር ከመንግሥት አካላት ተጽዕኖ በተለይ ከፖለቲካ ተጽዕኖ ነፃና ገለልተኛ መሆን አለበት ነው ያሉት።

ምክንያቱም ፖለቲከኛው ፖሊሲ የማውጣት ተልዕኮና ኃላፊነት ነው ያለበት። ሲቪል ሰርቫንቱ ደግሞ ፖለቲከኛው ያወጣውን ፖሊሲ የማስፈጸም ግዴታ አለበት። ይህም ማለት ሲቪል ሰርቫንቱ ስልጣን ላይ ያለው ፖለቲከኛ ያወጣው ፖሊሲ ከእኔ አመለካከት ጋር አይሄድም ማለት አይችልም። የሚል ከሆነ ደግሞ የመንግሥት ተቋሙን ለቆ መሄድ አለበት ይላሉ።

በሌላ በኩል ደግሞ አንድ ኃላፊ በአንድ ተቋም ሲሾም ፊት የነበረውን አደረጃጀት ያፈርስ እና አዲስ እሱ በሚመስለው መልክና አስተሳሰብ ልቅረጽ ይላል ያሉት እንዳለ (ዶ/ር)፤ እንደዚህ አይነት ችግሮች መቀረፍ እንዳለባቸው ተናግረዋል።

በአጠቃላይ ተቋማቱን ውጤት ተኮር አድርጎ ማደራጀት፣ ነፃና ገለልተኛ ሲቪል ሰርቪስ ተቋም ማድረግ፣ በዋና አላማቸው የሚመሳሰሉትን በአንድ ማደራጀት፣ የረጅም ዓመት ግብን መሰረት ያደረጉ እና ቴክኖሎጂ የሚጠቀሙ ተቋማት እንዲኖሩ ማድረግ እንደሚገባ ያብራራሉ።

ከዚህም ባለፈ በግል ዘርፉ መሰራት የሚችሉ አገልግሎቶችን ለግል ዘርፉ በማስተላለፍ፣ የሠራተኛ ቅጥርን ሙያ ተኮር በማድረግ እና ሌሎች የሚታዩ ክፍተቶችን በመሙላት ውጤታማ የመንግሥት አገልግሎቶች እንዲኖር ማድረግ እንደሚቻል ያመለክታሉ።

አሁን ላይ ሆኖ የወደፊት የመንግሥት አገልግሎት (ሲቪል ሰርቪስ) እጣ ፈንታን መገመት አይቻልም። የዚህ ምክንያቱ ሲቪል ሰርቪስ የሚወስነው በመንግሥት ፖሊሲ እና ርዕዮተ ዓለም እንደሆነ ገልጸዋል። ነገር ግን ከላይ የተጠቀሱት የመፍትሔ አማራጮች በአግባቡ የሚተገበሩ ከሆነ ውጤታማ ሲቪል ሰርቪስ መገንባት ይቻላል ነው ያሉት።

የፐብሊክ ፖሊሲ ተመራማሪ ሄኖክ ስዩም (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ሲቪል ሰርቪስ የሚታየው የመንግሥት ክፍል ይባላል። የመንግሥት ፖሊሲዎችና የልማት እቅዶች እንዲሁም መንግሥት ለዜጎች ቃል የገባቸውን ነገሮች ወደ ተግባር የሚቀየሩት በሲቪል ሰርቪሱ ነው ይላሉ።

ይህንን ማድረግ የሚችል መንግሥት ጠንካራ ነው ይባላል። በተቀራኒው ሲሆን ደግሞ ደካማ ይባላል ነው ያሉት ሄኖክ (ዶ/ር)፤ ሲቪል ሰርቪስ ማለት የመንግሥትን አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት፣ ግለሰቦች፣ አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው መመሪያዎች፣ አሰራሮችና ህጎች ማለት ነው ያሉት።

ዜጎች መንግሥት ሲሉ አብዛኛውን ጊዜ የሚያነሱት በየአካባቢያቸው ያለውን የወረዳና የቀበሌ አገልግሎት አሰጣጥን መሆኑን ተናግረው፤ አሁን ላይ ዜጎች ወይም ተገልጋዮች እርካታ እንዲያገኙ የሚያስችል ሕግና አሰራር ከሞላ ጎደል አለ። ሕጎቹንና አሰራሮቹ የወጡበትን ዓላማ አሳክተዋል ለማለት አስቸጋሪ መሆኑን ነው የተናገሩት።

እሳቸው ባጠኑት ጥናት በፌዴራል መንግሥቱ ካሉ ሰራተኞች ውስጥ 79 በመቶ የሚሆኑት ድጋፍ ሰጪ ናቸው። ይህም ማለት 21 በመቶ የሚሆኑት ዓላማ ፈፃሚ ናቸው ማለት ነው። ከ21 በመቶ ደግሞ በብቃት ሥራውን የሚወጣው ምን ያህሉ ነው ሲባል ቁጥሩ ትንሽ ይሆናል ነው ያሉት።

የሰው ኃይል ብቃት ማነስ፣ የሪፎርም ሥራዎች በአግባቡ ተግባራዊ ያለማድረግ እና ውስብስብና የኢትዮጵያን አውድ መሰረት ያደረጉ አለመሆናቸው፣ ሲቪል ሰርቪሱ ከሚከፍለው ክፍያ አንፃር የተሻለ ሙያ ያለውን ሰው የመሳብ እድሉ አናሳ መሆን እና የሰራተኞች የሥራ እድገት ዝቅተኛ መሆኑ በሲቭል ሰርቪሱ የሚስተዋሉ ክፍተቶች መሆናቸውን ገልጸዋል።

መንግሥት በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ሰነድ አዘጋጅቷል ያሉት ሄኖክ (ዶ/ር)፤ ማሻሻያ ሰነዱ የሰው ኃይል የመመልመያ ሥርዓት አበጅቷል። ሌላው ውጤትን መሰረት ያደረገ የክፍያ ሥርዓት እና ሌሎች የአሰራር ሥርዓቶች ማቀፉን ነው የጠቆሙት። ጅምሮቹ ተጠናክረው ከቀጠሉ ወደፊት ውጤታማ የሲቪል ሰርቪስ መገንባት እንችላለን የሚል ተስፋ አለኝ ነው ያሉት።

# የባንኮች...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሀብት ረዳት ፕሮፌሰር ዳዊት ሀይሶ (ዶ/ር) እንደሚገልጹት፤ ኢትዮጵያ የባንክ ዘርፉን ለዓለም አቀፍ ገበያው ክፍት ማድረጓን ተከትሎ ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ባንኮች ከፍተኛ ካፒታል ይዘው የሚመጡ በመሆኑ ሀገር ውስጥ ያሉ ባንኮች ተዋህደው ኢኮኖሚያቸውን ማጠናከር ካልቻሉ ገበያውን የመቋቋም አቅማቸው አነስተኛ ነው::

አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ብዛት ያላቸው ባንኮች መደበኛ ወጪያቸውንም መሸፈን እያቃታቸው አለፍ ሲልም ብሔራዊ ባንክ ልዩ ድጋፍ እያደረገላቸው እየቀጠሉ መሆኑን የሚያነሱት ረዳት ፕሮፌሰሩ፤ በኢትዮጵያ የሚገኙ አብዛኞቹ ባንኮች በመነሻ ካፒታል ብቻ ተቋቁመው በዛው የቀጠሉ መሆናቸውን በማንሳት ከሰው ኃይል፣ ከቴክኖሎጂና ከካፒታል አንጻር አቅማቸው እምብዛም መሆኑን ይናገራሉ::

እንደ ዳዊት (ዶ/ር) ገለጻ፤ የውህደት ጉዳይ በተለይ በዚህ ወቅት አስፈላጊ በመሆኑ በሌሎች ሀገሮችም ተወዳዳሪ የነበሩ ኩባንያዎች ወደ ውህደት እየገቡ ትልቅ አቅም እየፈጠሩ ነው:: ደቡብ አፍሪካ፣ ናይጄሪያ፣ ካናዳ፣ እንግሊዝና ህንድ ብዙ የነበሩትን ባንኮች በውህደት ቀንሰው ጠንካራ ባንኮች ፈጥረዋል::

ከዚህ ቀደም 40 ዓመታትን ያስቆጠረው የቢዝነስና ኮንስትራክሽን ባንክ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጋር በመዋሀድ በቅርንጫፍ፣ በካፒታል፣ በሰው ኃይልና በቴክኖሎጂ ትልቅ አቅም መፍጠር መቻሉን የሚያስታውሱት ዳዊት (ዶ/ር)፤ ባንኮቹ ሊዋሃዱ የሚችሉበት ማእቀፍ መዘጋጀት አለበት ነው የሚሉት።

በሀገራችን ያሉ የፋይናንስ ተቋማት ለውህደት አመቺዎች አይደሉም፤ ቢዝነሶች በሃይማኖት፣ በብሔረሰብና በፖለቲካ ግንኙነቶች ላይ ተመስርተው የመፈጠራቸው ጉዳይ ውህደትን ለማከናወን አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል:: ነገር ግን ቢዝነሶች መቋቋም ያለባቸው የኢኮኖሚን መሠረት በመያዝ ነው ሲሉም ያክላሉ::

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሀብት መምህሩ አጥላው አለሙ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ የባንኮች ውህደት ሊፈጠር የሚችለው ባንኮች ችግር ውስጥ ሲወድቁ ነው:: እንዲሁም የተሻለ አቅም ለመፍጠር ሲባል ተቀራራቢ አቅም ያላቸውም ቢሆኑ የሚዋሀዱበትን ሁኔታ መፍጠር እንደሚቻል በማንሳት፤ ባንኮች ይህንን ዕድል በመጠቀም ጠንካራ ኢኮኖሚ መገንባት እንደሚችሉ ይጠቁማሉ::

የውጭ ሀገራት ባንኮች ወደ ኢትዮጵያ ገንዘባቸውን ፈሰስ በሚያደርጉበት ወቅት በሀገር ውስጥ የሚገኙ ባንኮች የመወዳደር አቅማቸው አነስተኛ ነው:: እነኚህ ባንኮች ፈተና ውስጥ የሚገቡ በመሆኑ ውህደት በገበያው ላይ ለመቀጠል ምቹ ሁኔታን ይፈጥርላቸዋል ነው የሚሉት::

በገበያው ላይ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመቀጠል የሀገር ውስጥ ባንኮች ያላቸውን ካፒታል፣ የሰው ኃይል፣ ቴክኖሎጂና ሌሎችንም ሀብቶቻቸውን በማሰባሰብ መጠቀም የሚችሉባቸው ሁኔታዎች የሚፈጠሩ ከሆነ ከውጭ ከሚመጡ ባንኮች ጋር ተወዳዳሪ በመሆን ነገን የመቀጠል ዋስትናቸው በጽኑ መሰረት ላይ ሊረጋገጥ እንደሚችል መምህር አጥላው ያመላክታሉ::

እንደ አጥላው (ዶ/ር) ገለጻ፤ የሀገር ውስጥ ባንኮች ያላቸው ካፒታል እጅጉን አነስተኛ ነው:: ከዚህ በኋላ ወደ ሥራ የሚገቡ ኢንቨስተሮች ከፍተኛ ካፒታል የሚያስፈልጋቸው በመሆኑ የሀገር ውስጥ ባንኮች ከውጭ ከሚመጡ ባንኮች ጋር ተወዳዳሪ ለመሆን በቂ ገንዘብ በመሰብሰብ፣ ተቀማጭ ካፒታላቸውን ማሳደግና በቂ የብድር አገልግሎትም ማቅረብ መቻል ይጠበቅባቸዋል::

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሰኔ 7 ቀን 2016 ዓ.ም ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ያቀረበው የባንክ ሥራ አዋጅ በርካታ አዳዲስ ድንጋጌዎችን የያዘ ሲሆን፤ ባንኮች ሊዋሃዱ የሚችሉበትን መንገድ የሚዘረዝረው የአዋጁ ክፍል ይገኝበታል። በውስጡ ባንኮች ውህደት ስለሚያከናውኑበት፣ ግዥ፣ እና ወሳኝ የባለቤትነት ድርሻ እንዲሁም የባንኮች ሀብት እና ዕዳ ስለሚተላለፍበት አግባብ የተመለከቱ ጉዳዮችን አካቷል::

ችግር ያለበትን ባንክ ለመታደግ ወይም የበለጠ አዋጭና ጠንካራ ባንክ ለመፍጠር በብሔራዊ ባንክ በሕግ የተደነገገ ውህደት ሊፈቅድ እንደሚችል እንዲሁም የፋይናንስ ሥርዓት መረጋጋትን ለማረጋገጥ አንድ የሀገር ውስጥ ባንክ በተለየ ሁኔታ በውጭ ባንክ ወይም በሌላ የሀገር ውስጥ ባንክ እንዲገዛ የሚፈቀድበት ዕድል እንዳለም ተጠቅሷል::

በብሔራዊ ባንክ ውሳኔ የሚፈጸም የባንክ ውህደትም ሆነ ግዥ (Merging and Acquisition) የባንኩን ጤናማነት፣ የፋይናንስ ሥርዓት መረጋጋትን፣ የፋይናንስ አገልግሎትና የሸማቾች መብትና ፍላጎትን፣ የፋይናንስ አቅርቦት፣ በባንክ ሥርዓት ውስጥ ውድድርና ቅልጥፍናን መሠረት በማድረግ እንዲሁም የአክሲዮን ድርሻ ገደብና አግባብነት ያለው የብሔራዊ ባንክ መመሪያን በማክበር እንደሚሆንም ይገልጻል::

የረቂቅ አዋጁን አስፈላጊነት የሚገልጸው ማብራሪያ፤ በአሁኑ ወቅት በኢንዱስትሪ ውስጥ ያሉ ባንኮች ወደ ውህደት መግባት ይኖርባቸዋል የሚለውን ጠንከር ያለ አመለካከት ወደ ተግባር ለመቀየር ጠቃሚ ነው:: በተጨማሪም ረቂቅ አዋጁ ከውጭ ባንኮች ጋር ሊኖር ስለሚገባው ጥምረትና ውህደት ታሳቢ ያደረገ ነው ይላል::

# ለሌማት ታስቦ ለገበያ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ዘመናዊ፣ 165 ሽግግር እና 135 ባህላዊ የንብ ቀፎዎችን ይዘው መንግሥት በሰጣቸው ቦታ ላይ እየሠሩ መሆኑን ይናገራሉ፡፡

የንብ ማነብ ሥራ አንድ ጊዜ ኢንቨስት ከተደረገ ቀሪው ክትትል የማድረግ ሥራ ነው፡፡ በአግባቡ ክትትል ከተደረገ በዓመት በአማካኝ ሦስት ጊዜ የማር ምርት ይገኛል፡፡ ንብ ማነብ በጣም አዋጭና ቀላል ሥራ ነው ሲሉም ወይዘሮ ጽላተማርያም ይገልጻሉ፡፡

ከ600 በላይ የንብ ቀፎዎች እንዳሏቸው የሚናገሩት ወይዘሮ ጽላተማርያም፤ ከአንዱ ቀፎ በአማካኝ 20 ኪሎ ግራም ማር ያገኛሉ፡፡ ከሁሉም ቀፎዎች ከ11 ኩንታል በላይ የማር ምርት ነው የሚያገኙት፡፡

ለማር ተጠቃሚዎች እንደፍላጎታቸው ከግማሽ ኪሎ ጀምሮ የተጣራ ማር ከማቅረብ ባለፈም ሰም ሰርተው እንደሚያቀርቡ የሚገልጹት ወይዘሮዋ፤ በተጨማሪም በንብ ማነብ ሥራ ለተሰማሩ ወጣቶች ሙያዊ እገዛ ያደርጋሉ፡፡ በቀጣይ ንጹህ ማር በማምረትና በማቀነባበር ወደ ውጭ መላክ እቅዳቸው መሆኑን ይጠቁማሉ፡፡

የዶሮ እርባታውም በቤት ውስጥ ለልጆች ተብሎ ተጀምሮ አሁን ላይ 37 ሺህ ዶሮ ደርሰዋል፡፡ እንቁላልና የዶሮ ስጋን በማከፋፈል ገበያውን ለማረጋጋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማበርከታቸውን እንዲሁም የ45 ቀን ጫጩት፣ የሦስት ወር እንቁላል ጣይ ዶሮዎችንና መኖ እንደሚያከፋፍሉ ነው የገለጹት፡፡

ምርትና ምርታማነትን ከመጨመር ባለፈም በዶሮ እርባታ ለ57 በንብ ማነብ ደግሞ ለ33 ዜጎች የሥራ እድል ፈጥረዋል፡፡ ሥራውን ስጀምር ያጣጣሉት ሰዎች አሁን ለውጡን አይተው ተገርመዋል የሚሉት ወይዘሮ ጽላተማርያም፤ ወጣቶችና ሴቶች ሥራን ሳይንቁ ማንኛውንም ሥራ ቢሠሩ በአጭር ጊዜ መለወጥ እንችላለን ነው ያሉት፡፡

የደብረብርሃን ከተማ ነዋሪ የሆነው ወጣት ሰውነት ሸዋይርጋ በከብት እርባታ የተሰማራ ወጣት ነው፡፡ ሥራው አዋጭና በአጭር ጊዜ ትርፋማ መሆን የሚችልበት ስለሆነ በዘርፉ ለመሰማራት ምክንያት ሆኖኛል ይላል፡፡

ሰውነትና ጓደኞቹ ስድስት ሆነው በማህበር ተደራጅተው የከብት እርባታ ሥራውን መጀመራቸውን የሚገልጸው ወጣት ሰውነት፤ ሁለቱ በራሳቸው ምክንያት ማህበሩን ለቀው ወጥተዋል፡፡ አሁን ላይ አራት የማህበሩ አባላት የከብት ዕርባታ እየሰራን ነው ይላል፡፡

ወጣት ሰውነት እንደሚለው፤ በ12 ላሞች የጀመርነው ሥራ በአራት ዓመታት ውስጥ ከነጥጃዎቹ 38 ደርሰውልናል፡፡ ከእነዚህ ላሞችም በቀን ከ250 እስከ 300 ሊትር የወተት ምርት የምናገኝ ሲሆን፤ ይህም የከተማዋን የወተት ፍላጎት ለማሟላት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል ይላል፡፡

በሁለት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር መነሻ የጀመርነውን ስራ በአጭር ጊዜ 25 ሚሊዮን ብር የሚገመት ሀብት አፍርተናል ይላል፡፡ ወጣቶችም ከዚህ በመማር ሥራ ጠባቂ ከመሆን ሥራ ፈጣሪ መሆን ይችላሉ ሲል ይናገራል፡፡

ሌላኛው የጎንደር ከተማ ነዋሪ አቶ መላኩ ታደሰ ከአማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም 40 ሺህ ብር ወስዶ የዶሮ እርባታ ጀምሯል፡፡ ሥራውን ከመጀመሩ በፊት በመንግሥት ሥራ ይተዳደር እንደነበርም ያስታውሳል፡፡ ሥራውን ሲጀምር የ45 ቀን ጫጩቶችን በማሰራጫት ነበር፡፡ አሁን ላይ የእንቁላል ጣይ ዶሮዎችን፣ የስጋ ዶሮዎችን እና እንቁላል ለገበያ እያቀረበ ይገኛል፡፡

ዘርፉን በአጭር ጊዜ መለወጥና ለበርካታ ዜጎች የሥራ እድል መፍጠር የሚቻልበት ነው፡፡ ወጣት መላኩ በ40 ሺህ ብር መነሻ የጀመረው የዶሮ እርባታ በአምስት ዓመታት ውስጥ 12 ሚሊዮን ካፒታል መድረሱንም ይናገራል፡፡

በዶሮ እርባታው ቤተሰቡን ከማስተዳደር አልፎ ለስምንት ሰዎች የሥራ እድል መፍጠሩን እና የእንቁላል ገበያውን ማረጋጋት እንደቻለም ያስረዳል፡፡

የመኖ አቅርቦትና የብድር አቅርቦት እጥረት መኖሩ እና የአካባቢው የጸጥታ ሁኔታ ለስራው እንቅፋት እንደሆነበት በመግለጽ፤ ችግሮቹ ቢፈቱ ከዚህ በበለጠ ውጤታማና ተጠቃሚ መሆን እንደሚቻል ይናገራል፡፡

በባህር ዳር ከተማ በተቀናጀ ግብርና የተሰማራው ወጣት አይሸሹም አለሙ በበኩሉ፤ ዓሳን ከአትክልትና ፍራፍሬ አቀናጅቼ በመሥራት ላይ እገኛለሁ ይላል፡፡ በቀጣይ ደግሞ የወተትና የላም እርባታን ለመጀመር ሼዶችን እየገነባ መሆኑን ያስረዳል፡፡

የዓሳ ውሃ ለአትክልትና ፍራፍሬ ምቹ በመሆኑ ግብርናውን አቀናጅቶ ለመሥራት እንዳነሳሳው በመግለጽ፤ በ600 ካሬ ላይ ያረፈ ሰው ሰራሽ ኩሬን በመገንባት የዓሳ እርባታ ሥራ መጀመሩን ይናገራል፡፡

አቩካዶ፣ ማንጎ፣ ፓፓዬ፣ቡና፣ ጌሾ፣ ሰላጣ፣ ጥቅል ጎመን፣ ቆስጣ፣ ቲማቲም ቃሪያ እና ሌሎች አትክልትና ፍራፍሬዎችን በማምረት ከቤተሰቡ አልፎ ለገበያ በስፋት እንደሚያቀርብ ያስረዳል፡፡

በቋሚነት ለአምስት ሰዎች የሥራ እድል መፍጠሩንና በጊዜዊነት ደግሞ በየቀኑ በአማካኝ ለአራት ሰዎች የሥራ እድል እንደፈጠረ በመግለጽ፤ በቀጣይ በቋሚነት የሥራ እድል የሚፈጥርላቸውን ሰዎች ወደ 25 ከፍ ለማድረግ ማቀዱን ይጠቁማል፡፡

በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ሃሳብ አመንጪነት የሌማት ትሩፋት መርሀ ግብር በመላ ሀገሪቱ ተግባራዊ መደረግ ከጀመረ ሰነባብቷል፡፡ የመርሀ ግብሩ ዓላማ የወተት፣ የዶሮ፣ የስጋ፣ የእንቁላል፣ የማር፣ የዓሳ እንዲሁም የአትክልትና ፍራፍሬ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ነው፡፡

በርካቶች ይህ መርሀ ግብር የሚያስገኘውን ዘርፈ ብዙ ተቀሜታ ተገንዝበው በመርሀ ግብሩ በመሳተፍ ሌማታቸውን ከራሳቸው አልፎ ለገበያ እያቀረቡ ነው፡፡ በዚህም ለወጣቶች የሥራ እድል ፈጥረዋል፤ ገበያንም ማረጋጋት ችለዋል፡፡ ከእነዚህ ተጠቃሚዎች መካከል ወይዘሮ ጽላተማርያም፣ ሰውነት፣መላኩና አይሸሹም ይገኙበታል፡፡ከእነዚህ ሥራ ፈጣሪዎች ትምህርት በመውሰድ ሥራ ከመጠበቅ ይልቅ ሥራን ፈጥሮ መሥራትንና ተጠቃሚ መሆን ይገባል፡፡

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# ከፍተኛ ትኩረት የሚሻው የወርቅ ኮንትሮባንድ

እንደ ኢትዮጵያ ባለ ሀገር ላይ ሕገ ወጥ ወይም በተለምዶ የኮንትሮባንድ ንግድ በርካታ አሉታዊ ተጽእኖዎችን ሊያስከትል ይችላል። ከነዚህም ውስጥ ቀዳሚው የኢኮኖሚ ውድመት ነው ፤ሕገ-ወጥ ንግድ ሕጋዊ የንግድ ድርጅቶችን በማዳከም የመንግሥትን ገቢ ይጎዳል። ታክስ እና ቀረጥ ይቀንሳል። እንዲሁም የገበያ ዋጋን ያዛባል። እንዲሁም ማህበራዊ ቀውሶችን ያስከትላል። ሥራ አጥነትን በማባባስ በዜጎች መካከል ከፍተኛ የሀብት ልዩነት ይፈጥራል። በተጨማሪም፣ የተደራጁ ወንጀሎች እና ሙስና እንዲስፋፉ አስተዋጽኦ በማድረግ መረጋጋት እንዳይኖር ያደርጋል።

የኮንትሮባንድ ንግድ በዜጎች ጤናና ደህንነት ላይ አደጋ ይደቅናል። በኮንትሮባንድ የሚገቡ መድሃኒቶች ወይም ደህንነታቸው ያልተረጋገጠ የፍጆታ ምርቶች በሕዝቡ ላይ ከፍተኛ የጤና ጠንቅ ሊያስከትሉ ይችላሉ። ኮንትሮባንድ የመንግሥት ተቋማትን በማዳከም ሕገ-ወጥ ንግድን ሙስናን እና ጉቦን በማስፋፋት የሕግ የበላይነትን ስለሚያዳክም የተደራጁ ወንጀለኞች እንዳሻቸው እንዲፈነጩ በማድረግ ሥርዓት አልበኝነትና አጠቃላይ ቀውስ ሊያስከትል ይችላል።

እንዲሁም አካባቢያዊ ጉዳት ያስከትላል። በዱር እንስሳት ወይም በተፈጥሮ ሀብት ላይ የሚደረግ ሕገ-ወጥ ንግድ የአካባቢ መራቆትን፣ ብዝሃ ሕይወትን መጥፋት እና ዘላቂ ያልሆነ የሀብት ብዝበዛን ያስከትላል። እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ጠንከር ያለ የሕግ ማስከበር፣ የተሻለ የድንበር ቁጥጥር እና ዓለም አቀፍ ትብብርን የሚያካትቱ አጠቃላይ ስልቶችን ይፈልጋል።

በሀገራችን እየተባባሰ የመጣው የጦር መሣሪያ፣ ወርቅን ጨምሮ የከበሩ ማዕድናት፣ የቁም እንስሳት፣ የመድሃኒት፣ የውጭ ምንዛሬ፣ የግንባታ ቁሳቁስ፣ የኤሌክትሮኒክስ፣ የልባሽ ጨርቅና የሌሎች ሸቀጣሸቀጥ የኮንትሮባንድ ንግድ በኢኮኖሚያችን ብቻ ሳይሆን በሀገራችን ህልውና ላይ አደጋ እየደቀነ ነው። በዚሁ የሚቀጥል ከሆነ ኢንዱስትሪና ፋብሪካ አልባ እንዳያደርገን ያሰጋል።

በተለይ በቤኒሻንጉል ጉሙዝና በትግራይ ክልል ያለው የወርቅ የኮንትሮባንድ ንግድ የውጭ ዜጎችን ሳይቀር ያሳተፈ፣ በተደራጁ ወንጀለኞች የሚመራ ከመሆኑ ባሻገር ለወርቅ ማውጫ የሚጠቀመው ኬሚካል አካባቢ እየበከለ ይገኛል። ከጊዜ ወደ ጊዜ ለብሔራዊ ባንክ የሚገባው ወርቅ እየቀነሰ በኮንትሮባንድ ስለሚወጣ የሀገር ኢኮኖሚ እየደማ ይገኛል። ብሔራዊ ባንክ ወርቅን በዕለቱ የምንዛሬ ዋጋ እንደሚገዛ ቢያሳውቅም ሕገ ወጥ ንግዱ ፈተና መሆኑን ቀጥሏል።

ኮማንድ ፖስትና ብሔራዊ ደህንነት ጣልቃ ቢገቡም የወርቅ ኮንትሮባንድ ሊቆም አለመቻሉን በዚያ ሰሞን የመገናኛ ብዙሃን አጀንዳ ነበር። በዚህ የተነሳ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚመራ የማዕድን ኮሚቴ አዲስ መርሐ ግብር ለማዘጋጀት ተገዷል። በመከላከያ ኮማንድ ፖስትና በብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ጭምር ክትትል ቢደረግም፣ በክልሎች እየጨመረ የመጣው የወርቅና የማዕድናት ኮንትሮባንድ ሊቆም አልቻለም።

በማዕድናት ሕገወጥ ግብይት፣ ኮንትሮባንድና የፀጥታ ችግር ምክንያት በዘጠኝ ወራት ወደ ብሔራዊ ባንክ የገባው ወርቅ ሦስት ቶን ብቻ እንደሆነ፣ ይህም ከዕቅዱ 50 በመቶ ብቻ መሆኑ ታውቋል። የወርቅ ገቢም ከታቀደው 363 ሚሊዮን ዶላር 67 በመቶ ብቻ መሳካቱን ለማወቅ ተችሏል። በመጋቢት ወር ብሔራዊ ባንክ የገባው ወርቅ 350 ኪሎ ግራም ሲሆን፣ ይህም በ2014 ዓ.ም. መጋቢት ወር ከተገኘው 800 ኪሎ ግራም በእጅጉ ያነሰ ነው ተብሏል።

በሀገሪቱ ያሉ ወርቅ አምራቾች የባህላዊና የኩባንያ ተብለው ሲከፈሉ፣ በተለይ በባህላዊ አምራቾች የሚወጣው ወርቅ ሙሉ ለሙሉ በሚባል ደረጃ ወደ ብሔራዊ ባንክ መግባት ያቆመ መሆኑን፣ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ከታቀደው 2,306 ኪሎ ግራም ውስጥ 609 ኪሎ ብቻ (26 በመቶ) መቅረቡን መረዳት ተችሏል። በተለይ ኦሮሚያ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ጋምቤላና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልሎች ለብሔራዊ ባንክ ለማቅረብ ካቀዱት አንፃር የቀረበው እጅግ አናሳ መሆኑን፣ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረበው የማዕድን ሚኒስቴር ሪፖርት ያሳያል።

ይሁን እንጂ ፈጽሞ ወርቅ ካላቀረቡት የትግራይ፣ የአፋር፣ የደቡብ ኢትዮጵያና የሶማሌ ክልል አንፃር የበፊቶቹ እንደሚሻል ሪፖርቱ ያሳያል። በኩባንያዎች ከቀረበው 2,400 ኪሎ ግራም ወርቅ ውስጥ ሚድሮክ ጎልድ በከፍተኛ መጠን ያቀረበ ሲሆን፣ ወደ ሥራ ገብተዋል የተባሉ ሌሎች ዘጠኝ የወርቅ ኩባንያዎች ሲደመሩ ያቀረቡት ከ100 ኪሎ ግራም በታች ነው። ከእነዚህም ውስጥ ስቴላ፣ ዙምባራ፣ ኦሮሚያ ማይኒንግ ኤልኤት፣ ኢዛናና ኢትኖ ማይኒንግ የሚባሉት ይገኙበታል። በተለይ ኢዛና 375 ኪሎ ግራም አቀርባለሁ ቢልም ምንም ዓይነት ወርቅ ወደ ብሔራዊ ባንክ እንዳላስገባ በሪፖርቱ ተመላክቷል።

ከወርቅ በተጨማሪም የታንታለም አፈጻጸም 40 በመቶ ብቻ የተሳካ ሲሆን፣ ኦፓል 49 በመቶ ነው። በአንፃሩ የሊትዬም፣ የጌጣጌጥና የኢንዱስትሪ ማዕድናት የወጪ ንግድ የተሻለ አፈጻጸም ታይቶበታል። አብዛኛው የባህላዊ አምራቾች ወርቅ በሕገወጥ ግብይትና በኮንትሮባንድ ከሀገር የሚወጣ መሆኑን፣ በአንፃሩ ኩባንያዎች ደግሞ በፀጥታ ምክንያት ወደ ሥራ ሊገቡ እንዳልቻሉ ሪፖርቱ ያትታል።

በተለይ በጋምቤላ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በኦሮሚያና በደቡብ አካባቢዎች በወርቅ ማውጫ አካባቢዎች በመከላከያ ሠራዊት እንዲጠበቁና የክልል መንግሥታት ከኮማንድ ፖስትና ከብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ጋር ተቀናጅተው እንዲሠሩ መደረጉ በሪፖርቱ ተመላክቷል።በእነዚህ ክልሎች ፕሬዚዳንቶች፣ የቢሮ ኃላፊዎችና የማዕድን ማውጫ አካባቢዎች አስተዳዳሪዎች ከኮማንድ ፖስት ኃላፊዎችና ከፌዴራል ተወካዮች ጋር ርብርብ እያደረጉ መሆናቸው ተገልጿል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ቀደም ባለ የባህር ዳር የብልፅግና ፓርቲ ስብሰባ ላይ የወርቅና የማዕድናት ኮንትሮባንድ ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረሱን ገልጸው፣ በተለይ አሶሳና ሽሬ ከፍተኛ የሕገወጥ ወርቅ ዝውውር መተላለፊያ መሆናቸውን አስረድተው ነበር። በተለይ ሕገወጥ ወርቅ በሱዳን፣ በኬንያና በሶማሊያ ድንበሮች ከሀገር በመውጣት በዋናነት ዱባይና ህንድ እንደሚደርሱ፣ እንዲሁም እስከ ኡጋንዳ ድረስ ከዚያም ወደ ዱባይ የሚያመራ ሰንሰለት እንዳለ ለዘርፉ ቅርበት ያላቸው ባለሙያዎች ይናገራሉ።

በሕጋዊውና በጥቁር ገበያ መካከል ያለው የምንዛሪ ክፍተት ዋነኛው የችግሩ ምንጭ እንደሆነም በሪፖርቱ ተጠቅሷል። ከጥቂት ወራት በፊት ብሔራዊ የማዕድን ልማት አስተባባሪ ኮሚቴ የተቋቋመ ሲሆን፣ የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ከፍተኛ አመራሮችና የክልል ፕሬዚዳንቶች የኮሚቴው አባል ናቸው። በአሁኑ ጊዜ ኮሚቴው በማዕድን አምራች አካባቢዎችና በማዕድን ኩባንያዎች ፕሮጀክቶች በመገኘት ምልከታና አሰሳ ካደረገ በኋላ፣ የማዕድናት ኮንትሮባንድን ለማስቀረት አዲስ የድርጊት መርሐ ግብር እያረቀቀ መሆኑን በሪፖርቱ ተጠቁሟል።

> **ባህላዊ ወርቅ አምራቾች ለብሔራዊ ባንክ የሚያቀርቡት የወርቅ መጠን ቋሚ ሳይሆን በየዓመቱ የሚዋዥቅ ነው**

የብሔራዊ ባንክ ገዥ አቶ ማሞ ምህረቱ በአንድ አጋጣሚ እንዳሉት፣ የወርቅ ምርት በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጥ ቁልፍ ሚና ከሚጫወቱ የኤክስፖርት ምርቶች መካከል አንዱ ነው። ‹‹ከጥቂት ዓመታት በፊት ከወርቅ ኤክስፖርት ብቻ ከ600 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ተገኝቷል፤›› ብለው እንደገለጹትም፣ በ2014 ዓ.ም. ከወርቅ ኤክስፖርት ብቻ የተገኘው የውጭ ምንዛሪ ገቢ 672 ሚሊዮን ዶላር መሆኑን በማዕድን ሚኒስቴርና በብሔራዊ ባንክ ይፋ ከተደረጉ የሰነድ መረጃዎች ለመገንዘብ ተችሏል። በ2014 ዓ.ም. ብቻ ሳይሆን ከ2003 ዓ.ም. እስከ 2006 ዓ.ም. ለተከታታይ ሦስት ዓመታት ከወርቅ ኤክስፖርት የተገኘው የውጭ ምንዛሪ ገቢ ከ600 ሚሊዮን ዶላር በላይ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል።

በእነዚህ ከፍተኛ ገቢ በተገኘባቸው ዓመታት በባህላዊ የወርቅ አምራቾች ተመርቶ ለገበያ የቀረበው የወርቅ መጠን በአማካይ 9,000 ኪሎ ግራም የነበረ ሲሆን፣ አልፎ አልፎም እስከ 12 ሺህ ኪሎ ግራም ተመርቶ ለብሔራዊ ባንክ ቀርቦ እንደሚያውቅ መረጃዎች ያመለክታሉ። ከ2010 እስከ 2011 ዓ.ም. ጨርሶ ምርት አለተመረተም በሚያስብል ደረጃ አንድ ሺህ ኪሎ ግራም ብቻ ነበር የተመረተው። በ2015 ዓ.ም. ግን በእጅጉ በማሽቆልቆል 3,900 ኪሎ ግራም ወርቅ ብቻ ነው ለብሔራዊ ባንክ የቀረበው።

የማዕድን ሚኒስትሩ ሀብታሙ ተገኝ (ኢንጂነር) ከ2000 ዓ.ም. አንስቶ ለ15 ዓመታት በባህላዊ አምራቾች የተመረተውን የወርቅ ምርት መጠን መረጃ በመዳሰስ፣ ለዓመታት የቀረበውን የወርቅ ምርት መጠን ሁኔታ ለቋሚ ኮሚቴው አስረድተዋል። በዚህም መሠረት ባህላዊ ወርቅ አምራቾች ለብሔራዊ ባንክ የሚያቀርቡት የወርቅ መጠን ቋሚ ሳይሆን በየዓመቱ የሚዋዥቅ ነው። የ15 ዓመታት የወርቅ ምርት አቅርቦት ሁኔታን በመዳሰስ ባቀረቡት ሪፖርትም፣ ባህላዊ አምራቾች ለብሔራዊ ባንክ የሚያቀርቡት የወርቅ መጠን በሕጋዊና በጥቁር ገበያው መካከል ባለው የውጭ ምንዛሪ ተመን ልዩነት እንደሚወሰን አስረድተዋል።

ሚኒስትሩ እንደገለጹት፣ ባለፉት 15 ዓመታት በባህላዊ ወርቅ አምራቾች ተመርቶ ለብሔራዊ ባንክ የቀረበው ትልቁ የወርቅ መጠን 12 ሺህ ኪሎ ግራም ሲሆን፣ ትልቁ ዓመታዊ አማካይ ደግሞ 9,000 ኪሎ ግራም ነው። ከዚህ የወርቅ መጠንም በአማካይ ከ600 ሚሊዮን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሪ ተገኝቷል። ለብሔራዊ ባንክ ከፍተኛ ወርቅ በቀረበባቸው በእነዚህ ዓመታት በሕጋዊና በጥቁር ገበያው መካከል የነበረው የውጭ ምንዛሪ ተመን ልዩነት ጠባብ እንደነበረ፣ በተጨማሪም ብሔራዊ ባንክ በዓለም የወርቅ ዋጋ ላይ እስከ 35 በመቶ ማበረታቻ ጭማሪ በማድረጉ ከፍተኛ ወርቅ እንደቀረበለት አስረድተዋል።

በአንፃሩ፣ የጥቁር ገበያው የምንዛሪ ተመን ከሕጋዊ ገበያው በከፍተኛ ልዩነት በጨመረባቸው ዓመታት፣ ለብሔራዊ ባንክ የሚቀርበው የወርቅ መጠን እጅግ አነስተኛ መሆኑን ጠቁመዋል። የማዕድን ሚኒስትሩ ሲያጠቃልሉም፣ ‹‹የባህላዊ የወርቅ ምርትን ችግር ውስጥ የከተተው በሕጋዊና በጥቁር ገበያው መካከል ያለው የውጭ ምንዛሪ ተመን መስፋት ነው፤›› ብለዋል።

በወርቅ ኮንትሮባንድ ረገድ ያሉትን ችግሮች በየመልካቸው ተረድቶ ከክልሎች ጋር ለመሥራት ያደረጉት ጥረት ቀላል አለመሆኑን የተናገሩት የጉምሩክ ኮሚሽነሩ አቶ ደበሌ ቀበታ፣ አንደኛው መፍትሔ ለወርቅ አምራቾች ፈቃድ በሚሰጡ ክልሎችና በአምራቾቹ መካከል ያለውን ግንኙነት የጠራ ማድረግ ይገባል ብለዋል። ‹‹ፈቃድ የተሰጠው አምራች በየዓመቱ ምን ያህል ወርቅ የማምረት ዕቅድ እንዳለው ታውቆ ቁጥጥር ሊደረግበት ይገባል፤›› ሲሉ ኮሚሽነሩ ምክረ ሃሳባቸውን አቅርበዋል።

የብሔራዊ ባንክ ገዥ አቶ ማሞ በበኩላቸው፣ የሚመረተው ወርቅ ወደ ብሔራዊ ባንክ እንዲመጣ ለማድረግ የተለያዩ የአጭር ጊዜ የመፍትሔ ርምጃዎች እየተወሰዱ መሆናቸውን ገልጸዋል። አንደኛው ከፀጥታ አካላት ጋር ተቀራርቦ መሥራት ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ ከዓለም የወርቅ ገበያ ዋጋ በተጨማሪ ከ60 እስከ 70 በመቶ ጭማሪ በማድረግ ወርቅ ወደ ብሔራዊ ባንክ እንዲመጣ ማድረግ ነው። በመሠረታዊነት ደግሞ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የማዕድን ዘርፍ እንቅስቃሴ ለማሳደግ ብሔራዊ የማዕድን ካውንስል የተቋቋመ መሆኑን፣ ይህም ሁሉንም ባለድርሻ አካላት በማቀናጀት የተሻለ ሥራ ለማከናወን መታቀዱን ገልጸዋል።

የማዕድን ሚኒስትሩ ሀብታሙ (ኢንጂነር)፣ የተቋቋመው ብሔራዊ የማዕድን ምክር ቤት በዘርፉ ላሉት መሠረታዊ ችግሮች መፍትሔ ይሰጣል የሚል እምነት እንዳላቸው ተናግረዋል። በዚህ ምክር ቤት የመጀመሪያ ውይይት ላይም በማዕድን ዘርፍ ያለውን ኮንትሮባንድና የፀጥታ ችግር መፍትሔ ለመስጠት የማዕድን ፖሊስ ሠራዊት እንዲደራጅ መወሰኑን አክለዋል። በዘላቂነት ደግሞ የወርቅ ሀብቱ ኃላፊነት በሚሸከሙ ከፍተኛ ወርቅ አምራች ኩባንያዎች እንዲመረት ማድረግ፣ የሀገሪቱን ጥቅም መጠበቅ እንደሚያስችል ገልጸዋል።

**ሻሎም ! አሜን ።**

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

## ሕይወት በተስፋ ገብረሥላሴ ማተሚያ ቤት

ምሕረት ሞገስ

ተስፋ ገብረሥላሴ የፊደል አባት መባል ቢያንስባቸው እንጂ የሚበዛባቸው አይደሉም። ምክንያቱም በኢትዮጵያ መጀመሪያ ፊደል በካርቶን ላይ ፅፈው ለማሰራጨት የሞከሩ ታላቅ አባት መሆናቸውን የትኛውም በተስፋ ገ/ሥላሴ ፊደል የተማረ ኢትዮጵያዊ የሚዘነጋው አይደለም።

ጥበበ ተስፋ ገ/ሥላሴ ደግሞ የተስፋ ገብረሥላሴ 5ኛ ልጅ ናቸው። አቶ ጥበበ የተወለዱት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በአሁኑ የተፈጥሮ ሳይንስ ፋክልቲ 4 ኪሎ ጊቢ ነው። በአራት ኪሎ የተፈጥሮ ሳይንስ ዩኒቨርሲቲ ጊቢ ውስጥ በ1935 ዓ.ም እርሳቸው ይህችን ዓለም ሲቀላቀሉ፤ የአሁኑ ቅድስት ሥላሴ አካባቢ ያለው ህንፃ በዛ ወቅት የትምህርት ሚኒስቴር ሕንፃ ነበር።

የአሁኑ የስድስት ኪሎ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ) ከመቋቋሙ በፊት፤ የአሁኑ የአራት ኪሎ ዩኒቨርሲቲ ደግሞ የመጀመሪያው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ሆኖ እንዲቋቋም እቅድ ተያዘ። ስለዚህ አቶ ጥበበ ልክ እንደተወለዱ አባታቸው ተስፋ ገ/ሥላሴ የወቅቱ የልማት ተነሺ ሆነው ኮሌጁ እንዲቋቋም ቦታቸውን ለቀቁ። በምትኩ ከአራት ኪሎ ብዙም ሳይርቁ ከአሁኑ ትምህርት ሚኒስቴር ጀርባ 7ሺህ ካሬ ሜትር ቦታ ተሰጣቸው። የአሁኖቹ የአራት ኪሎ ሕንፃዎች ባሉበት አካባቢ ሰፊ ቦታ የተሰጣቸው ቢሆንም፤ አሁን ላይ 2ሺህ 500 ካሬ ሜትር ቦታ ውጪ ሁሉም ቦታ በተለያየ ጊዜ እየተገፉ ተወስደውባቸዋል።


‹‹የላይኛው የስድስት ኪሎ ዩኒቨርሲቲ የቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ዩኒቨርሲቲ ይባል ነበር። በኋላ በደርግ ጊዜ ስሙ ተቀይሮ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተባለ። ከዛ በፊት ግን የመጀመሪያው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ የተቋቋመው እኔ በተወለድኩበት በአባታችን በተስፋ ገ/ሥላሴ ጊቢ ነው።›› ሲሉ የሚናገሩት አቶ ጥበበ፤ አባታቸው የአሁኑ የተስፋ ገብረሥላሴ ማተሚያ ቤት ባለበት አካባቢ መኖሪያ ቤት ገንብተው ኑሯቸውን ከመመሥረት አልፈው ማተሚያ ቤት ከፍተው አሁን ድረስ የሕትመት ሥራ እየተከናወነ እንደሚገኝ ገለፁልን።

አቶ ጥበበ ምንም እንኳ ለቤታቸው ሁለት ታላላቅ ሴት እህቶች እና ሶስት ታላላቅ ወንድሞች ቢኖሯቸውም፤ አሁን ላይ ሶስቱም ወንድሞቻቸው በሕይወት የሉም። ስለዚህ አቶ ጥበበ ለ47 ዓመታት ከኖሩባት ሀገረ አሜሪካ መጥተው የተስፋ ገ/ሥላሴን ማተሚያ ቤት እየመሩ ይገኛሉ።

### የፊደሉ ታሪክ

ተስፋ ገብረሥላሴ በቡልጋ ሸንኮራ አካባቢ የሚኖሩ ካህናትን የተዛመዱ ብቻ ሳይሆኑ የካህን ዘር ናቸው። የቡልጋ ሕዝብ ደግሞ አለቃ እገሌ፤ አለቃ እገሌ የሚባባል ሲሆን፤ የአካባቢው ነዋሪ ከ80 በመቶ በላይ ፊደል የቆጠረ ነው። ስለዚህ ተስፋ ገብረሥላሴም የተወለዱበት አካባቢ ፊደል ለመቁጠር ምቹ ሁኔታ ስለፈጠረላቸው ፊደላትን በደንብ አወቁ። ነገር ግን በዛ አላበቁም። ዳዊት መድገም ቻሉ፤ ድቁና ላይ ደረሱ። ተስፋ ከድቁና አልፈው ወደ ቄስነት ሊሄዱ አልወደዱም። ቄስነት ይቅርብኝ አዲስ አበባ ከተማ መግባት ይሻለኛል ብለው ወንድማቸው ብርሃኑ ቤት መጥተው ተቀመጡ።

ሌላ ሥራ መሥራት ስለማይችሉ መነገድ ጀመሩ። የመጀመሪያው ንግዳቸው ሽቶ መሸጥ ነበር። ሽቶ አልሸጥላቸው ብሎ ተቸገሩ። ሽቶ መሸጥን ትተው፤ ጋዜጣ መሸጥ ጀመሩ። በሌላ በኩል ደግሞ የጋዜጣ ሽያጫቸውም አዋጭ አልሆነም። ምክንያቱም ሰዎች መግዛት ቢፈልጉም ማንበብ ስለማይችሉ ጋዜጣ መሸጥ ፈተና ሆነባቸው። አንዳንዶች ደግሞ ‹‹እንግዛህ እና አንብብልን።›› እያሉ መጠየቅ ጀመሩ። ተስፋ ገበያ በማጣታቸው ብቻ ሳይሆን ሰዎች ማንበብ ስለማይችሉ፤ ‹‹ለምን ሰዎች ማንበብ አቃታቸው ?' ብለው ራሳቸውን ጠየቁ። ለጥያቄያቸው ራሳቸው ምላሽ አገኙ። ምክንያቱም ፊደል የሚያውቁት እና ማንበብ የሚችሉት ልክ እንደሌላው ዓለም ሁሉ የቤተ ክህነት እና የቤተመንግሥት ሰዎች ብቻ በመሆናቸው ነው ሲሉ ለራሳቸው ምላሽ ሰጡ። በእርግጥ የመንግሥት ሥራን የሚሠሩ ሰዎችም ፊደል ለይተው ማንበብ ይችሉ ነበር። ነገር ግን እነርሱም ከቤተ ክህነት እና ከቤተመንግሥት ብዙም የራቁ አልነበሩም።




ስለዚህ ተስፋ ጋዜጣው እንዲሸጥላቸው ብቻ ሳይሆን ሕዝቡ ማንበብ መቻል አለበት ብለው ማሰብ ጀመሩ። መላ ዘየዱ። በእርግጥ እርሳቸው በቤተክህነት ሲማሩ ፊደል በቆዳ ተቀርፆ ይቆጥሩ ነበር። ያንን ማድረግ እና ለሕዝብ ማዳረስ ከባድ መሆኑን ተረድተዋል። ስለዚህ ከዕፅዋት ቀለም እየቀመሙ ካርቶን ላይ ፊደሎቹን በቅደም ተከተል ፃፏቸው። ሀ ሁ ሂ ...ከሚሉት በተጨማሪ ኣ ቡ ጊ ዳንም ፃፉ። ተስፋ ይህንን ያደረጉት በ 1910 ዓ.ም ነበር። ፊደላቱን በብዛት ፅፈው የካቲት 23 ቀን የዓድዋ ድል ሲከበር አራዳ ጊዮርጊስ መሸጥ ጀመሩ። በዛ ጊዜ ብዙዎች ፊደል ማወቅ ይፈልጉ ስለነበር የፃፉትን በሙሉ ገዟቸው። ከዛ ወዲያ ፊደላቱ በመላ ከተማዋ እየታወቁ ሔዱ። ነገር ግን በእጅ እየፃፉ መሸጥ ቀላል አይደለም።

ስለዚህ ሌላ አማራጭ ለመፈለግ ወሰኑ። በዛ ጊዜ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ያቋቋሙት መርሃፅድቅ ማተሚያ ቤት ሄዱ። ‹‹ቤተክህነት ፊደል አምጥቷል። እናንተ ደግሞ ማተሚያ አላችሁ። ፊደል እናትምና ሕዝቡን ፊደል እንዲለይ እናግዘው። እባካችሁ ፊደላቱን እንዳትም ፍቀዱልኝ።›› በማለት ለማተሚያ ቤቱ ሃላፊ ጥያቄ አቀረቡ። ማተሚያ ቤቱን ሲያስተዳድሩ የነበሩት ሰው ‹‹ይቻላል›› ብለው ፈቀዱላቸው። በኋላ መሃል ላይ መልዕክተ ዮሃንስ አካተው። በግራ ሀ ሁ ሂ ሃ ... በቀኝ አ ቦ ጊ ዳ ... አሳትመው መሸጥ ጀመሩ። በመጨረሻም የአማርኛ ፊደል ብቻ ሳይሆን የእንግሊዝኛ ፊደል እና ቁጥሮች ተካተውበት በስፋት እየታተመ እንዲሸጥ ማድረግ ቻሉ። በኋላም ራሳቸው ማተሚያ ቤት አቋቋሙ ሲሉ የፊደሉን ታሪክ የነገሩን ልጃቸው አቶ ጥበበ ተስፋ ናቸው።

### የተስፋ ገ/ሥላሴ ትዳር

ቀኝ አዝማች ተስፋ ከመጀመሪያው ትዳራቸው ሁለት ወንድ እና አንዲት ሴት ልጅ ወልደው ነበር። ወንዶቹ አሁን አርፈዋል። የእነርሱ እናት ደግሞ የሞቱት በጣሊያን ወረራ ጊዜ ነው። ጣሊያን ማይጨው ላይ የጦርነቱን ሳይሆን የጦር ሜዳውን ሲያሸንፍ፤ ሰዎች ከአዲስ አበባ ተነስተው ይሸሹ ነበር። አንዳንዶች ደግሞ ሸፍተው ይዋጉ ነበር። ቀኝ አዝማች ተስፋም ከነራስ አበበ አረጋይ ከእነሃይለማሪያም ማሞ ጋራ ቡልጋ ሸፈቱ። ቀኝ አዝማች ተስፋ ሲሸፍቱ ባለቤታቸው በወረርሽኙ ተያዙ። በቂ ህክምና ማግኘት ባለመቻላቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። ከዛ ከነፃነት በኋላ የእነጥበበ ተስፋን እናት አገቡ።

ሁለተኛዋ ሚስታቸው ወ/ሮ አለሚቱ ንጉሤ የመጡት ከጎጃም ነው። ፊደል ስለማይለዩ ማንበብ እና መፃፍ አይችሉም ነበር። ስለዚህ ቀኝአዝማች ተስፋ ገብረስላሴ ሚስታቸውን በደንብ ፊደል እንዲቆጥሩ ከማስተማር ባሻገር፤ ልጆች እየወለዱና እያሳደጉ ዳግማይ ምኒልክ ትምህርት ቤት ገብተው እንግሊዝኛም ማንበብ እና መፃፍ እንዲችሉ አገዟቸው። በኋላም የተስፋ ገብረሥላሴ ሚስት ከማህይምነት ወጥተው የራሳቸውን መኪና እስከመንዳት ደርሰው ነበር።

### ሕይወት እስከ ተስፋ ገ/ሥላሴ ማተሚያ ቤት

አቶ ጥበበ እንደሚናገሩት፤ እርሳቸው እና ታናናሾቻቸው ተወልደው ጭምር እናታቸው ትምህርት ቤት እየተመላለሱ ሲማሩ እንደነበር ያስታውሳሉ። አቶ ጥበበ አራት ዓመት ሲሞላቸው ፊደል ቆጠሩ። ቀኝ አዝማች ተስፋ ከቡልጋ ቄስ አስመጥተው አቶ ጥበበ ዳዊት እንዲደግሙ አደረጉ። የቅድስት ሥላሴ ቤተክርስቲያን መንፈሳዊ ኮሌጅ ከመቋቋሙ በፊት የድቁና ትምህርት ነበር። እዛም ቀጠሉ። በኋላ ሊሴ ገብረማርያም ትምህርት ቤት ገቡ። በኋላም አባታቸው እና እናታቸው ተመካክረው ‹‹ፈረንሳይኛ ከሚማር እንግሊዝኛ ቢማር ይሻላል።›› ብለው አጠና ተራ ልዑል መኮንን ትምህርት ቤት አስገቧቸው። ፈተናቸውን አልፈው ጀነራል ዊንጌት ትምህርት ቤት ተምረው ጨረሱ።

በወቅቱ የተስፋ ገ/ሥላሴ ማተሚያ ቤት በደንብ እየሠራ ነበር። የመጀመሪያውን ሃይሊንበርግ የተባለ ትልቅ ሲሊንደር ያለው የማተሚያ ማሽን ከውጭ አስመጥተው ነበር። ማሽኑ ትልልቅም ሆነ ትንንሾቹ ወረቀቶች ላይ የሚያትም አውቶማቲክ ማሽን ነበር። ያንን ማሽን ኢትዮጵያ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ያመጡት ተስፋ ገብረሥላሴ ናቸው። እናም አቶ ጥበበ ከትምህርት ቤት መጥተው መጀመሪያም ከወንድሞቻቸው ጋር ይሠሩ የነበረበት የአባታቸው ማተሚያ ቤት ገቡ። የማተሚያ ማሽኑ ሲበላሽ የፈረንሳይ መካኒክ ያስተካክለው ይባል ነበር። ማሽኑን የሚሠራው ሰው ከፈረንሳይ ከመጣ በኋላ የሚነጋገረው ከአቶ ጥበበ ጋር ብቻ ሆነ። ምክንያቱም አቶ ጥበበ ፈረንሳይኛ ስለሚያውቁ ከፈረንሳዩ መካኒክ ጋር አብረው ማሽኑን መሥራት ቀጠሉ። አቶ ጥበበ በኋላም የማሽኑን መመሪያ (ማንዋል) እያነበቡ ማሽኑን በደንብ አወቁት። አቶ ጥበበ በማተሚያ ቤቱ ከመሥራት አልፈው ስለህትመት መማር ፈለጉ።

የአቶ ጥበበ እናት ደግሞ ለቀኝ አዝማች ተስፋ እ.አ.አ በ1966 ዓ.ም፤ ‹‹ጥበበ ጀነራል ዊንጌት ተምሮ 12ኛ ክፍል አጠናቋል። ዩኒቨርሲቲ ከመግባት ይልቅ ውጪ ሔዶ ቢማር ይሻላል። ብለው አማከሯቸው። ይህንን ሃሳብ ተከትሎ አቶ ጥበበ የህትመት ሳይንስ ለመማር ጀርመን ሔዱ። በዛ ጊዜ ጀርመን ውስጥ ብዙ ኢትጵያውያን አልነበሩም። ከአቶ ጥበበ በፊት ሁለት ሰዎች ብቻ ነበሩ። በሚኖሩባት ከተማ ውስጥ ኢትዮጵያዊ ወንጀል ሰራ ቢባል የሚጠየቁት እርሳቸው ብቻ ነበሩ። በጀርመን የቴክኒክ ትምህርት ቤት ገብተው የሕትመት (ፕሪንቲንግ) ሳይንስተ ተማሩ። ቀጥለው በ1968 ዓ.ም እንደገና አንድ ማሽን ላይ ጥናት ለማካሔድ ኬንያ እና እንግሊዝ ሄደው ጥናታቸውን አጠናቀቁ። በኋላም ለትምህርት አሜሪካን የሔዱ ሲሆን፤ እዛም በድጋሚ የሕትመት ሳይንስን ተማሩ። ዛሬ ነገ ወደ አገሬ እመለሳለሁ ሲሉ፤ ከአንድ አሜሪካዊት ጋር በፍቅር ወደቁ። ልጆች ወለዱ፤ በኋላም በዛው ቀሩ።


ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

## ሕይወት በተስፋ ገብረሥላሴ...

ከገጽ 6 የዞረ



**ለመጀመሪያ ጊዜ ዘመናዊ ማሽን ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ ያደረጉት ተስፋ ገብረሥላሴ ናቸው:: አሁን ግን የነበራቸው ይዞታ ተቀንሶ ከ100 ዓመት በላይ ዕድሜን ያስቆጠሩ ማሽኖች መቀመጫ አጥተዋል**

አቶ ጥበበ አራት ልጆች ወልደው አሳደጉ:: ልጆቹ ተመርቀው ራሳቸውን ችለው እየኖሩ ናቸው:: አንደኛው የአሜሪካ ወታደር ሆነ:: ሁለቱ ዳግሞ ባዮኬሚስት ናቸው:: አንደኛዋ ደግሞ ሕይወቷ አልፏል:: እንደአቶ ጥበበ ገለፃ፤ አሜሪካ ለመኖር ምቹ ናት:: አንድ ሰው ከሠራ ቤተሰብ መመሥረት ይችላል:: ቤተሰቡን በደንብ ለማስተዳደር አይቸገርም:: በአሜሪካ በቂ የጤና አገልግሎት አለ:: አንድ ሰው ከሠራ በአሜሪካ ምድር የፈለገበት መድረስ ይችላል:: በአብዛኛው የአሜሪካ ሕዝብ በጣም ጥሩ ሕዝብ ነው::

ከስምንት ዓመት በፊት ግን ለ47 ዓመታት ከኖሩባት ከአሜሪካን መጡ:: አሜሪካ ጡረታ ሲወጡ ወደ ሀገራቸው ገቡ:: ወደ ኢትዮጵያ አዲስ አበባ መጥተው የአባታቸውን ተስፋ ገ/ሥላሴ ማተሚያ ቤትን ማስተዳደር ጀመሩ:: አሁን በማተሚያ ቤቱ በተለይ የቤተክህነት መፅሃፍትን እያሳተሙ ይገኛሉ:: ከ300 በላይ ዓይነት የቤተክህነት መፅሐፍትን እያሳተሙ ሲሆን፤ ከእነዚህ መሃል ተዓምረ እየሱስ፣ ተዓምረ ማሪያም፣ መዝሙረ ዳዊት እና ሌሎችም ይገኙበታል:: አሁን ግን የወረቀት ዋጋ በከፍተኛ መጠን እየጨመረ በመሆኑ ፈታኝ ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ ገልፀውልናል::

### የአሜሪካ ኑሮ

አቶ ጥበበ በአሜሪካ ትዳር መሥርተው ልጅ ወልደው ሲኖሩ፤ አንዷ ልጅ በጣም ታመመችባቸው:: ሐኪም ቤት ስትሔድ ገና በሶስት ዓመቷ የሥኳር በሽተኛ መሆኗ ታወቀ:: ከፍተኛ ክትትል ስለሚያስፈልጋት ሆስፒታሉ ውስጥ መተኛት አለባት ተባለ:: አቶ ጥበበ በበኩላቸው ሆስፒታሉ የሚያስከፍለው ገንዘብ ከፍተኛ በመሆኑ ‹‹አቅም የለኝም፤ ልጄን ወደ ሌላ ሆስፒታል እወስዳለሁ›› አሉ:: ሐኪሙ ግን የገንዘቡ ጉዳይ ከልጅቷ ሕይወት አይበልጥም፤ ስለዚህ ቅድሚያ ልጅቷ ትትረፍ ብሎ ሕክምናው ተሰጣት እናም ተሽሏት ወደ ቤት ገባች:: አቶ ጥበበ በአራት ወር ውስጥ ሠርተው ልጃቸውን ያሳከሙበትን ዕዳ ለሆስፒታሉ ከፈሉ::

‹‹አሜሪካ ሀኪም በጭራሽ ክፍያ ካልተፈፀመ አላክምም ማለት አይቻልም:: ታካሚው ወይም የታካሚው ቤተሰብ ሠርቶ ይከፍላል:: ከዛ ውጪ በዋናነት ትኩረት የሚሰጠው ሰዎችን የህክምና አገልግሎት ሰጥቶ ማዳን ብቻ ነው::›› ይላሉ:: አያይዘውም አሜሪካን ትምህርት ቤት በነፃ ነው:: ልጆች ምሳ የሚበሉት እዛው ትምህርት ቤት ነው::

አቶ ጥበቡ እንደሚገልፁት፤ ወደ ውጪ ከመሔዳቸው በፊት አዲስ አበባ በነበሩበት ጊዜ የኢትዮጵያ አጠቃላይ ሕዝብ 23 ሚሊዮን ብቻ ነበር:: የአዲስ አበባ ነዋሪም 100 ሺህ አይሞላም:: ስለዚህ በሁሉም መስክ ኑሮ የተሻለ ነበር:: የሕዝቡ ቁጥር ውስን ቢሆንም የህክምና አገልግሎት ንግሥት ዘውዲቱ ሆስፒታል ነበር:: ሐኪሞቹ እና ነርሶች ከውጪ የመጡ ነበሩ:: ደጅ አዝማች ባልቻ ሆስፒታልም ራሺያዎች ነበሩ፤ የጣሊያን እና የግሪክ ዶክተሮች የኢትዮጵያንም እነፕሮፌሰር አስራትን ጨምሮ ምርጥ ሐኪሞች ነበሩ:: በዛ ወቅት ሕዝቡ ጥቂት በመሆኑ ሐኪሞቹም ሆኑ ሆሲፒታሎቹ በቂ ነበሩ:: ዶክተሮች በበቅሎ ገጠር ሔደው ቤት ለቤት ሳይቀር ያክሙ ነበር::

አሁን የሕዝቡ ቁጥር እጅግ ጨምሯል:: በእርግጥ ብዙ ሐኪሞችም አሉ:: ሆስፒታሎች ግን ቁጥራቸው ውስን ነው:: የካቲት 12 ሆስፒታል በፊትም ነበር:: ራስ ደስታ ሆስፒታል እና ሌሎችም ነበሩ:: የሆስፒታል ቁጥር ብዙ አልጨመረም:: በቂ ዶክተሮችም የሉም:: ዶክተሮቹም ልምዳቸው ውስን ነው::

### መልዕክት

አቶ ጥበበ ባስተላለፉት መልዕክት፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠንካራ ነው:: ብዙ ነገር ሲሠራ ይታያል:: ኢትዮጵያውያን ሀገራቸው ላይ ይሠራሉ:: ‹‹ከጠረፍ እስከ ጠረፍ የነበረው የኢትዮጵያዊነት ስሜት አሁን እየወረደ ነው:: በእኛ ጊዜ ይሔ አማራ ነው፤ ይሔ ኦሮሞ ነው፤ ይሔ ትግሬ ነው የሚባል ነገር የለም::›› ይላሉ:: እንደአቶ ጥበበ ገለፃ፤ በፊት እነርሱ ልጆች እያሉ የሚወራው ስለጀግንነት ነው:: ተደጋግሞ የሚነሳው ኢትዮጵያውያን ከኢትዮጵያውያን ጋር ያደረጉት ጦርነት ወይም ይሔኛው ብሔር ከዚህ ብሔር ጋር ብሎ መለየት አልነበረም:: ጣሊያንን እንዴት እንዳሸነፋ ይወራ ነበር::

ያው ከጣሊያን ጋር በነበረው ጦርነት ደግሞ ቀኝ አዝማች ተስፋ ገ/ሥላሴ ተሳትፈው ስለነበር፤ እርበኞች በቤታቸው አቅራቢያ ተገናኝተው ያወሩ ነበር:: ብዙም ሳይቆይ ያንን ተከትሎ በ1933 ዓ.ም የኢትዮጵያ ጀግኖች ማህበር ተቋቋመ::

የማህበሩ ሊቀመንበር ማን ይሁን? ሲባል አንዳንዶች ‹‹የምንወዳቸው እና የምናከብራቸው ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ይሁኑ›› ሲሉ፤ ሌሎች ደግሞ እርሳቸው በጣሊያን ወረራ ጊዜ ተሰደዋል እርሳቸው አይሆኑም አሉ:: አልጋ ወራሽ እከሌ ሲባል ሁሉም ተሰደዋል:: እኛ እንምረጥ ብለው እንቁ ስላሴ፣ በኋላ አበበ አረጋይም አርበኛ ነበሩ:: አበበ አረጋይ የራስ ጎበና የልጅ ልጅ ናቸው:: ነገር ግን የቡልጋን አርበኛ ሲመሩ እርሶ ኦሮሞ ነዎት እኛ በእርሶ አንመራም አላሉም:: በፊት በጠቅላይ ግዛት ነበር:: ጠቅላይ ግዛት ማለት ደግሞ በገንዘብ መግዛት አይደለም:: ለግዛት ያመች ዘንድ አካባቢውን በግዛት ማስቀመጥ ስለነበር የብሔር ልዩነት ጉዳይ እንደአሁኑ ከሮ የሚታይ አልነበረም::

የተስፋ ገ/ሥላሴ ዘብሔረ ቡልጋ ማተሚያ ቤቱ ከተቋቋመ 100 ዓ.ም ሆኖታል:: የሚሉት አቶ ጥበበ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ይህ ማተሚያ ቤት የጀርባ አጥንት ሆኖ ቆይቷል:: አሁንም ማገልገላችንን እንቀጥላለን ሲሉም ሃሳባቸውን ቋጭተዋል::

### 52 ዓመታትን በማተሚያ ቤት

በ1945 ሰሜን ሸዋ እንሳሮ አውራጃ የተወለዱት አቶ ንጉሤ ቃቂሳም፤ መጀመሪያ ፊደል የለዩት በተስፋ ገ/ሥላሴ የፊደል ገበታ መሆኑን በመግለፅ ኮከበ ፅብሃ ገብተው እስከ 12ኛ ክፍል መማራቸውን ይናገራሉ:: በ1964 ዓ.ም የተቀጠሩ ሲሆን፤ ለ52 ዓመታት በዛው ማተሚያ ቤት ውስጥ ሲሠሩ ቆይተዋል:: ሙያም የተማሩት እዛው አካባቢ መሆኑን ይናገራሉ::

አቶ ንጉሤ እንሳሮ ተወልደው ወደ አዲስ አበባ የመጡት አያታቸው ቤት ለማደግ ነበር:: አያትየው የቤተመንግሥት ፈረስ ቤትን ይጠብቁ ነበር:: ስለዚህ ከአያታቸው ጋር ሲኖሩ፤ አያት የልጅ ልጃቸውን አቶ ንጉሤን ትምህርት ቤት አስገቧቸው:: በ1953 ዓ.ም ደግሞ እናት እና አባታቸው ከገጠር በመምጣታቸው፤ ወደ አባታቸው ቤት ገቡ:: አባታቸው አቶ ቃቂሳ ለአቶ ተስፋ ገብረሥላሴ የጭቃ ቤት ሠርተው ሲጨርሱ፤ ‹‹ምን ላድርግልህ?›› ሲሉ ጠየቋቸው:: ልጄን ሥራ አስቀጥሩልኝ አሏቸው:: በዛ አጋጣሚ አቶ ንጉሤ በተስፋ ገብረሥላሴ ማ/ቤት ለመቀጠር ዕድል አገኙ:: ደሞዛቸው 15 ብር ሆኖ መሥራት ጀመሩ::

ማሽን ሲበላሽ ለመሥራት እየሞከሩ በሒደት ራሳቸውን ችለው መሥራት ቀጠሉ:: በኋላም የህትመት ማሽን ጥገና ከፍተኛ ብቃት ያላቸው ቢሆኑም፤ በትምህርታቸው እና ባላቸው ሙያ ልክ ተጠቃሚ አለመሆናቸውን ይናገራሉ:: በተስፋ ማተሚያ ቤት ብቻ ሳይሆን አርትስቲክ ማተሚያ ቤት ገብተው ሠርተዋል:: የማተሚያ ቤት ሥራ በፈረቃ በመሆኑ አርትስቲክ ማተሚያ ቤትም ለ33 ዓመታት ሲሠሩ፤ ጎን ለጎን በተስፋ ገ/ሥላሴ ማተሚያ ቤትም ያገለግሉ ነበር:: አንዱ ማተሚያ ቤት ጠዋት ሠርተው ከወጡ፤ እስከማታ ደግሞ ሌላ ማተሚያ ቤት ይሠሩ እንደነበርም ይናገራሉ::

ከተስፋ ገ/ሥላሴ ጋር ልዩ ቅርበት እንደነበራቸው የሚናገሩት አቶ ንጉሤ፤ በ1990ዎቹ ሲያርፉ በምትካቸው ልጆቹ ማስተዳደር መጀመራቸውን እና በዛ ማተሚያ ቤት ምክንያት ብዙዎች እንጀራ እንደወጣላቸው ምስክርነት ሰጥተዋል:: እርሳቸውም በተስፋ ገ/ሥላሴ ማተሚያ ቤት በቀሰሙት ሙያ ሰሜን ጎንደር፤ ባህርዳር እና ወሎ ድረስ ሔደው ማሽን እየሠሩ ገቢ እያገኙ ሲያገለግሉ ቆይተዋል:: በምስራቅ ሱማሌ አርጌሳ ድረስ ማሽን ለመትከል እና ለመጠገን መሔዳቸውንም ነግረውናል::

አንድ ሰሞን ከተስፋ ገ/ሥላሴ ማተሚያ ቤት ራቅ ብለው ነበር:: በዛ አጋጣሚ አንድ ማሽን ተበላሽቶ ብዙ ተሞክሮ ሊሠራ አይችልም ከተባለ በኋላ፤ አቶ ንጉሤ ግን በተወሰነ ሰዓት ውስጥ እንዲሠራ አድርገውታል:: ይህ ማሽን አሁንም እያገለገለ ይገኛል ብለውናል:: ‹‹የተስፋ ገ/ሥላሴ ማተሚያ ቤት ብዙ ዋጋ አግኝቼበታለሁ:: ስለዚህ ለማተሚያ ቤቱ እቆረቆራለሁ:: የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል በመሆኔ፤ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና ባህል ቱሪዝም ድረስ እየሔድኩ የተስፋ ታሪክ መታወቅ አለበት እያልኩ እሞግታለሁ::›› ብለውናል::

እንደአቶ ንጉሤ ገለፃ፤ ቀኝ አዝማች ተስፋ ተቀጣሪዎችን ሠራተኞቻቸውን የማይበድሉ ነበሩ:: በፍፁም አያባርሩም ነበር:: ሀገር ወዳድም ነበሩ:: በጣም ፈጣን ጭንቅላት ያላቸው ሰውም ነበሩ:: ከዕፅዋት ቀለም እያወጡ ይፅፉ ነበር:: በጣሊያን ጊዜ የቅስቀሳ ወረቀት እያተሙ ይበትኑ ነበር:: ተስፋ የሀገር ባለውለታ ናቸው:: ነገር ግን ከ7 ሺህ ካሬ ሜትር ቦታ ውስጥ የቀራቸው እጅግ በጣም ጥቂት ነው:: የልጃቸው ቤት እና መጋዘናቸው ተገንብቶ የነበረበት ቦታ በሌላ ሰው ተወስዶ ሕንፃ ተገንብቶበታል:: የአትክልት ሥፍራቸውም በሌሎች ሰዎች ተወስዶባቸዋል:: ለመጀመሪያ ጊዜ ዘመናዊ ማሽን ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ ያደረጉት ተስፋ ገብረሥላሴ ናቸው:: አሁን ግን የነበራቸው ይዞታ ተቀንሶ ከ100 ዓመት በላይ ዕድሜን ያስቆጠሩ ማሽኖች መቀመጫ አጥተዋል::

አቶ ንጉሤ አልወለድም፣ ኦሮማይ፣ ሰመመን እና ሌሎችም ታዋቂ መጽሐፎችን ማተም ብቻ ሳይሆን ከደራሲን ጋርም የጠበቀ ግንኙነት እንደነበራቸው ይናገራ:: በተለይ ከአቤ ጎበኛ ጋር የቅርብ ግንኙነት እንደነበራቸውም ይናገራሉ:: ኮምፒውተር ባልነበረበት ዘመን፤ ብዙ የመፅሃፍ አንባቢ ነበር የሚሉት አቶ ንጉሤ፤ እርሳቸውም ጋዜጦችን በተለይም አዲስ ዘመን ላይ የጳውሎስ ኞኞን አምድ እንደሚያነቡ ይናገራሉ:: 15 ብር ደሞዝ ሲከፈላቸው አዲስ ዘመንን እና የዛሬይቱን ጋዜጣ በ20 ሳንቲም በየሳምንቱ እየገዙ ያነቡ ነበር::

አቶ ንጉሤ ስለአቶ ተስፋ ሲናገሩ፤ ‹‹ቀኝ አዝማች ተስፋ የአመጋገብ ሥርዓታቸው ጥሩ ነው:: ስፖርታዊ እንቅስቃሴ ያደርጋሉ፤ ተስፋ እስከ መጨረሻው ቀና ብለው ይሔዱ ነበር:: ጥራጥሬ በተለይም ገብስ እና ሽንብራ ያዘወትሩ ነበር:: አልኮል ከመጠጣት ይልቅ የሚያዘወትሩት ቆሎ ብቻ ነው:: ለማንኛውም ሰው ዓርአያ መሆን የሚችሉ አባት ነበሩ›› በማለት ሃሳባቸውን አጠናቀዋል

### ከልጅነት እስከ ዕውቀት በተስፋ ገ/ሥላሴ ማተሚያ ቤት

ወይዘሮ ፅጌ በየነም ለአምስት አስርት ዓመታት በተስፋ ገ/ሥላሴ ማተሚያ ቤት ሲሠሩ ቆይተዋል:: ወይዘሮ ፅጌ አዲስ አበባ ሰሜን ሆቴል አካባቢ የተወለዱ ሲሆን፤ መጀመሪያ ወይዘሮ ቀለመወርቅ ትምህርት ቤት ገብተው እስከ ስድስተኛ ክፍል ተማሩ:: 7ኛ ክፍል ሲደርሱ ግን የ1966 ዓ.ም ለውጥ መጣ:: መማር አልቻሉም፤ ስለዚህ ትምህርት አቋረጡ:: በድጋሚ በ1968 እና በ1969 ዓ.ም ተምረው የ8ኛ ክፍል ፈተናን ተፈትነው ሲጨርሱ፤ለቀኝ አዝማች ተስፋ ገብረሥላሴ የሚሠሩ አጎታቸው ለክረምት ትስራ ብለው አምጥተው ወይዘሮ ፅጌን አስቀጠሯቸው::

ወረቀት ማጠፍ እና ሌላውንም ይሠራሉ:: በሂደት መፅሃፍ መስፋት እና መጠረዝ ጀመሩ:: ፊደል ማጠፍ፣ አስሮ ማስቀመጥ እና ሌሎች ሥራዎችንም መሥራት ቀጠሉ:: በዕድሜ ገና ልጅ በመሆናቸው ሙሉ ደሞዛቸውን ለቤተሰቦቻቸው ይሠጡ ነበር:: በ1970 ዓ.ም የመንግሥት ሠራተኞች ደሞዝ ሲጨመር፤ የእርሳቸውም ደሞዝ ወደ 50 ብር አደገ:: በዛ ጊዜ 50 ብር ብዙ ነበር:: ነገር ግን ሙሉ ደሞዛቸውን ሰጥተው ምሳቸውን ተቀብለው በማተሚያ ቤቱ ውስጥ እየሠሩ ሕይወትን መግፋት ቀጠሉ::

በኋላም ቀን ማተሚያ ቤት እየሠሩ የማታ መማር ጀመሩ:: 12ኛ ክፍል ቢደርሱም ወደ ሌላ ቦታ ሥራ ለመቀየር አልፈለጉም:: ምክንያቱም ትዳር መስርተው ልጆች መውለድ ሲጀምሩ፤ አለቆቻቸው ብዙ አይጫናቸውምና እዛው ማተሚያ ቤት እንደተቀጠሩ መቆየትን መረጡ:: ልጆች እስኪያድጉ ነፃነቱ አለና በተስፋ ገብረሥላሴ ማተሚያ ቤት እየሠሩ ሁለት ወንድ ልጆች እና አንድ ሴት ልጅ ወልደው አሳደጉ::

ወይዘሮ ፅጌ ስለተስፋ ገብረሥላሴ ሲናገሩ፤ ቀኝ አዝማች ተስፋ ሕይወታቸው ሥራ እና ሥራ ብቻ ነበር:: ለመሠረተ ትምህርት ፊደል በነፃ አትመው ይሰጡ ነበር:: ለትምህርት ሚኒስቴርም ብዙ መፅሃፍ ያትሙ ነበር:: የሃይማኖት መፅሃፎችን በተለይም የፀሎት መፅሃፍ ሥርዓቱን እንደጠበቀ እንዲሠራ አድርገው እስከ አሁን እንዲቆይ መሠረት የጣሉ ትልቅ ባለውለታ ናቸው ይላሉ:: በመጨረሻም ወይዘሮ ፅጌ እኚህ አባት መረሳት የለባቸውም መሥሪያ ቤቱም ከመፍረስ ይልቅ አድጎ ሰፊ ቦታ ላይ ትልቅ ሆኖ መገንባት እንዳለበት ተናግረዋል::

# ባህልና ቱሪዝም

## የቡና ቱሪዝም- ያልተገለጠው ዘርፍ ምን በረከት ይዞ ይሆን?

**ዳግም ከበደ**



ኢትዮጵያ የምታመርተው ቡና በወጪ ንግድ ከሚያስገኘው ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ በተጨማሪ በቱሪዝም ዘርፍ ሀገሪቱን ለማስተዋወቅ ግዙፍ አቅም እንዳለው ይነገራል። በዘርፉ ዘለግ ያለ ልምድ ያላቸው ምሁራን ‹‹የቡና አመራረት ዘዴን ከውብ ባህላዊ የቡና አፈላል ጋር አዛምዶ በዓለም አቀፍ ደረጃ ማስተዋወቅ›› አዲስ የቱሪዝም መስህብ እንደሚፈጥር ይናገራሉ። የቱሪስት ፍሰቱን በመጨመር ኢትዮጵያን በአዲስ መንገድ በማስተዋወቅ ረገድም የላቀ ድርሻ መያዝ እንደሚችል ይገልፃሉ።

የቡና መገኛ በሆነችው ኢትዮጵያ ልዩ ጣዕም ያለውን ቡና እንደ አንድ የቱሪዝም መስህብ ለመጠቀም የተለያዩ ሙከራዎች መደረጋቸውን መረጃዎች ያመለክታሉ። ይሁን እንጂ ዘላቂ በሆነና በተደራጀ መልኩ ተግባራዊ አለመደረጉ እንደ አንድ ክፍተት ይነሳል።

ከሰሞኑ ይህንን የኢትዮጵያን እምቅ አቅም ለመጠቀም እንዲሁም ሄድ መለስ እያለ የሚታየውን ሙከራ በዘላቂነት አስቀጥሎ ውጤት ለማምጣት የሚያስችል እቅድ የኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽን እና የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን በጋራ ይፋ አድርገዋል። እቅዱ የኢትዮጵያን ቡና ከግብይት ባሻገር በትብብርና በቅንጅት በቱሪዝም ዘርፍም ሀገሪቱን ለማስተዋወቅ እንዲችል ለማድረግ መሥራት ነው። ይህንን እቅድ ተግባራዊ ለማድረግ ሁለቱ አካላት ከሰሞኑ የመግባቢያ ስምምነት ተፈራርመዋል።

የቡናና ሻይ ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር አዱኛ ደበላ (ዶ/ር ) ስምምነቱን አስመልክቶ እንደተናገሩት፤ የኢትዮጵያ ቡና ከምርት እስከ ግብይት ባለው ሂደት የሀገርን ገፅታ በመገንባት ለቱሪዝም ዘርፉ መኅልበት ትልቅ ሚና ይኖረዋል። ከኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽን ጋር የተደረገው የመግባቢያ ስምምነት ሰነድ ቡናን ከቱሪዝሙ ዘርፍ ጋር በማስተሳሰር የቱሪስት መስህብ ማድረግን ያለመ ነው።

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ገለፃ፤ በዚህም በኢትዮጵያ የተለያዩ የቡና ዝርያዎችን በምርምር በማግኘት ምርቱን ለማሳደግ እና የውጭ ምንዛሬ ምንጭ ለማድረግ በትኩረት እየተሠራ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ቡናን ከማስተዋወቅም ባለፈ ለቱሪዝም ዘርፉም ትልቅ ሚና እንዲኖረውና ትስስሩ እንዲጠናከር የማድረግ ሥራ ተገግባራዊ ይደረጋል። ቡና በጥራት ተመርቶና እሴት ተጨምሮበት ለዓለም ገበያ እንዲቀርብ የማድረጉን ሥራ ከቱሪዝም ዘርፍ ጋር ለማስተሳሰር ይሠራል።

‹‹በቡና ተክል ልማት ውስጥ ሎጆችን እና መዝናኛ ሥፍራዎችን በመገንባት ቡና የቱሪስት መስህብ ይደረጋል›› ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ባለፈው በጀት ዓመት ከቡና ከአንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን ዶላር በላይ ገቢ መገኘቱን ይናገራሉ። የቱሪዝም ዘርፉን ከቡና ምርትና ግብይት እንዲሁም ከኢትዮጵያ ባህላዊ የአፈላል ሥርዓት ጋር ማስተሳሰር ከተቻለ ከሀገር ገፅታ ግንባታ ባሻገር ኢኮኖሚያዊ አማራጭን ማስፋት እንደሚቻል አስረድተዋል።

‹‹የመግባቢያ ስምምነቱ ምን ማእቀፎች ይኖሩታል? የኦሮሚያ ክልል ቱሪዝም ኮሚሽንስ በዚህ በኩል ምን ድርሻ አለው?›› የሚል ጥያቄ ያቀረብንላቸው የክልሉ ቱሪዝም ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነሩ አቶ ነጋ ወዳጆ በሰጡት ምላሽ ቡና ኢትዮጵያ ውስጥ መገኘቱን ጠቅሰው፣ ከአራት ሺህ በላይ ጣዕምና ዝርያዎች እንዳሉትም ገልጸዋል። ከዚህ ውስጥ ጥቂቱ ብቻ እየተመረተ ወደ ገበያ እየቀረበ መሆኑን አመልክተው፣ ምርቱም በዓለም ተወዳዳሪ ብቻ ሳይሆን መሪና ተመራጭ እንደሆነም ተናግረዋል።

‹‹ትልቅ ተቀባይነት ያለውና ባለ ልዩ ጣዕም የሆነውን የኢትዮጵያን ቡና የቱሪዝም አካል ለማድረግ አልተሠራም›› የሚሉት ምክትል ኮሚሽነሩ፤ ቡናን ከኢትዮጵያ ወስደው በማብቀል ተወዳዳሪ የሆኑ ሀገራት ግን በቡና ቱሪዝም ላይ በስፋት በመሥራት ተጠቃሚ መሆናቸውን ይገልፃሉ። ይህንን እውነታ መቀየር እንደሚያስፈልግና ኢትዮጵያም የዚህ ድርሻ ተጋሪ መሆን እንደሚገባት አመልክተዋል።

አቶ ነጋ እንዳሉት፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ቱሪዝምን ከአምስቱ ዋና ዋና የኢኮኖሚ ምሰሶዎች ውስጥ አንዱ በማድረግ የፖሊሲ ማሻሻያ አድርጓል፡፡ በዚህም ለዘርፉ ትልቅ ትኩረት ተሠጥቷል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተገነቡ ያሉ የቱሪስት መዳረሻዎች እና የቱሪዝም መሠረተ ልማቶችም ይህንን ልዩ ትኩረት የሚያጎሉ ለዘርፉ መነቃቃት የሚፈጥሩ ናቸው ይህም በዓለም ላይ ካሉ የመስህብ ቦታዎች ኢትዮጵያ ቀዳሚ ተመራጭ እንድትሆን እድል ይፈጥራል። ይህን ታላቅ ተግባር በቡና ቱሪዝም ለመድገምና ኢትዮጵያ ያላትን እምቅ አቅም ለማስከፈት መሞከር ይኖርባታል።



የኢትዮጵያ አየር መንገድም በዓመት በርካታ ሚሊዮን ተጓዦችን የሚያስተናግድ የአፍሪካ ኩራት ሆኖ እያለ ኢትዮጵያ ግን በሚፈለገው ልክ ከቱሪስቶች ተጠቃሚ መሆን አልቻለችም ያሉት አቶ ነጋ፤ አየር መንገዱን ተጠቅመው እንደ ኬንያ፣ ሞዛምቢክ፣ ታንዛኒያ፣ ዛንዚባር፣ ዚምቧቤ፣ ዛምቢያና ደቡብ አፍሪካ ያሉት ሀገሮች ተጠቃሚ መሆናቸውን ጠቅሰዋል። እነዚህ ሀገራት የኢትዮጵያ አየር መንገድ የሚያመላልሳቸውን ቱሪስቶች ተጠቅመው የቱሪዝም ዘርፋቸውን ማላቃቸውን ጠቅሰው፣ በተቃራኒው ኢትዮጵያ ዝቅተኛ መጠን ያለው ቁጥር ማስመዝገቧ እንደሚያስቆጭም ይናገራሉ። ይህ የሚሆንበት ምክንያትም ኢትዮጵያ ያላትን መስህብና የተፈጥሮ ሀብት (በዩኔስኮ የተመዘገቡ ቅርሶች እና እንደ ቡና ያሉትን ሀብቶችን) በበቂ ሁኔታ ማስተዋወቅ ባለመቻሏ እንደሆነም ያመለክታሉ።

ምክትል ኮሚሽነሩ እንዳሉት፤ የኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽን ባለፉት ሶስትና አራት ዓመታት ውስጥ ይህንን ችግር ለመቅረፍ ሰፋፊ ሥራዎችን ሲሠራ ቆይቷል። በዚህም የኢትዮጵያን በተለይ የክልሉን የመስህብ ሀብቶች የማስተዋወቅና የማልማት ሥራ እያከናወነ ነው።

ከዚህ ባሻገር በቅርቡ ቡናን በልዩ ትኩረት በማስተዋወቅ፣ መዳረሻዎችን በማልማት እንዲሁም በልዩ ልዩ ምክንያት ኢትዮጵያውያንን እንዲወክል በማድረግ መሥራት ቢቻል ከቱሪዝም ዘርፍ የሚገኘውን ጥቅም ማስፋት እንደሚቻል ታምኖበታል። ይህንን እቅድ መሬት ለማውረድ እየተሰራ ይገኛል፡፡

‹‹የኦሮሚያ ክልል አብዛኛዎቹ ዞኖች ቡና አብቃይ ናቸው›› የሚሉት ምክትል ኮሚሽነሩ፤ እስከ 70 በመቶው የሚሆነው የኢትዮጵያ የቡና ምርት የሚገኘው ከዚሁ ክልል መሆኑን ይገልፃሉ። ከዚህ ባሻገር ቡና አብቃይ የሆኑት አካባቢዎች ያላቸው ተፈጥሮና መልከዓምድራዊ አቀማመጥ ውበት ልዩ መሆኑን ይናገራሉ። በመሆኑም እነዚህን ሀብቶች ከቡና ጋር አስተሳስሮ በቱሪዝም ዘርፉ ቢሠራ የሚፈለገውን ውጤት ማምጣትና ሀገሪቱ ከዘርፉ የምታገኘውን ጥቅም ማሳደግ እንደሚቻል ያስረዳሉ። ኮሚሽኑም ይህንን ታሳቢ ያደረገ እቅድ በማውጣት ተግባራዊ ለማድረግ እየሠራ መሆኑንም ይገልፃሉ።

የቡና አምራቹ አርሶ አደር አዲስ የኑሮ ዘይቤ እንዲጀምር መሥራት ያስፈልጋል የሚሉት ምክትል ኮሚሽነሩ፣ ቡና ከማምረት ባሻገር በማሳ ውስጥ የሚተገበረውን ሙሉ ሂደት ለቱሪስቱ ማስጎብኘት እንዲችል፤ ከቡና እርሻ ጀምሮ፣ ለቀማውን፣ መፈልፈሉንና ማድረቁን ጨምሮ ተፈልቶ ለመጠጥ እስኪውል ድረስ ያለው ሂደት ለጉብኝት በመከፈት ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ እንደሚያስፈልግም ይገልፃሉ።

ከቡናና ሻይ ባለሥልጣን ጋር የተፈራረመው ስምምነትም ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል መሆኑን ያነሳሉ። ከቡና ምርት ባሻገርም የሻይ ቅጠል አብቃይ አካባቢዎች ታሳቢ ያደረገ እቅድ መኖሩን ጠቁመዋል። በክልሉም ወደ 30 ሺህ ሄክታር በሚሆን መሬት ላይ ሻይ እየለማ መሆኑን ማሳ እየለማ መሆኑን አንስተው ቱሪዝሙ ይህንን ያካተተ እንደሚሆንም ገልፀዋል።

እንደ አቶ ነጋ ገለፃ፤ የቡናና ሻይ ግብይት በባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ በኩል የሚያልፍ ነው። በዓለም አቀፍ ደረጃ የኢትዮጵያን ቡና እና ሻይ በሚገበያዩበት ጊዜ ምርቱን ለሸያጭ ከማቅረብ ባሻገር ኢትዮጵያን በቱሪዝም በማስተዋወቅ በኩል ያለውን አቅም እንዲጠቀሙ የሚያስችል ስምምነት ተደርጓል። ባለሥልጣኑ ከግብይቱ ባሻገር በቡናና ሻይ ልማት ላይ ትልቅ ደርሻ ያለው በመሆኑ ከመሠረተ ልማት፣ ከሎጅ፣ በቡና ማሳ ውስጥ ለጎብኚዎች ምቹ የአገልግሎት መስጫ መዳረሻዎችን ከማልማት አኳያ በጋራ ድጋፍ አድርጎ በመሥራት የበኩሉን መወጣት ይችላል። የኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽንም የክልሉን የቡና ቱሪዝም ከማስተዋወቅ አንፃር በቅንጅት አብሮ ለመሥራት ተዘጋጅቷል።

የቡና ቱሪዝም ዋናው ባለቤት ከትንሽ አስከ ትልቅ የእርሻ ማሳ ያላቸው አርሶ አደሮችና ባለሀብቶች ናቸው የሚሉት አቶ ነጋ፤ ዋናው ተግባር የሚሠራውም በባለቤቶቹ መሆኑን ይገልፃሉ። ህብረተሰቡን የማንቃት፣ አዳዲስ የቱሪዝም ኢንቨስትመንት ላይ ይህን መሰል ሃሳብ መኖሩን የማሳየት ሃላፊነቱን ኮሚሽኑና የባለሥልጣን መሥሪያቤቱ ሃላፊነት ወስደው እንደሚሠሩም ያስረዳሉ።

የኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽን የቡና ቱሪዝም ተግባራዊ የሚደረግባቸው የክልሉ አካባቢዎችን መለየቱን ምክትል ኮሚሽነሩ አቶ ነጋ ይገልፃሉ። 70 በመቶ የሚሆነው ቡና ከዚሁ ክልል የሚገኝ እንደመሆኑም በርካታ ለቱሪዝም መስመር የሚሆኑ አካባቢዎች መኖራቸውን ይገልፃሉ። በተጨማሪ የቡና አብቃይ በሆኑ አካባቢዎች በሙሉ የቡና ቱሪዝም ማካሄድ እንደሚቻልም ያስረዳሉ።

መነሻቸውን ከአዲስ አበባ የሚያደርጉ ጎብኚዎች በደቡብ ምእራብ በኩል በወሊሶ አድርገው፣ በጅማ፣ ቡኖ በደሌ፣ ወደ ሊሙ አሊያም ወደ ኢሉ ባቡር መሄድ እንደሚችሉ እና የቡና ማሳዎችን፣ የአፈላል ሥርዓቱን እንዲሁም የተፈጥሮ ውበትና መልከዓ ምድሩን መመልከትና የማይረሱ ትዝታዎችን ገብይተው መመለስ እንደሚችሉ አቶ ነጋ ይናገራሉ። ከዚህ በተጨማሪ ሌሎች የቡና ቱሪዝም መስመሮች መኖራቸውን ገልፀው፣ ጉጂንና ሲዳማን ማስተሳሰር እንደሚቻል ያስረዳሉ። የሀገር ወስጥም ሆነ ዓለም አቀፍ ቱሪስቶች በእነዚህ አካባቢዎች የቡና ቱሪዝም በስፋት ማግኘት እንደሚችሉም ይገልፃሉ።

አቶ ነጋ ሌላው ቡና አብቃይ የሆነው የክልሉ አካባቢ ‹‹ነን ሰቡ›› የሚባለው ቦታ መሆኑን ጠቅሰው፣ ጎብኚዎች በዚያ አድርገው ወደ ባሌ በመሻገር ትልቅ የቡና ጫካ ወዳለበት አረና፣ ደሎ መና አካባቢ ማራኪ ጉብኝት ማድረግ እንደሚችሉ ይገልፃሉ።


ሀረር የቡና ሀገር መሆኑን ጠቅሰው፣ ከኢሉ አባቦር፣ ከጋምቤላ ጀምሮ ወደ ሀረር ሲኬድ ኢትዮጵያን በሁለት አቋርጦ መሄድ የሚችል የቡና ቱሪዝም መስመር መዘርጋት እንደሚቻል ያነሳሉ። በክልሉም ሆነ ከክልሉ ውጪ በርካታ የቡና አብቃይ አካባቢዎች እንዳሉ አመልክተው፣ እነርሱን በማስተሳሰር ግዙፍ አዲስ የቱሪዝም የጉብኝት መዳረሻ መፍጠር እንደሚቻልም ይገልፃሉ። ጎብኚውም ልዩ ልዩ ባህል፣ የኑሮ ዘይቤን እንዲሁም መልከዓ ምድርን እየተመለከተ ከተፈጥሮ ጋር ራሱን በማስተሳሰር የማይዘነጋ ትዝታን ቋጥሮ መመለስ እንደሚችል ነው የገለፁት።

ምክትል ኮሚሽነሩ ፤የመገናኛ ብዙሃን ኢትዮጵያ ከዘርፉ ተጠቃሚ እንድትሆን፣ ማህበረሰቡም ቡናን ከማምረት ባሻገር ያልተገለጠ የቱሪዝም እድል መኖሩን እንዲያውቅ ግንዛቤ የመፍጠር፣ የማስተዋወቅ ሃላፊነታቸውን እንዲወጡ ጥሪ አቅርበዋል። ይህን በትብብር ማድረግ ሲቻል የሚፈለገውን ውጤት በአጭር ጊዜ ማሳካት ቀላል እንደሚሆን ገልፀዋል።

# ሳምንቱን በታሪክ

## አንድ አምሳል፤ በአንድ ቀን

**ዋለልኝ አየለ**



ዳግማዊ አጼ ምኒልክ



እቴጌ ጣይቱ

እነሆ ዛሬ 180ኛ ዓመት ተቆጠረ:: ከ180 ዓመታት በፊት ልክ በዛሬዋ ቀን ነሐሴ 12 ቀን 1836 ዓ.ም የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የነበሩት ዳግማዊ አጼ ምኒልክ ተወለዱ:: አጼ ምኒልክ ከኢትዮጵያ ነገሥታት ሁሉ ስማቸው ጎልቶ ይጠቀሳል:: አንዱና ዋናው የዓድዋ ድል ነው:: ይህ ዓለም አቀፍ ዝና አስገኝቶላቸዋል:: የጥቁር ሕዝብ ሁሉ የነፃነት ተምሳሌት የሆነው ዓድዋ በአጼ ምኒልክ የሚመራ ነበርና የጥቁር ሕዝብ የጀግና ተምሳሌት አድርጓቸዋል::

የዛሬው ሳምንቱ በታሪክ ድንቅ የታሪክ ግጥምጥሞሽ ያለበት ነው:: ይሄውም በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ጎልተው የሚታወቁት አጼ ምኒልክ እና ባለቤታቸው በአንድ ቀን የተወለዱ መሆናቸው ነው:: በኢትዮጵያ ሀገረ መንግሥት ምሥረታ ውስጥ ከፍተኛ ሚና ያላቸውን ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ አጼ ምኒልክ እና ባለቤታቸውን እቴጌ ጣይቱን ያስታውሰናል:: ባልና ሚስት በሃይማኖታዊ አገላለጽ ‹‹አንድ አካል አንድ አምሳል›› ይባላሉ፤ አንድ ናችሁ ለማለት ነው:: የዳግማዊ አጼ ምኒልክና የእቴጌ ጣይቱ ባልና ሚስትነት ይህን አገላለጽ ያሟላል:: አንድ አካል አንድ አምሳል ሆነው አንዲት ሀገር ገንብተዋል:: አንዲት ኢትዮጵያን አጽንተዋል:: ዓድዋን የሚያክል ዓለም አቀፍ ግዙፍ ድል አስመዝግበዋል:: ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር የጥቁር ሕዝብ የነፃነት ተምሳሌት እንድትሆን አድርገዋል:: የእነኝህ ንጉሥና ንግሥት ታሪካዊ ግጥምጥሞሽ ደግሞ የተወለዱበት ቀን ተመሳሳይ መሆኑ ነው:: የዓመተ ምህረት ልዩነት ቢኖረውም ሁለቱም ነሐሴ 12 ቀን ነው የተወለዱት:: ይህ ብቻ አይደለም ግጥምጥሞሹ፤ የዓድዋው ጀግና ፊታውራሪ ገበየሁም የተወለዱት ነሐሴ 12 ቀን ነው:: የእቴጌ ጣይቱን እና የዳግማዊ አጼ ምኒልክን ታሪክ ዘርዘር አድርገን እናያለን::

ጣይቱ ብጡል ከ184 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ልክ በዛሬዋ ቀን ነሐሴ 12 ቀን 1832 ዓ.ም ጎንደር ውስጥ ፋርጣ በታሪካዊቷ ደብረ ታቦር ከተማ ተወለዱ:: አባታቸው ደጃች ብጡል ሲሆኑ እናታቸው ደግሞ የደብረ መዊዕ እመቤቷ ወይዘሮ የውብዳር ናቸው:: ‹‹እቴጌ ጣይቱ ብርሃን ዘ ኢትዮጵያ›› በሚል ስም ይታወቃሉ:: የዘር ሐረጋቸውም ከጎንደር፣ ከስሜን፣ ከጎጃምና ከየጁ ወረ ሴህ ይመዘዛል:: በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ወርቃማ ስም ካላቸው ሴት የነገሥታት ሚስቶች አንዷ ናቸው::

እንደነ ረዳት ፕሮፌሰር አበባው አያሌው ያሉ የታሪክ ባለሙያዎች እንደሚሉት፤ እቴጌ ጣይቱ የትውልድ ሐረጋቸው ከብዙ የሰሜን ኢትዮጵያ መሳፍንት ጋር መተሳሠሩ ለንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ አጼ ምኒልክ ምቹ ሁኔታ ፈጥሮላቸዋል፤ ግዛታቸውን ለማደላደል አግዟቸዋል:: የዳግማዊ አጼ ምኒልክ ከእቴጌ ጣይቱ ጋር መጋባት ጠቀሜታው በክብር ብቻ ሳይሆን በፖለቲካም ጭምር ነበር::

በቤተ ክህነት ብዙ መንፈሳዊ ትምህርት፣ ሕግና ሥርዓት የተማሩት እቴጌ ጣይቱ፤ ከዳግማዊ አጼ ምኒልክ ጋር ሚያዚያ 25 ቀን 1875 ዓ.ም በአንኮበር መድኃኒዓለም በቁርባን ጋብቻቸውን ፈጸሙ:: ከዚያ በኋላ የንጉሠ ነገሥቱ ሚስት ብቻ ሳይሆኑ በብዙ ምክሮች ስማቸው የሚጠራ የዳግማዊ ምኒልክ ስኬታማ የአስተዳደር ዘመን ምክንያት ለመሆን በቁ:: ታላቁ የዓድዋ ድል ስኬት የእቴጌ ጣይቱ ብልህነት የተሞላበት ለመሆኑ ዓድዋ በመጣ ቁጥር ሲተረክ የምንሰማው ነው::

ጥንዶቹ አጼ ምኒልክ እና እቴጌ ጣይቱ ንጉሠ ነገሥት እና እቴጌ ተብለው ሲሰየሙ ከተለያዩ የየአካባቢው ገዢዎች ጋር በዲፕሎማሲያዊ መንገድ ጥምረት በመፍጠር አልያም ወታደራዊ አቅም በመጠቀም የበለጠ ግዛታቸውን አስፋፍተዋል።

እቴጌ ጣይቱን በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ስማቸው በተደጋጋሚ እንዲነሳ የሚያደርጋቸው በዓድዋ ጦርነት ጊዜ የነበራቸው ድፍረት እና ብልህነት ነው:: ከጣሊያን ጋር ከተደረጉ ስምምነቶች መካከል ኢትዮጵያን ቅኝ ተገዢ ሊያስደርጋት የነበረው የውጫሌውን ስምምነት ውል አንቀፅ 17 ውድቅ በማድረግ ይታወቃሉ። መቀሌን ተቆጣጥረው የነበሩትን የጣሊያን ወታደሮች ለማሸነፍ እንዲቻል ጣይቱ ባቀረቡት ሃሳብ ይታወቃሉ። በዚህም መሠረት ጣሊያኖች የሚጠቀሙበትን የውሃ ምንጭ በኃይል በመቆጣጠር ከመቀሌ እንዲወጡ ለማስደረግ ተችሏል። ጣይቱ ብጡል ጣሊያኖች በተሸነፉበት እና በድል በተጠናቀቀው የዓድዋ ጦርነት በነበራቸው ሚናም ይታወቃሉ። እቴጌ ጣይቱ ኢትዮጵያን ቅኝ ግዛት ለማድረግ የሞከረውን የጣሊያን ጦር ለመዋጋት በስራቸው 5000 እግረኛ እና 600 ፈረሰኞችን አሰልፈው ነበር።

እቴጌ ጣይቱ ለዚህኛው ዘመን ሴቶች ተምሳሌት ሆነው ይጠቀሳሉ:: ለብዙ ነገሮችም ስያሜ መሆን ችለዋል:: ጣይቱ ማለት ስም ብቻ ሳይሆን ጀግንነት፣ ብልህነት ማለት መስሏል:: ይህ የሆነው በእቴጌ ጣይቱ ነው::

እቴጌ ጣይቱን ታሪክ በሰፊው ያስታውሳቸዋል:: በስማቸው ብዙ ነገሮች ተሰይመዋል:: ብዙ ዘፈኖች ተዘፍነዋል:: ‹‹የኛ›› የሙዚቃ ቡድን በ2006 ዓ.ም ካወጡት የጋራ ዘፈን ውስጥ እነዚህን ስንኞች እናገኛለን::

ኩሩ ንግሥት የሴት አርበኛ
አትንኩኝ ባይ ፍርድ አወቅ ዳኛ
ለነፃነት ፋና የሆነች
ብልህ ጀግና እመቤት ማነች?
ፀሐይ ሆና ሀገር የሞቃት
ፊት አውራሪ ዓለም ያወቃት!

በቴዎድሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ) ‹‹ጥቁር ሰው›› ዘፈን ውስጥ ደግሞ ይቺን ስንኝ እናገኛለን::

የቀፎው ንብ ሲቆጣ ስሜቱ
ከፊት ሆና መራችው ንግሥቲቱ

እቴጌ ጣይቱ ከባለቤታቸው ዳግማዊ አጼ ምኒልክ ሕልፈት አራት ዓመታት በኋላ ባደረባቸው ህመም የካቲት 4 ቀን 1910 ዓ.ም በ78 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፤ ሥርዓተ ቀብራቸውም ራሳቸው ባሰሩት በእንጦጦ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ተፈጽሟል::

### እቴጌ ጣይቱ ብጡል
### ዳግማዊ አጼ ምኒልክ

በኢትዮጵያ የነገሥታት ታሪክ ውስጥ ዳግማዊ አጼ ምኒልክ ትልቅ ቦታ ያላቸው ንጉሥ መሆናቸው ተደጋግሞ ሲነገር የቆየ ነው:: የታሪክ ባለሙያዎች እንደሚሉት አሁን ያለው የኢትዮጵያ ቅርጽ በአጼ ምኒልክ የሀገር ግንባታ ሂደት የተገነባ ነው:: የብልህነትና የታጋሽነት ምሳሌ ይደረጋሉ:: በ1874 ዓ.ም በተደረገው የእምባቦ ጦርነት የጎጃሙ ንጉሥ ተማረኩ፤ ተማርከውም ንጉሥ ምኒልክ ጋ ደረሱ:: የእምባቦ ጦርነት በሸዋው ንጉሥ ምኒልክ እና በጎጃሙ ንጉሥ ተክለሃይማኖት የተደረገ ጦርነት ነው:: ንጉሥ ምኒልክ በትህትና እና በጨዋ ደንብ ሲነግሯቸው ንጉሥ ተክለሃይማኖት ተገረሙ:: ንጉሥ ምኒልክም ንጉሥ ተክለሃይማኖትን ‹‹አንተ ብትሆን ምን ታደርገኝ ነበር?›› ሲሉ ጠየቋቸው:: ንጉሥ ተክለሃይማኖትም ስሜታቸውን አልደበቁም:: ‹‹ጠላት ሆነን እየተዋጋን ነው፤ አልዋሽህም እኔ ብሆን እገልህ ነበር›› በማለት ንጉሥ ምኒልክን ‹‹አንተማ እናት ነህ!›› አሏቸው:: ‹‹እምዬ ምኒልክ›› የሚለው የዳግማዊ አጼ ምኒልክ ቅጽል ስም የመጣው በዚህ ምክንያት ነው ይባላል::

እኚህ የኢትዮጵያ ታላቅ ንጉሥ ዳግማዊ አጼ ምኒልክ የተወለዱት ከዛሬ 180 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ከአባታቸው ንጉሥ ኃይለመለኮት ሳህለሥላሴ እና ከእናታቸው እጅጋየሁ ለማ ነሐሴ 12 ቀን 1836 ዓ.ም በሸዋ አንኮበር አንጎለላ ነው:: አካባቢውም አንጎለላ ኪዳነ ምህረት ይባላል:: ቦታው ዛሬ ድረስ ዓድዋ በመጣ ቁጥር ጉብኝት ይደረግበታል::

ዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስ ሸዋን ለማስገበር ከጎንደር ወደ ሸዋ በሄዱበት ወቅት ንጉሥ ኃይለመለኮት ታመው ሲሞቱ፤ ንጉሠ ነገሥቱ ልጅ ምኒልክን ወደ መቅደላ ይዘዋቸው ተመለሱ:: ከስምንት ዓመታት ቆይታ በኋላ፣ በ1857 ዓ.ም ልጅ ምኒልክ ከመቅደላ አምልጠው ሸዋ ገቡ፤ የአባታቸውን የንጉሥ ኃይለመለኮት ሳሕለሥላሴን አልጋ ወረሱ:: ጥቅምት 25 ቀን 1882 ዓ.ም ደግሞ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሆኑ:: ዳግማዊ አጼ ምኒልክ በንግሥና ዘመናቸው የሠሯቸው ዓለም አቀፋዊና የሀገር ውስጥ ሥራዎች በየታሪክ አጋጣሚው የሚነገሩ ናቸው::

ዳግማዊ አጼ ምኒልክ ባደረባቸው ህመም ታህሳስ 3 ቀን 1906 ዓ.ም በ69 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፤ ሥርዓተ ቀብራቸውም ራሳቸው ባሰሩት በባዕታ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ተፈጽሟል::

በዚሁ ቀን የተወለዱት ፊት አውራሪ ገበየሁ ሌላኛው የዚህ ሳምንት የታሪክ አካል ናቸው:: የንጉሠ ነገሥቱ የመሐል ጦር አዛዥ የነበሩት ፊታውራሪ ገበየሁ ከጣልያኖች ጋር በተደረጉ በሁሉም ጦርነቶች ጀግንነታቸውን ያስመሰከሩ ሀገር ወዳድ ሰው ነበሩ:: ዋነኛው የኢትዮጵያና የኢጣሊያ ጦርነት ዓድዋ ላይ ከመካሄዱ ቀደም ብሎ አምባላጌ ላይ በተደረገው ውጊያ የአምባላጌውን ምሽግ በመስበር በጣሊያን ላይ የመጀመሪያውን የድል ደወል ያሰሙትና ዋናው የድሉ ባለቤት እርሳቸው ነበሩ:: በዚህም ምክንያት በወቅቱ የፈረንሳይ ጋዜጦች ‹‹የአምባላጌው የኢትዮጵያ ጀግና›› በማለት እንዳወደሷቸው አንጋፋው የታሪክ ፀሐፊ ተክለፃዲቅ መኩሪያ ጽፈዋል::

ፊታውራሪ ገበየሁ ገና ወደ ዓድዋ ሲዘምቱ ‹‹ስሸሽ ከኋላዬ ከተመታሁ አሞራ ይብላኝ፤ ከፊት ለፊት ስፋለም ከወደቅሁ ግን ሬሳዬን አፅሜን ትውልድ ቦታዬ ውሰዱልኝ›› በማለት ተናዘውም ነበር ይባላል:: ይህ ንግግራቸውም ዓድዋ በመጣ ቁጥር ይነገራል:: ከጠላት ጋር በፅናት ሲፋለሙ ስለ ሀገራቸው ነፃነት ዓድዋ ላይ ወደቁ:: በኑዛዜያቸው መሠረትም ከሞቱ ከሰባት ዓመት በኋላ አፅማቸው ወደ ትውልድ አካባቢያቸው አንጎለላ ኪዳነ ምህረት ቤተ ክርስቲያን ተወስዶ እዚያው አረፈ::


የዓድዋ ሥላሴን ጠላት አረከሰው
ገበየሁ በሞቴ ግባና ቀድሰው!

ተብሎም የተገጠመላቸው ለዚህ ጀግና ነው::

ዳግማዊ አጼ ምኒልክ እና እቴጌ ጣይቱ በየዓመቱ ነሐሴ 12 ቀን ዳግማዊ ምኒልክ አደባባይ (ፒያሳ) በሚገኘው ጣይቱ ሆቴል የመታሰቢያ ፕሮግራም ሲዘጋጅላቸው እንደነበር ይታወሳል:: እነሆ በአንድ ቀን የተወለዱትና አንዲት ኢትዮጵያን አጽንተው ያቆዩት ባልና ሚስቱ በታሪክ ሲታወሱ ይኖራሉ::

# የዝነኞች ገጽ

## ነቢይ በሀገሩ



**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

ያውና እዚያ ማዶ
ብርሃን ያድላሉ፤
አሁን እኔ ብሄድ
አለቀ ይላሉ::

❖ ❖ ❖ አለ ባለቅኔው ነቢይ:: በቃላት መንገድን መሥራትና ማበጀትም ያውቃልና ደግሞ “ነገም ሌላ ቀን ነው” ሲል ከሠራት መንገድ ፊት ቆሞ ሩቅ እያየ እሩቅ ተመኘ:: በዳግም ተስፋ ልቡ ላይ የተንጠለጠለችው ይህቺ ሌላ ቀንም ሌላ ነገር ነበራት:: ምን ይዛ እንደምትመጣ ግን ነቢይም ሆነ ሌላ ማንም ሊያውቀው የሚችል አልነበረም:: ታዲያ ነቢይ ግን ማነው? ... ነቢይ ሲሉ እሱ እንደ ኤሊያስ፤ አሊያም እንደ ኢሳያስ ያለ አልነበረም:: ምናልባት “ነቢይ በሀገሩ አይከበርም” የሚለውን አብረው ይጋሩ ይሆናል እንጂ:: ምናልባትም ይህ ነቢይ በጥበብ ለምድር ከተጠሩ ነቢያት መካከል አንደኛውና ፊተኛው ... ልንልም እንችል ይሆናል:: በእርግጥም ደግሞ ነው:: ይኼ ነቢይም ታላቁና ሁለገቡ የጥበብ ሰው ነቢይ መኮንን ነው:: ሀገሩን ወዳድ የጥበብ ሰው ካሉ እርሱ ነው:: የጥበብ ሰው ሀገሩን ሲወድስ እንዴት ነው? ቢሉ ልክ እንደርሱ ነው:: እርሱስ? ካሉ ደግሞ ... እርሱ ሁሉም ነገሩ ከሀገሩ ወደ ሀገሩ ... ስለሀገሩ ነው:: ኢትዮጵያዊነት መልክ አለው:: የኢትዮጵያን መልክ ይዞ፣ መልኳንም ለብሷል::

ነቢይ መኮንን ሃሳብና የቃላት ውጥር ውጥን የማያልቅበት ገጣሚ ነበር:: ከብዕር ጋር የቆመ ጋዜጠኛም ጭምር ነበር:: በትያትር ዓለም ውስጥ የተንቈለለ ጸሀፊም ነው:: የሙዚቃ ግጥም ደራሲነትም ይነካካዋል:: ሰዓሊ፣ ያውም የረቂቅ ሰዓሊነትም አለበት:: ሳይበቃውም ተርጓሚና አርታኢም ነው:: በርከት ያሉ መጻሕፍትን ጽፎ ለንባብ ወግ ማዕረግ አብቅቷል:: ብቻ ምን አለፋችሁ፣ ነቢይ "አይደለም" የሚባለው ነገር የለውም:: በዚህም ሆነ በዚያ ሲያልፍ፣ ስለዚህም ሆነ ስለዚያ ሲጨነቅ፤ ከእርሱ ጭንቀትና ውጥረት ፊት ሁሌም ስለ አንዲት ሀገሩ ነበር:: በብሶትም ሆነ በደስታ፣ በትዝታም ሆነ በመከፋት፣ በወኔም ቢሉ በቁጭት ውስጥ ሆኖ ለሀገሩ ስንኝ ያልቋጠረላት ገጣሚ ባይኖርም፤ ነቢይ መኮንን ግን የእነዚህ ሁሉ አውራ አድርጎታል:: በዚህ ነገሩም ከብዙ ገጣሚያን ለየት የሚያደርገው አንድ ነገር አለው:: ይኸውም ስለሀገሩ የገጠማቸው ግጥሞች በቁጥር ከ20 ያለፉ መሆናቸው ነው:: ነቢይ በሀገሩ ገጣሚ ነው:: ልቡን አሸፍቶ፣ ቀልቡን ሰውሮ የሚገጥመውም ስለሀገሩ ነው:: ገጣሚነቱ እንኳንስ የግጥም አንባቢያኑን ቀርቶ ለገጣሚያኑም የሚያስቀና ነው:: ብዕራቸውን እያነሱም ሆነ አንደበታቸውን እየከፈቱ ስለ እርሱና ስለ እርሱ ግጥሞች ማውራት ለብዙ ገጣሚያን አስደሳቹ ነገር ይመስለኛል:: በተለየ መንገድ ደግሞ ስለ ሀገራዊ ግጥሞቹ ብዙ ብዙ ይሉለታል::

ነቢይን ቀርቦ ለሚመለከተው ስለ እርሱ ባህሪ በመጀመሪያ የሚያጤነው ነገር፤ ነቢይ ያለ ብዕርና ወረቀት መታየት የማይችል መሆኑን ነው:: አፍታ ብዕሩ ቢለየው ያቁነጠንጠዋል:: ጭንቅ ጭንቅ ይለዋል:: ይኼ ሰው ታዲያ በአንድ ወቅት ብዕርና ወረቀትም ሆነ መጻሕፍት ከሌሉበት ዘብጥያ ወረደ:: ጊዜው በደርግ ዘመነ መንግሥት ሲሆን የታሠረውም የዚያ መከረኛ "የኢህአፓ አባል ነህ" በሚል ጦስ ነበር:: እናም ጸረ አብዮተኛ ነህ ተብሎ ከአንደኛው የእስር ቤቱ ክፍል ተወረወረ:: በዚያም ሆኖ ወዲህ ወዲያ ይንጎራደዳል:: በሃሳቡ ነገር እያወጣ ያወርዳል:: ከሃሳቡ ውስጥ ቱር! ቱር! የሚልበት ነገርም "ለምንስ ታሰርኩ ... እንዴትስ ነው ከእስር የምፈታው?" እያለ ሳይሆን፤ "እንዴት አድርጌ፣ በምን መላ መጻፊያ ወረቀት ላግኝ?" እያለ ነበር:: ልማዱን ያጦዘበት ደግሞ ከኪሱ ውስጥ ብዕር መኖሩ ነበር:: ቀንበር ያለ ማረሻ ዋጋ አልነበረውምና የወረቀቱ መገኘት የግድ ነበር:: ግራ ቀኙንም ተመለከተ:: እስር ቤቷም በተአምራዊ ችሮታዋ ወረቀት እንድትሰጠው በዓይኖቹ ተማጸናት::

ድንገት አንድ የሲጋራ ፓኮ ከዓይኑ ሲገባ አንድ ሃሳብ ብልጭ አለለትና ከመሬቱ ላይ አንስቶ ላጠው:: ከብዕሩም ጋር አገናኘው:: ቀና ብሎም በሌላኛው እጁ ላይ የያዘውን መጽሐፍ ተመለከተ:: ርዕሱ “Gone with Wind” ይላል:: መጽሐፉም የእውቋ አሜሪካዊት ደራሲና ጋዜጠኛ፣ የማርጋሬት ሚሼል መጽሐፍ ነበር:: ሃሀሳቡን ከብዕርና ቁርጥራጭ ወረቀት ጋር አድርጎ ይተረጉመው ጀመረ:: በዚሁ የሲጋራ ወረቀት ሲሞነጫጭር ላየ ሥራ የፈታ ቄስ ነበር የሚመስለው:: ነቢይ ግን እንዲችው እንደተፏከተ ተርጎሞ ጨረሰው:: ሰው ከአካላዊ እስር ውስጥ ሲገባ ከመንፈሳዊው አዕምሮው ጋር ይጣበቃልና ነቢይ ከእስር ቤቱ ውስጥ ሆኖ የምናብ ቡረቃ ውስጥ ገብቶ ነበር:: የትርጉም ሥራውንም “ነገም ሌላ ቀን ነው” በሚል ስያሜ ተረጎመው:: የውጭውን ነገረ ዓለም ሁሉ እረስቶ እስር ቤቱን እንደ ግል ቢሮው ተጠቀመበት:: በሥራ ተጠምዶ በምናብ እንደተዘፈቀ ብዙ ማዕልትና ሌቶች አልፈው አሥር ዓመታት ተቆጠሩ:: ከአሥርት ዓመታት በኋላ ሲወጣም ከእስር ተፈቶ ሳይሆን ከአንድ ሌላ የተመስጦ ዓለም ውስጥ ከርሞ የመጣ ነበር የሚመስለው:: ይህን አስገራሚ ታሪኩን የሰማች አንዲት አሜሪካዊት ጋዜጠኛም በ1990ዎቹ መካከል ወደ ኢትዮጵያ መጥታ ቃለመጠይቅ አድርጋው ነበር::

“Gone with Wind” ስለዚህ መጽሐፍ ሳስስ አንድ የገረመኝን ሌላ ነገር አገኘሁ፤ ይኸውም የዚህ መጽሐፍ ደራሲ የሆነችው ማርጋሬት ሚሽል እና ተርጓሚው ነቢይ መኮንን፤ ሁለቱንም የሚያመሳስሉ ብዙ ነገሮች መኖራቸው ነው:: የመጀመሪያው ነገር ማርጋሬት ሚሽልም እንደ ነቢይ ሁሉ ጋዜጠኛ ነበረች:: መጽሐፉን ለመጻፍ ያበቃት አጋጣሚ በአንድ ወቅት እግሯን ታማ ከቤት መዋል በጀመረችበት ሰሞን ላይ ነበር:: ነቢይ ሲተረጉመው ደግሞ ከእስር ቤት በመግባቱ ነበር:: መጽሐፉን ለመጻፍ ስትነሳ መነሻ የሆናት የሀገሯ፤ የአሜሪካ በርስ በርስ ጦርነት ውስጥ መተራመስ ነበር:: በዚያን ሰሞን የነቢይ ሀገርም በአብዮታዊና በሀገራዊ ጦርነቶች የተከበበችበት የነበረ መሆኑ ነው:: ማርጋሬት ሚሽል የፖለቲከኞቹን ሴራ እየነቀሰችና እየነቀፈች በገጸ ባህሪያት አላብሳ ታፍረጠርጠዋለች:: ልክ የኦሮማይን ዓይነት ዳራ የነበረው ነው:: ታዲያ ይህን መጽሐፍ ለመጻፍ የፈጀችው 10 ዓመታትን ነበር:: ነቢይ ደግሞ ከታሰረበት እስር ቤት ለመውጣት አሥር ዓመታትን ጠብቋል:: የተተረጎመው መጽሐፍም በ1980ዎቹ አጋማሽ ላይ ለንባብ ቢበቃም ዳሩ ግን ባጠላበት ግዙፍ የሳንሱር ጥላ ምክንያት ከውስጡ ብዙ ነገሮች እንዲጎማመዱበት ሆነ:: በወቅቱ ለነበረው የኢትዮጵያ ፖለቲካ እንደ ዘንዶ አስፈሪ ሆነው የታዩ ነገሮች በሙሉ ከመጽሐፉ ላይ ተነቅለው እንዲወጡ በመደረጉ ሙሉእነት አልነበረውም:: ቢሆንም ግን በጣም ተወዳጅና በብዙ የተዋጣለት የትርጉም ሥራ እንደነበረ አይካድም::

የነቢይ አበርክቶዎች ለመስማት ባይታክቱም ለመቁጠር ግን ሳያዳግቱ አይቀሩም:: የሆነው ሆነና ከ2 ዓመታት በፊት ነቢይ ሦስት መጻሕፍትን በአንድ መድረክ ላይ አስመርቆ ነበር:: እነዚህም “የኛ ሰው በአሜሪካ”፣ “ነገም ሌላ ቀን ነው”፣ እና “የመጨረሻው ንግግር” ናቸው:: “ነገም ሌላ ቀን ነው” ከዚህ ቀደም ታትሞ ለንባብ የበቃ ቢሆንም፤ በሳንሱር የታጨዱትን የመጻሕፍቱን ገሚስ አካላት አክሎ በድጋሚ ለማሳተም ችሏል:: ተርጉሞ ለእይታ ካበቃቸው ተውኔቶች መካከል “ጁሊየስ ቄሳር” አይረሴው ነው:: ደግሞም ነቢይ መኮንን የሙዚቃ ግጥምም ይነካካዋል ብለናል:: ሲነካም ያውም ጫን፣ ጠብሰቅ አድርጎ ነው:: ከሠራቸው የሙዚቃ ግጥሞች መካከል አንዱ የንዋይ ደበበ “እንኖራለን ገና” የተሰኘው ግሩም ሙዚቃ ነው:: አንጋፋው ነቢይ መኮንን እንደ ጋዜጠኝነት በሙያው ካገለገለባቸው ስፍራዎች አንዱ አዲስ አድማስ ጋዜጣ ነበር:: ከጋዜጣው መሥራቾች መሀከልም አንደኛውና ቁልፉ ሰው እሱ ነበር:: አልፎም የጋዜጣው ዋና አዘጋጅ በመሆን መርቷል:: መምራት ብቻም አይደለም፤ እጅግ ጠለቅ ያሉ ሃሳቦችን እያነሳ በርካታ ጽሁፎችንም ዘርቶበታል:: በተለይ በልዩ የርእሰ አንቀጽ አጻጻፉ ሁሉም ያነሳዋል። የግጥም ሥራዎቹ በብዙዎች ዘንድ ተወዳጅነታቸው ላቅ ያለ ነው:: በተለያዩ ጊዜያትም በመድበሎቹ እየደበለ አሳትሟቸዋል:: ከግጥም መጽሐፍቶቹ ባሻገር በሌሎች ልዩ ልዩ ዘርፎች ላይም ብዕሩን አንስቷል:: በተለይ ደግሞ “ነገም ሌላ ቀን ነው” የተሰኘው የትርጉም ሥራው ዝነኛ ነው:: ከጉዞ ማስታወሻዎቹ በተጨማሪም፣ የተውኔት ሥራዎቹ የሆኑትን በአንድ ደጉሶ በመጽሐፍ መልክ አኑሯቸዋል::

በአንድ ወቅት አንጋፋው አርቲስት አበበ ባልቻ አንድ መድረክ ላይ ተገኝቶ ከነቢይ መኮንን ጋር ስለነበረው አጋጣሚ እንዲህ ሲል ነበር ያወጋው፤ “ነቢይን መጀመሪያ ያየሁት 1970 ዓ.ም ነበር:: በዚያ ዓመት የጀርመን ተማሪዎች ጂምናዚየም ነበርን:: ወደ ኬንያ የሚሄድ የቅርጫት ኳስና የእጅ ኳስ ቡድንም ልምምድ ጀምረናል:: ሶራ ጃርሶ የሚባል እኩያ የሌለው ሰው ነበር የሚያሰለጥነን:: በኋላም ነቢይን አየሁት:: እየሮጠና እንደ እንዝርት እየሾረ ... ጎበዝ ነው ብቻ ሳየው:: እሱ ተመረጠ:: እኔ ሳልመረጥ ቀረሁ:: እኔን ጸጋዬ ገ/መድኅንና አባተ መኩሪያ ተባብረው አስረው እዚህ መድረክ ላይ አወጡኝ:: እሱን ደግሞ ደርግ አስተባብሮ አሰረውና ወደ ሦስተኛ ወሰደው:: ከስምንት ዓመት በኋላ እንደገና ተገናኘን:: ተፈቶ ሲመጣ እኔ ስታሪንግ (ኮኮብ) ሆኜ ጠብቄዋለሁ:: እሱም በሲጋራ ወረቀት...” በማለት ትዝታውን አጋራ:: ያ አጋጣሚም ለነቢይ መኮንን እና ለአበበ ባልቻ ግንኙነት የመጀመሪያው እንጂ የመጨረሻው አልነበረም:: በመሀከላቸው አርቲስት ፍቃዱ ተ/ማርያምን አክለው ድንቅ የሆኑ ተውኔቶችንና የትርጉም ሥራዎችን ሠርተዋል:: በአንደኛው ቀንም አበበ ባልቻ ስለተመለከተው ስለ አንድ የውጭ ፊልም ለነቢይ ይተርክለታል:: ነቢይም አድምጦ ሲጨርስ ወዲያውኑ ብዕሩን ከወረቀት አገናኝቶ መጻፍ ጀመረ:: በመጨረሻም “ባለጉዳይ” የተሰኘው የቴሌቪዥን ድራማ ለመወለድ በቃ:: “ደራሲው ነቢይ በየጊዜው እንዲህ እንዲህ ነው እያለ ይጽፋል:: እኔና ፍቃዱም እንተውናለን” ሲልም ጭምር ነበር አበበ ባልቻ በትውስታው::

በሌላኛው ቀን ደግሞ ነቢይ ከአንዲት ጀርመናዊት ሴት የመኖሪያ ቤቷ ግርግዳና በር ላይ አንድ የሚያምር ረቂቅ (አብስትራክት) ሥዕል ይሥላል:: እናም ሰዎች እንደተመለከቱት “ይኼማ በእርግጠኝነት የሰይጣን ማምለኪያ ቤት ነው” በማለት በቁጣ በሯን ይደበድቡታል:: በነገሩ ግራ የተጋባችው ጀርመናዊትም በጣም አዝና ስታወራቸው እንዲህ ሲሉ ጠየቋት፤ “ቆይ ግን፣ እናንተ ሀገር ይህን እንዴት ነው የቻላችሁት? ... ናዚዎች አሉ:: አይሁዳዊው አለ ...” እሷም ለምላሸዋ የኤፍሬም ኔልሲንግን “ናታን ዘ ዋይዝ” ጠቢቡ ናታን አንስታ ተረከችላቸው:: ከጨዋታው በኋላም አበበ ባልቻ ወደ ሴትየዋ ጠጋ ብሎ ወደ ነቢይ እያመለከታት “ይኼ ሰውዬ እንዴት ቆንጆ አድርጎ ′ናታን ዘ ዋይዝ′ን መተርጎም ይፈልጋል መሰለሽ ...” አላት:: ምኞቱም ሰመረና ይኸው ትያትር በነቢይ ተተርጉሞና በአንድ ጀርመናዊ ዳይሬክት ተደርጎ በሀገር ፍቅር ቲያትር ቤት ለመታየት በቃ:: ”ጠቢቡ ናታን” የተሠራውም እንዲህ ባለው የአጋጣሚ መንገድ ነበር:: "ዐሥር" የሚሏት ቁጥር መቼም ከዚህ ሰው የሕይወት ጓሮ መሽከርከሯን አንዴ ቀጥላለችና ከአሥር ዓመታት በኋላም “ባለጉዳይ” የተሰኘው ድራማ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በድጋሚ የታየ ሲሆን፤ ከዚያ ሁሉ ጊዜ በኋላም በተመልካቹ ዘንድ አድናቆትን ተቸሮታል::

“ነቢይ በሀገሩ ይከበራል” የሚለውን ከፍ በማድረግ ግንቦት 30 ቀን 2011 ዓ.ም የነቢይ ወዳጅ ዘመድና አድናቂዎቹ ተሰባስበው በአዲስ አበባ ትያትርና የባህል አዳራሽ ውስጥ ተገናኝተው ነበር:: የመገናኘታቸው ምክንያት ደግሞ ነቢይ በዕድሜ ዘመኑ ከልጅነት እስከ ሽበት በኪነ ጥበቡ ውስጥ ስለሀገሩ መሸጎ፤ ለሀገሩ ላበረከተው ሁሉ በስሙ የምስጋና ዝግጅት ተሰናድቶ የነበረ መሆኑ ነው:: በዚህም በዚያም አጋጣሚ ሁሉ ስለ እርሱ ለማውራት የቆሙ ሰዎች ሁሉ ካለው ልዩ የጥበብ ችሎታው ጋር እኩል በእኩል ስለ ሰዋዊውና መልከ መልካም ባህሪው ያወሩለታል:: በብዙ ሙያዊ ጉዳዮች ዕውቀቱ የሰላ፣ ብቃቱ ደግሞ የሞላ ቢሆንም እንደ አጉል አዋቂዎች አንድም ቀን ቀረርቶውን የሚነፋና በሠራው የሚሸልል አልነበረም:: ለትንሹም ሆነ ለትልቁ ከሙያው ቆርሶ ሲያቋድስ ስስትን አያውቅም:: ባለማወቅ ስህተት ውስጥ ቢያገኛቸው እንኳን ያቺን የሚያውቃትን መንገድ ማሳየት እንጂ በንቀት ማብጠልጠልን አይችልበትም:: ለዚህም ነው ጀማሪ የጥበብ ሰዎች በተለየ ሁኔታ የሚቀርቡት::

ጥበብ ነው ሀገርህ፤
ባገር የመሸ ቀን
ሰው ሀገር አይነጋ፤
እስር ቤት ስደት ቤት
ሕይወት ስትላጋ፤
የእንክርትህ ጉዞ
ሀገርክን ፍለጋ፤
ማብቃቱ ታወቀኝ
ሲደርስ አፈሯ ጋ!

...

እያለ በግጥሙ ይቀጥላል:: ስለ ሀገሩ ባገሩ ቀልድ አያውቅም:: ባገኘበት አጋጣሚ ሁሉ ስለ ሀገሩ ማውራትና እንዲህ እንሁን፣ እንዲያ እያለ በተለይ ለወጣቱ ምክረ መድኃኒቱን ከመስጠትና ከማዘዝ ወደ ኋላ አይልም:: “′ሆድ ከሀገር ይሰፋል′ የሚለው ተረት ... እዚያ ጋር ግራጫው ዞን ግን ከዩኒቨርሲም ይሰፋል:: እንደሱ ብለን ካላሰብነው ደግሞ ጽንፈኛ እንሆናለን:: ጽንፈኛ ከሆንን ደግሞ ዕድሜ ልካችንን ከጦርነት አንወጣም:: ... ደርግ አንድ ጊዜ እንዲህ የሚል መግለጫ አውጥቶ ነበር፤ ′ዳሩ ሲነካ መካከሉ ዳር ይሆናል′ የሚል መግለጫ ነበረው:: ... በተለይ ወጣቶች በሩ እንደሚንኳኳ አውቀን በሩን በሥነ ሥርዓት መዝጋት ይኖርብናል:: ... ይህን ካላደረግን የኋላ መወነጃጀል፣ እሱ ነው እሱ ነው የሚል ሰርክል ነው የምንፈጥረው:: ... በዚህ ሰርክል ውስጥ ሁላችንም ስለሀገራችን ተጠያቂዎች ነን ማለት ነው” ይላል:: ተበደልኩኝ ... ተገፋሁኝ የማይል ሆኖ እንጂ እንደርሱ በፖለቲካ ዳፋ ውስጥ የተዳጠ አልነበረም:: ቢሠራ ሁሌም ሙያ በልብ፣ ቢገፋ በሁሉም እርሱ እንዳለውም “ሆድ ከሀገር ይሰፋል” ብሎ ችሎ ይኖራል እንጂ በምሬት ጮኾ ማጯጯህን አያውቅም:: ባይሆን በእንዲህ ዓይነቶቹ መሳቅ ይቀለዋል:: ነቢይ በሥራው ሁሉ እንደ ወርቅ በእሳት እየተፈተነ፤ የነጠረ የጥበብ ሰው ነበር:: አሳዛኙ ነገር የነቢይን ታላቅነትና ውለታ የሚያውቁ ጥቂቶች ብቻ መሆናቸው ነው:: ምናልባትም ደግሞ ከእርሱ በላይ ሥራዎቹ ታዋቂዎች ናቸው::

ነቢይ መኮንን በጠና ህመም ተይዞ በሕይወት ማቃሰት ከጀመረ ዋል አደር ብሎ ከረመ:: በትዳሩ የሦስት ልጆች አባት ለመሆን ቢበቃም፣ የዚህ ጊዜ ግን ባለቤቱና ልጆቹ በሀገር ውስጥ አልነበሩም:: ይህችን በጣር ሰቀቀን ውስጥ የምታምጠውን አንድ ነብሱን ለማዳን ደርሶ ያልነካው ዶክተር አልነበረም:: ሆኖም፣ የሁሉም ነገር ፍጻሜ ከዛሬ አንድ ወር በፊት ሆነ:: ሰኔ 28 ቀን 2016 ዓ.ም ላይ የሕይወቱ ሰኔና ሰኞ ገጠሙ:: አንድ ጊዜ የመጣባትን ምድር ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በ69 ዓመቱ ተሰናበታት:: በስተመጨረሻም ነቢይ በሀገሩ ስለሀገሩ ተከበረ::

# ዓለም አቀፍ



## ተደፍራ የተገደለችውን ህንዳዊት ዶክተር ተከትሎ የሀገሪቱ ዶክተሮች የሥራ ማቆም አድማ መቱ

በጋዜጣው ሪፖርተር

በህንድ ኮልካታ ከተማ በምትሰለጥንበት ሆስፒታል ተደፍራ የተገደለችውን ህንዳዊት ዶክተር ተከትሎ የሀገሪቱ ዶክተሮች ብሔራዊ የሥራ ማቆም አድማ መቱ።

የሀገሪቱን ዶክተሮች ያሰባሰበው የህንድ ህክምና ማህበር ሁሉም ድንገተኛ ያልሆኑ የሆስፒታል አገልግሎቶች በመላው ሀገሪቱ በትናንትናው ዕለት አገልግሎት መስጠት እንዳቆሙ ገልጿል።

ማህበሩ ባለፈው ሳምንት በባልደረባቸው ላይ የተፈጸመውን ግድያ “አረመኔያዊ ወንጀል” ሲል የጠራው ሲሆን ለሴቶች ደህንነቱ የተጠበቀ ባለመኖሩ እንደተፈጸመም ገልጿል።

ተቋሙ አክሎም ፍትህ ለማግኘት በሚደረገው ትግል ሕዝቡ ድጋፉን እንዲሰጥ ጠይቋል።

የዶክተሯን ግድያ በመቃወም እና ሴቶች የተሻለ ጥበቃ እንዲደረግላቸው የሚጠይቁ ሕዝባዊ ተቃውሞዎች ከቅርብ ቀናት ወዲህ በከፍተኛ ሁኔታ ተቀጣጥለው ይገኛሉ። ከነዚህ ተቃውሞዎች ጋር በተገናኘ አንድ ሆስፒታል ውድመት እንደደረሰበት ተገልጿል።

የአደጋ እና የድንገተኛ አገልግሎቶች እንደሚቀጥሉ የገለጸው የህክምና ማህበሩ የሥራ ማቆም አድማው ለ24 ሰዓታት ይቆያል ብሏል። በአንዳንድ የመንግሥት ሆስፒታሎች ውስጥ ያሉ ዶክተሮች የሥራ ማቆም አድማው ላልተወሰነ ጊዜ እንደሚቀጥል ነው ያስታወቁት።

ማህበሩ የሕክምና ባለሙያዎች ከጥቃት በተሻለ ሁኔታ ለመጠበቅ ሕጉን ማጠናከር፣ በሆስፒታሎች ውስጥ ያለውን የጸጥታ ሁኔታ ጥብቅ ማድረግ እንዲሁም ደህንነቱ የተጠበቀ ቦታዎችን መፍጠርን ጨምሮ ሌሎች ጥያቄዎችን አቅርቧል።

በዶክተሯ ግድያ ላይ “ጥልቅ እና በሙያ የታገዘ ምርመራ” እንዲከፈት እንዲሁም ለሟቿ ቤተሰቦች ካሳ እንዲከፈላቸው ማህበሩ ጠይቋል።

የ31 ዓመቷ ሰልጣኝ ዶክተር መንግሥታዊ በሆነው አርጂ ካር ሜዲካል ኮሌጅ ሆስፒታል ባለፈው ዓርብ በአሰቃቂ ሁኔታ መገደሏን ተከትሎ በሀገሪቱ ቁጣ ተቀስቅሷል።

ዶክተሯ እረፍት የለሽ የ36 ሰዓታት የፈረቃ ሥራዋን ካጠናቀቀች በኋላ ለመኝታ የተዘጋጀ ሥፍራ ባለመኖሩ ሥልጠና በሚሰጥበት ክፍል መተኛቷ ተነግሯል።

በማግሥቱ ጠዋት ባልደረቦቿ በከፍተኛ ሁኔታ ጉዳት የደረሰበት እና ግማሽ እርቃን የሆነውን ሕይወት አልባ ገላዋን አግኝተውታል።

ፖሊስ ወጣቷን ደፍሮ ገድሏል ያለው በጎ ፈቃደኛ በቁጥጥር ሥር ቢያውልም ነገር ግን ወንጀሉን ለመሸፋፈን እንዲሁም ቸልተኝነት ታይቶበታል የሚሉ ክሶች ቀርበውበታል።

ከዚህም ጋር ተያይዞ ጉዳዩ ከአካባቢው ፖሊስ ወደ ፌዴራል የምርመራ ቢሮ እንዲተላለፍ ተደርጓል።

የዶክተሯን ግድያ ተከትሎ በህንድ ተጨማሪ መደፈሮች ርዕሰ ዜናዎች ሆነዋል ይህንንም ተከትሎ የሀገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ናሬንድራ ሞዲ “በሴቶች ላይ አረመኔያዊ ድርጊቶችን የሚፈጽሙ በአስቸኳይ እና በከፋ ሊቀጡ ይገባል” ብለዋል።

## ዩክሬን በኩርስክ ግዛት እያካሄደች ባለችው ጥቃት ቁልፍ ድልድይ አወደመች

በጋዜጣው ሪፖርተር



ዩክሬን በኩርስክ ግዛት እያካሄደች ባለችው ጥቃት ቁልፍ ድልድይ አወደመች።

ዩክሬን በሩሲያ ኩርስክ ግዛት ጥሳ በመግባት እየፈጸመችው ያለው ጥቃት አሁን ሁለተኛ ሳምንቱን አስቆጥሯል።

ዩክሬን በፈጸመችው በዚህ ድንገተኛ ጥቃት 120 ሺህ ሰዎች ከቀያቸው እንዲፈናቀሉ አስገድዷል። ዩክሬን በኩርስክ ግዛት ተጨማሪ ቦታዎችን መያዟን እየገለጸች ቢሆንም፣ ሩሲያን የመውረር ፍላጎት እንዳልነበራት በተደጋጋሚ ተናግራለች።

"ዩክሬን የሩሲያን ግዛት የመውረር ፍላጎት የላትም" ሲሉ የዩክሬኑ ፕሬዝደንት ቮሎድሚር ዘለንስኪ ከፍተኛ አማካሪ ዓርብ ዕለት ተናግረዋል።

አማካሪው ማይካይሎ ፖዶሊያክ የሩሲያን ግዛት የመውረር ቁልፉ ዓላማ ሞስኮ "እኛ ባስቀመጥነው ቅድመ ሁኔታ" እንድትደራደር ማድረግ ነው ብለዋል።

"በኩርስክ ግዛት ሩሲያ ፍትሀዊ ወደ ሆነ ድርድር እንድትመጣ ወታደራዊ አማራጭ እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውል አይተናል" ሲሉ በኤክስ ገጻቸው የገለጹት አማካሪው አክለውም ኬቭ "ውጤታማ የማስገደጃ ዘዴ" ምን እንደሆነ አረጋግጣለች ብለዋል።

የዩክሬኑ ኢታማዦር ሹም አሌክሳንደር ሲይርስኪ የማጥቃት ዘመቻው መሻሻል እያሳየ ነው ብለዋል። "በማጥቃት ላይ ያሉት ወታደሮች እየተዋጉ መሆናቸውን እና በአንድ አንድ ቦታዎች ከአንድ እስከ ሶስት ኪሎ ሜትር ወደ ጠላት መጠጋታቸውን" በማህበራዊ ሚዲያ በተለቀቀ ቪዲዮ ሲርስኪ ለዘለንስኪ ሲናገሩ ተደምጠዋል።

ሲርስኪ ከድንበር 13 ኪሎ ሜትር ላይ በምትገኘው ማላ ሎክንያ መንደር አቅራቢያ እየተደረገ ባለው ውጊያ "ብዙ እስረኞችን" እንደሚያስለቅቁ ተስፋ ማድረጋቸውን ተናግረዋል።

ዩክሬን ወደ ፊት እየገፋች ሲሆን ከዩክሬን ጋር ድንበርተኛ የሆነችው የሩሲያዋ ቤልጎሮድ ባለሥልጣናት ከሰኞ ጀምሮ የአምስት መንደሮች ነዋሪዎችን እንደሚያስወጡ እየተናገሩ ናቸው።

የዩክሬን ኃይሎች በምዕራብ ሩሲያ ወደፊት መግፋታቸውን ቢገልጹም፣ የሩሲያ ኃይሎችም በመሳሳይ በምስራቅ ዩክሬን ተጨማሪ ቦታዎችን እየያዙ ነው ተብሏል። በትናንትናው ዕለት ሞስኮ ወታደሮቿ ሰርሂቪካ የተባለች ከተማ መያዛቸውን ገልጻለች።

በቅርቡ የተያዙት ቦታዎች፣ የሩሲያ ኃይሎች የዩክሬን ኃይሎች እንደ ሎጂሴቲክ ማዕከል ወደሚጠቀሙባት ፖክሮቭስክ ከተማ እንዲቀርቡ አስችሏቸዋል። ፖክሬቭስክ በሩሲያ ቁጥጥር ስር ከአለው የዶኔስክ ግዛት በሰሜን ምዕራብ የሚገኝ ከተማ ነው።

የከተማዋ ዋና አስተዳዳሪ የሆኑት ሰርጌ ዶብሪያክ ባስተላለፉት መልእክት የሩሲያ ኃይሎች ወደ ከተማዋ ዳርቻዎች እየመጡ ስለሆነ ሕዝብ እንዲወጣ አሳስበዋል።

ዩክሬን እስካሁን በኩርስክ ግዛት እየፈጸመች ባለው ጥቃት ከአንድ ሺህ ስኩየር ኪሎ ሜትር በላይ ስፋት ያለው መሬት መቆጣጠሯን ገልጻለች።

ጥቃቱን አደገኛ ትንኮሳ ሲሉ የገለጹት ፑቲን በኩርስክ ግዛት የገባው ኃይል እንዲደመሰስ ትዕዛዝ ማስተላለፋቸው ይታወሳል ሲል የዘገበው አል ዓይን ነው።


## ማስታወቂያ

ኢንተርናሽናል ክራይሲስ ኤድ የተባለ የውጭ ድርጅት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን በመዝገብ ቁጥር 1834 መስከረም 05 ቀን 2012 ዓ.ም የተሰጠው የምዝገባ የምስክር ወረቀት እና መተዳደሪያ ደንብ ጠፋብኝ ብሎ በ11/11/2016 በቁጥር ICA/032/24 እና በቁጥር ICA/031/24 በተጻፈ ደብዳቤ ጠይቋል።

ስለሆነም የተጠቀሰውን የምዝገባ ምስክር ወረቀት እና መተዳደሪያ ደንብ ወድቆ ያገኘ ወይም በዕዳ ይዤዋለሁ የሚል ወይም ማንኛውም ጉዳይ ይመለከተኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሰባት (7) ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን ህብረት ኢንሹራንስ ህንጻ 4ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 406 ድረስ በመቅረብ ካላመለከተ ተለዋጭ የምዝገባ ሠርተፍኬት እና መተዳደሪያ ደንብ የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን**



## የደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ክልል በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ በወረዳ 04 ቤት ቁጥር B3F2H2/4 በ0005511809 ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር(tin) ለሚታወቁ ዮሴፍ ወልቀማ ኡስማን ንግድ ድርጅት በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት ከአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የህትመት ፍቃድ በማግኘት ከምጠቀምባቸው ደረሰኞች ውስጥ እጅ በእጅ ሻት ደረሰኝ 0517-0550 ያልተሰራበት ጥቅም _ ላይ ሳይውል ስለጠፋብኝ በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብተው ወንጀል እንዳይሰራባቸው እና የጠፋ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል። ይሁንና ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዢ በማከናወን ክፍያ ለመፈጸሙ በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው  ግብርናታክስ ከፋይነት ለተመዘገበበት የ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ወይም አቅራቢያው ለሚገኝ ገቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ እንጠይቃለን::

**ድርጅቱ በግብር ከፋይነት የሚታወቅበት ስም ዮሴፍ ወልቀማ ኡስማን**



## የጨረታ ማስታወቂያ

የሱሉልታ ወረዳ ፍርድ ቤት ለ 2017 የበጀት ዓመት ግዢ

1. ቋሚ እቃዎች (የቢሮ ፈርኒቸሮች)
2. የሠራተኞች የደንብ ልብስ
3. የፅዳት እቃዎች
4. ህትመት
5. ስቴሽነሪ እና
6. የኤሌክትሮኒክሰ ዕቃዎችበጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡

**በዚህ መሰረት:-**

1. በጨረታው ለመካፈል የምትፈልጉ ተጫራቾች በተጠቀሱት የስራ መስኮች የተሰማራችሁ ነጋዴዎች የዘመኑን የታደሰ የንግድ ፍቃድ እና TIN ያላቸው መሳተፍ ትችላላችሁ።
2. የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና 15,000 (አስራ አምስት ሺ ብር) CPO በ ሱሉልታ ወረዳ ፍርድ ቤት በሚል ስም በማሰራት ማቅረብ ይችላሉ፡፡
3. የጨረታ ሰነዱን በስራ ሰዓት የማይመለስ ብር 100 /አንድ መቶ ብር/ በመክፈል ከሱሉልታ ፍርድ ቤት ማግዛት ይችላሉ፡፡
4. ጨረታው የሚከፈተው ይህ መስታወቂያ በወጣ በ 15ተኛ ቀን ከጠዋቱ 4:00 ሰዓት ተጫራቾቹ ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በሱሉልታ ወረዳ ፍርድ ቤት ይሆናል፡፡
5. ተጫራቾች ተጨማሪ የእሴት ታክስ ( VAT) ተመዝጋቢ የሆኑና የቲን ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው፡፡
6. መስሪያ ቤቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው።

አድራሻ:- ስልክ ቁጥር 0111880817/ 0912647844

**በሰሜን ሸዋ ዞን የሱሉልታ ወረዳ ፍርድ ቤት**

# ስፖርት





# አነጋጋሪው የኦሊምፒክ ኮሚቴ ምላሽ

ብርሃን ፈይሳ


የኢትዮጵያ የፓሪስ ኦሊምፒክ ተሳትፎ እና የኦሊምፒክ ኮሚቴው ተግባራት ተከትሎ የስፖርት ቤተሰቡ በብርቱ እየተቃወመው ይገኛል:: ይህንን እንዲሁም ተሳትፎውን በተመለከተም የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ ለመጀመሪያ ጊዜ ጋዜጣዊ መግለጫ የሰጠ ሲሆን፤ በብዛት ሲነሱ ለቆዩ ጉዳዮችም ምላሽ ሰጥቷል::

ከፓሪስ ኦሊምፒክ ጋር ተያይዞ ከተነሱ አወዛጋቢ ጉዳዮች መካከል አንዱ የሆነው በድብቅ የተከናወነው የኮሚቴው ሥራ አስፈጻሚ ቦርድ ምርጫ መሆኑ ይታወቃል:: ከዚህም ጋር ተያይዞ ኮሚቴው የሚመሠርቱት ብሄራዊ የስፖርት ማህበራት ባላወቅነውና ባልተሳተፍንበት ሁኔታ ምርጫው መደረጉ የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ሕግን እንዲሁም የዓለም አቀፉን ኦሊምፒክ ኮሚቴ ቻርተርን የሚጥስ በመሆኑ ሕገወጥ እንደሆነ ከሰሞኑ ባቀረቡት አቤቱታ ላይ ገልጸው ነበር:: ይህንን በሚመለከትም የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ ፕሬዚዳንት ዶ/ር አሸብር ገብረጊዮርጊስ በሰጡት ምላሽ ‹‹ምርጫ የተካሄደው ሕግና ሥርዓትን ጠብቆ ነው ስለዚህም ትክክል ነው:: በቀረበው አቤቱታም አንረበሽም›› ብለዋል:: በተጨማሪም ክሱ ወደ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የተላከ እንጂ ወደ ኮሚቴው የደረሰ ባለመሆኑ ተቋማዊ አሠራርን ያልተከተለ እንደሆነም አንስተዋል::

ኦሊምፒኩን ተከትሎ ሕዝቡን ካስከፉ ጉዳዮች መካከል አንዱ ‹‹ኦሊምፒክ ተሳትፎ ነው›› የሚለው ሃሳብ ሲሆን፤ በአትሌቲክስ ስፖርት ሜዳሊያዎችን ስትሰበስብ ለቆየች ሀገር ተሳትፎ በሚል ቃል መወሰኑን በርካቶች ተችተው ነበር:: ለዚህም የኮሚቴው ፕሬዚዳንት ዶ/ር አሸብር ‹‹ሕዝባችን ያለመደው ቃል በመሆኑ ይቅርታ እንጠይቃለን›› ብለዋል:: ይሁን እንጂ ‹‹ተሳትፎ›› የሚለውን ቃል የተጠቀሙት ቻርተሩ (የኦሊምፒክ ፍልስፍና) ባስቀመጠው መሠረት እንጂ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሜዳሊያ አይገባውም ለማለት አይደለም:: በውድድሩ ወቅት በርካታ ሜዳሊያዎችን ማሳካት ባይቻልም ሲሠራ የቆየው ወርቅ፣ ብር ወይም ነሃስ ለማግኘት እንደሆነ መገንዘብ አስፈላጊ መሆኑንም አሳስበዋል::

ከሪዮ ኦሊምፒክ ጀምሮ ለጠፋው ውጤት ሁሉም እንደየድርሻው ተጠያቂ መሆኑን ፕሬዚዳንቱ ይጠቁማሉ:: ነገር ግን አትሌቶችን ማዘጋጀት፣ በፕሮጀክት መያዝ፣ ብሄራዊ አሠልጣኞችን መያዝና ማፍረስም የኮሚቴው ሥራ አይደለም:: የትኛውም ፌዴሬሽን እቅድ በማውጣት ለአሸናፊነት መሥራት ይኖርበታል፤ የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ ደግሞ በተቀመጠለትና በተሰጠው ኃላፊነት ልክ ድጋፍ ያደርጋል እንጂ ሥራቸው ውስጥ ጣልቃ አይገባም:: ስለዚህ ይህንን መሰል ጥያቄ ሊቀርብ የሚገባው ለብሄራዊ ፌዴሬሽኖች ነው፤ ባለፉት ወራት የፓሪስ ኦሊምፒክ የዝግጅት ወቅት ኮሚቴው ያጎደለው ነገር ካለ ግን ሊጠየቅ ይገባል:: ከዚያ ባለፈ ግን ‹‹የጅምላ ጭፍጨፋ ተገቢ አይደለም›› ሲሉ ጉዳዩን ወደ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ገፍተዋል::

ኢትዮጵያ በፓሪስ የኦሊምፒክ መድረክ ውጤት ያሳጣትና ተሳታፊ አትሌቶችም ከሚታወቁበት በተቃራኒ ተፎካካሪነታቸው አንሶ ለመታየቱ በርካታ ጉዳዮች በምክንያትነት ይነሳሉ:: ከእነዚህ መካከል አንዱ ደግሞ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን እና ኦሊምፒክ ኮሚቴ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት በምርጫው ሳይቀር ጣልቃ በመግባታቸው በመሆኑ ነው:: ለዚህም ኮሚቴው በመግለጫው ላይ ባቀረበው የፓሪስ ኦሊምፒክ ተሳትፎ ሪፖርት ላይ የወርቅ ሜዳሊያ ባለቤት የሆነው የማራቶን አትሌት ታምራት ቶላ ከተጠባባቂነት ተነስቶ ተሳታፊ እንዲሆን ኮሚቴው ሚና እንደነበረው በመግለጽ በራሱ ላይ መስክሯል:: ይሁንና ቅሬታ ሲያቀርቡ ለነበሩ ሌሎች አትሌቶች ምላሽ ያለመስጠታቸው በተለየ ምክንያት መሆኑ ተጠቁሟል:: በተለይ አትሌት ፍሬወይኒ ኃይሉ ጋር በተገናኘ ከአንድ በላይ ርቀት ተሳታፊ የነበረችውን አትሌት ጉዳፍ ጸጋይን ለማወያየት ቢሞከርም ካለችበት አቋምና ሀገሯን ለማስጠራት ከነበራት ጉጉት አንጻር አልተቻለም:: በውድድሩም ወቅት ባልተጠበቀ ሁኔታ ህመምም ስለነበረባት ውጤታማ ሳትሆን ቀርታለች::





የዮሚፍ ቀጄላ ቅሬታም በሁለት ርቀት የሚሮጠው በ10ሺ ሜትር ሜዳሊያ ካገኘ በሚል ቢሆንም የሆነ ነገር አልነበረም:: ሌላዋ መሰል ቅሬታዋን ያቀረበችው አትሌት ፍሬህይወት..... ከስፖርት አበረታች ቅመሞች ምርመራ አለማድረግ ጋር የተያያዘ መሆኑን በመግለጫው ተጠቁሟል:: ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ጸረ አበረታች ቅመሞች ባለሥልጣን አትሌቷ በእጩ ዝርዝር ውስጥ ባለመኖሯ በምርመራው ያልተካተተች መሆኑን አንጸባርቋል:: ከዚህ ባለፈ አንድም አትሌት ምርጫ ላይ ፕሬዚዳንቱ እጃቸው እንደሌለ ነው ያረጋገጡት::

ከስፖርት ወዳዱ የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ከብሄራዊ የስፖርት ማህበራት እንዲሁም ከስፖርት ሙያተኞች ሲነሱ የቆዩ ቅሬታዎችን ተከትሎ ፕሬዚዳንቱ እንዲሁም የሥራ አስፈጻሚ ቦርዱ ራሱን ከሥልጣን እንዲያነሳም በተደጋጋሚ ተጠይቆ ነበር:: ምላሻቸው ግን ‹‹ከዚህ ቀደም እግር ኳስን ጥዬ ወጥቻለሁ የመጣ ለውጥ ግን አልነበረም:: ጥሎ መውጣት መፍትሄ አይደለም፤ ስለዚህም ሥስልጣኑን አልለቅም›› ሲሉ ገልጸዋል::


## ግልፅ የጨረታ ማስታወቂያ
## የጨረታ ቁጥር ኢኤአ/ምስ.አ.አ.ዲስ/ግጨ/003/2016

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት
Ethiopian Electric Utility

በኢትዮጵያ ኤሌክተሪክ አገልግሎት የአዲስ አበባ ከተማ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የምስራቅ አዲስ አበባ ዲስትሪክት ቁጥ- 9 አገ/መ/ማዕከል ለደንበኞች አገልግሎት አመቺ የሆነ ከለሚ ኩራ ክ/ከተማ እስከ አያት አደባባይ ዙሪያ እና ከ ጣፎ መስመር እስከ ለሚኩራ ክ/ከተማ ፖሊስ መምሪያው ድረስ ባለው አካባቢ የሚገኝ የቢሮ ኪራይ አገልግሎት በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ መከራየት ይፈልጋል፡፡

| ተ.ቁ | የግዥው ዓይነት | ስፋት በካሬ ሜትር | የጨረታ ዋስትና ማስከበሪያ (CPO) | የጨረታ መዝጊያና ቀን እና ሰዓት | የጨረታ መከፈቻ ቀን እና ሰዓት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የቢሮ ኪራይ አገልግሎት ግዥ | 400 | ብር 8,000.00 (ስምንት ሺህ) | ነሀሴ 20 ቀን 2016 8፡00 | ነሀሴ 20 ቀን 2016 8፡30 |

1. ማንኛውም በዘርፉ የተሰማራ የዘመኑ ግብር የተከፈለበት የንግድ ፈቃድ ያለው ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ያለው እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆነ በጨረታው መሳተፍ ይችላል፡፡
2. ተጫራቾች ዝርዝር መግለጫ የያዘውን የጨረታ ሰነድ ጨረታው ከወጣበት ቀን ጀምሮ ዘወትር በስራ ሰዓት ኮተቤ ብረታብረት ፊትለፊት የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ግቢውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ ኤሌክትሪክ አገልግሎት- የምስራቅ አዲስ አበባ ዲስትሪክት ግዥ፣ ሎጂስቲክስ ንብረትና እና ፋሲሊቲ ቢሮ ቁጥር 113 የማይመለስ ብር 300.00 (ሶስት መቶ ብር) በመክፈል መውሰድ ይችላሉ፡፡
3. ተጫራቾች የመወዳደርያ ሰነዳቸውንና የጨረታ ዋስትና ማስከበሪያ ብር 8,000.00 /ስምንት ሺህ/ በባንክ በተረጋገጠ ቼክ /CPO/ ወይም በቅድመ ሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና (Bid Bond/ በማድረግ በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ እስከ ነሀሴ 20 ቀን 2016 ዓ.ም ከሰዓት በኋላ 8፡00 ሰዓት ድረስ ከላይ በተራ ቁጥር 2 በተገለጸው አድራሻ የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት አለባቸው፡፡
4. ጨረታው በተመሳሳይ ቀን ነሀሴ 20 ቀን 2016 ዓ.ም 8፡00 ሰዓት ተዘግቶ በዚሁ ዕለት ነሀሴ 20 ቀን ቀን 2016 ዓ.ም ከሰዓት በኋላ በ8፡30 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት/ባይገኙም ግዥ፣ ሎጂስቲክስ ንብረትና እና ፋሲሊቲ ቢሮ ቁጥር 113 ይከፈታል፡፡
5. ተጨማሪ ማብራሪያ ቢያስፈልግዎ በስልክ ቁጥር +251-116-67-58-65፤011-667-58-75 መደወል ይችላሉ።
6. ድርጅቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ ኤሌክትሪክ አገልግሎት**
**የምስራቅ አዲስ አበባ ዲስትሪክት**

## የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ

የፍባለመብት አቶ እስጢፋኖስ መብራቱ እና በፍ/ባለዕዳ አቶ ደሊሉ ረሺድ መካከል ስላለው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 03318 30/10/2015 ዓ.ም እና መ/ቁ 08533 በ23/7/2016 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ሸገር /ክ/ከተማ ወረዳ 8 ቡሩክ ፕላሲቲክ ማምረቻ ግቢ ወስጥ ሪሳይክልንግ ማሽን የሐራጅ ሽያጭ መነሻ ዋጋ ብር320,000 (ሶስት መቶ ሃያ ሺ ብር) ሆኖ የትራንዛክሽን ታክስ ገዥ የሚከፍል መሆኑ ታውቆ መስከረም 10 ቀን 2017 ዓ/ም በሐራጅ ይሸጣል፡፡ የተጫራቾች ምዝገባ በ5፡00 ሰዓት ተጀምሮ የቀረቡ ተጫራቾች ተመዝግበው እንደተጠናቀቀ ወዲያወኑ ጨረታው የሚካሄድ ይሆናል፡፡

የሐራጁ ሽያጭ የሚካሄደው በፌደራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የጨረታ አዳራሽ ውስጥ ሲሆን፣ ንብረቱን ተጫርተው ለመግዛት የሚፈልጉ ተጫራቾች ከጨረታው ቀደም ብሎ ባሉት አራት የሥራ ቀናቶች ውስጥ ባለመብቱ ለማስጎብኘት በሚመርጧቸው ሶስት የስራ ቀናት በፌ/ፍ/ቤቶች ፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ሐራጅ ክፍል ድረስ ከጠዋቱ በ3፡30 ጀምሮ በመገኘትና ባለመብቱ በሚያቀርበው ትራንስፖርት ንብረቱን ባለበት ቦታ ድረስ በመውሰድ መጎብኘት የሚችሉ ሲሆን እያንዳንዱ ተጫራች በሚጫረትበት ወቅት የንብረቱን ግምት 1/4 ኛውን በንግድ ባንክ በተረጋገጠ C.P.O ማስያዝ ይኖርበታል፡፡፡ ከ1/4ኛ አስበልጦም ሆነ አሳንሶ C.P.O የሚመጣ ተጫራች በጨረታው አይካፈልም፡፡ በጨረታው አሸናፊ የሆነው ግለሰብ አሸናፊ የሆነበትን ገንዘብ በአጠቃላይ ጨረታውን ከአሸነፈበት ቀን ጀምሮ በፍ/አ/ዳ/ስም CPO አሰርተው በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በተከፈተ አሰርቶ ሙሉ ገንዘቡን በ15 ቀናት ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት የፍ/አ/ዳይሬክቶሬት ንብረቱን በህጋዊ መንገድ በሀራጅ ስለመሸጡ ለሚመለከተው አካል ማስረጃ ከመፃፍ ባለፈ ስም የማዞወር ግዴታ የሌለበት መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈፃፀም**
**ዳይሬክቶሬት**